# ኢስላም ለሰው ልጆች ተፈጥሮ ምቹ ሃይማኖት

በአላህ ስም በጣም አዛኝና በጣም ሩህሩህ በሆነው ።

ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው፡፡ሰላትና ሰላም በሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)፣ በቤተስቦቹ እና በባልደረቦቹ ላይ ይሁን። የእስልምና ሃይማኖት ሙስሊም ባልሆኑ ህዝቦች ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝና እንዲስፋፋ ካደረጉት መሰረታዊ ምክንያቶች በዋነኝነት የእስልምና ሃይማኖት የእምነት መርሆቹን ለመማርና በጥልቀት ለመገንዘብ፣ የሃማኖቱ አምልኮአዊ ተግባራት ደንብና ስርዓት በተግባር ላይ ለማዋል፣የሰዎች ምድራዊ ህይወት ስኬታማ በሆነ መንገድ ለመምራት የተደነገጉ ህግጋት ቀላል ምቹና ውስብስብ ባለመሆናቸውና፣ አላህ የሰው ልጅን ከፈጠረበት ንፁህ ተፈጥሮአዊ ማንነት ጋር የማይጋጩና የሚስማሙ በመሆናቸው ነው። ይህ ከሌሎች እምነቶች አንፃር የኢስላም ልዩ መገለጫው ነው።

ይህን በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) በተከበረው ንግግሩ እንዲህ ብሎ ገልፆታል።

"ፊትህንወደ እውነት ተዘንባይ ኾነህም ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ። የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በእርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃይማኖት ያዟት)። የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም። ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው። ግን አብዛኞዎቹ ሰዎች አያውቁም" አልሩም 30

ለዚህም የኢስላም ሃይማኖት ባህሪ አይነተኛ ምሳሌ ይሆነን ዘንድ ኢስላም የሰዎችን ተፈጥሮአዊ የግብረ ስጋዊ ፍላጎት ያስተናገደበት መንገድ ማንሳት ይቻላል።የሰው ልጅን ግብረ ስጋዊ ፍላጎት ተፈጥሮአዊ እንደመሆኑ መጠን ኢስላም ይሄን ተግባር መፈፀም አላንቋሸሸም ወይንም እንደ አፀያፊ ተግባር በመቁጠር እሱን እንዳይፈጽሙ ክልክል አላደረገም። ነገር ግን ይህን ተፈጥሮአዊ ስሜታዊ ፍላጎት ተገቢ በሆነ መንገድ ተግባራዊ እንዲደረግ ያበረታታል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ በማለት፡- "ያላገቡ ወጣቶቻችሁን አጋቡ...."። ሰዎች ይህን ተፈጥሮአዊ ፍላጎት አግባብ ባለው መንገድ በመፈፀም ይረኩ ዘንድ የአላህ መልዕክተኛም እንዲህ በማለት አብራርተዋል። "እናንተ ወጣቶች ሆይ ከናንተ ውስጥ የትዳርን መስፈርት ማሟላት የሚችል ሰው ያግባ። ይሄም አይኑን እንዲሰብር፤ ብልቱን እንዲጠብቅ ያደርገዋል። ያን ማድረግ ያልቻለ በመጾም አደራችሁን ጾም ለናንተ ጋሻ ነው።

ኢስላም በአንድ በኩል ይህን የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ስጋዊ ተራክቦ ተግባራዊ በማድረግ እርካታ እንዲያገኝ ሲፈቅድ በሌላ በኩል ደግሞ ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ የሚፈፀም ልቅና ስድ ተግባር አላደረገውም።በትክክለኛ እና ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ተግባራዊ በማድረግ እርካታና ደስታ እንዲገኙ ስርዓት አበጅቶለታል። ይህም መንገድ በትዳር ውስጥ ብቻና ብቻ እንዲሆን አድርጎታል፡ ፡ በትዳር ውስጥ መረጋጋትና ስክነት ይገኛል እነዚህ ነገሮች ደግሞ ሁሉም ሰው ለማግኘት የሚጓጓው ነገር ነው። ትዳር በባለትዳሮች መካከል የመፈቃቀርና የመዋደድ ስሜት ስለሚፈጥር

የትዳር ህይወትን ዘለቄታ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ደንብና ስርዓት አክብሮ የሚፈጸም ትዳር ለባለትዳሮቹ አካላዊና መንፈሳዊ እርካታ ከማጎናጸፉ በተጨማሪ የዘር ሀረጋቸው እንዲቀጥል ምክንያት ስለሚሆን ቀጣይነት ያለው ደስታና የተረጋጋ ህይወት እንዲመሩ ያስችላል፡፡
አላህ (ሱ.ወ) እንደገለፀው፡-

"ለእናንተም ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደእነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ተዓምራቶች አሉ፡፡"

ከትዳር ውጪ የሚፈጸም ግብረስጋዊ ግንኙነት የተለያዩ በሽታዎች እንዲስፋፉ፣ የዘር ግንድ የሚቆራርጥ፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ክብር የማይሰጣቸው የዝሙት የሚወለዱ ልጆች እንዲስፋፉ ስለሚደርግ ኢስላም ከትዳር ውጪ የሚደረግ ስጋዊ ተራክቦ ከልክሏል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

"ዝሙትንም አትቅረቡ፡፡ እርሱ በእርግጥ መጥፎ ሥራ ነውና፡፡ መንገድነቱም ከፋ!"

በዚህ መንገድ የትዳርን አስፈላጊነት ጠቀሜታ የማስቀመጡን ያህል ባለትዳሮች በትዳር አብረው መቀጠል የማይችሉባቸው ሁኔታዎች ሲከሰቱ አንዴ ተጋብተዋልና እስከ ህይወታቸው ፍጻሜ በአንድ ላይ እንዲኖሩ አያስገድድም፡፡ ለወንድም ለሴትም የመለያየት መብት ሰጥቷል፡፡ ሁለቱ የትዳር አጋሮች ከሁለቱ አንዱ ትዳራቸውን መቀጠል ካልፈለጉ የሁለቱንም መብትና ግዴታ በሚያስከብር መንገድ እንዲለያዩ ይደነግጋል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ኢስላም ስኬታማ ማህበረሰብ ይፈጠር ዘንድ ደስተኛ ቤተሰብ መመስረት አላማ ያደረገ በመሆኑ ነው፡፡

በሌሎቹም የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ የህይወት ዘርፎችም በተመሳሳይ መልኩ ኢስላም ለሰዎች ለተፈጥሮአዊ ማንነታቸው ቀላሉንና ምቹ የሆነዉን መንገድ ነው የተከተለው፡፡የሰው ልጅን ነፍስ አቅሟ ከሚችለው በላይ አላሸከማትም፡፡እነዚህ የኢስላም ባህርያት አላህ ለሰው ልጆች ምድራዊም ሆነ መጻኢ የህይወት ስኬት እንዲጎናፀፉ ለአለም ህዝቦች የወደደውና፣ የመረጠው የመጨረሻው ሃይማኖት ነው፡፡

ይህን ሃይማኖት የተከተለ ሰው ሁሉ ምድራዊ ህይወቱ ምቾትና የመንፈስ መረጋጋትን የሚሰያጎናፅፈው ሲሆን በቀጣይ ህይወት ደግሞ የዘላለማዊ ደስታ ባለቤት ይሆናል፡፡በአንፃሩ ደግሞ ከዚህ መንገድ የራቀ በቅርቢቱ አለም የጭንቀትና የመከራ ሂይወት የሚገፋ በቀጣዩ ዘላለማዊ ህይወቱም ከዚህ የከፋ ነገር ይጠብቀዋል፡፡ጌታችንን አላህ ከዚህ እንዲጠብቀን እንማፀነዋለን፡፡

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ከጎዶሎነት የፀዳ ካልሆነ ዘንዳ ኢስላም ይሄን የሰው ልጅ ተፈጥሮ ማስተናገድ የሚችል እጅግ በጣም ምቹና ገር የሆነ ሃይማኖት ነው፡፡ በተለይ የፈጣሪን ትዕዛዝ ተግባራዊ በማድረግ በኩል በሚፈጠሩ ጉድለቶችና ስህተቶች በይቅርባይነትና በምህረት የተገነባ ሃይማኖት ነው በአንድ ነገር ብቻ ሲቀር፡፡ እሱም ከአላህ ውጪ ሌላን መገዛትና በሱ ላይ ባላንጣ ማድረግን ነው፡፡ ከእንዲህ ያሉ ድርጊቶች ጥራት የተገባው አላህ የማይወደው ነገር ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ይህን በማስመልከት ሲገልፅልን፦

"አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም፡፡ ከዚህ ሌላ ያለውንም (ኀጢአት) ለሚሻው ሰው ይምራል፡፡ በአላህም የሚያጋራ ሰው ታላቅን ኀጢአት በእርግጥ ቀጠፈ፡፡"

ኢስላም ሙስሊሞች ከፈፀሟቸው ስህተቶችና ወንጀሎች ነፃ እንዲሆኑ ወደ ፈጣሪያቸው ፊታቸውን አዙረው ለሰሩት ስህተትና ወንጀል ተፀፅተው ምህረት እንዲያደርግላቸው ከለመኑት የሰሩት ጥፋት እንደሚያብስላቸው በመንገር አዕምሮዋቸውን ያናግራል፡፡ ነፍሳቸውንም ያክማ፡፡ ይህም አላህ ቸርና ለጋስ ጌታ በመሆኑ ነው፡፡ ከወንጀል መፀፀት ምህረትን ብቻ ሳይሆን የሚያጎናፅፈው ለፈጣሪ ብሎ በመተው የባለ ትልቅ ምንዳ ባለቤትም ያደርጋል፡፡ ከዚህ የበለጠ ገርነት ከየት ይገኛል፡፡ አላህ (ሰ.ወ) በቁርዓኑ እንዲህ ይላል፦

" በላቸው «እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ፡፡ አላህ ኃጢኣቶችን በመላ ይምራልና፡፡ እነሆ እርሱ መሓሪው አዛኙ ነውና፡፡" ዙመር 53

በኢስላም ከወንጀል ምህረት የሚጠየቅበት መንገድ ለሰው ልጆች ቀላልና ገር የማይከብድ አድርገነታል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡

"መጥፎም የሚሠራ ሰው ወይም ነፍሱን የሚበድል ከዚያም (ተጸጽቶ) አላህን ምሕረት የሚለምን አላህን መሓሪ አዛኝ ኾኖ ያገኘዋል፡፡" ኒሳዕ 110

በሌላ የቁርዓን አንቀጹም አላህ እንዲህ አለ፦

"እርሱም ያ ከባሮቹ ንስሓን የሚቀበል፣ ከኃጢአቶችም ይቅር የሚል፣ የምትሠሩትንም ሁሉ የሚያውቅ ነው፡፡"

ወንጀል በመስራት አዘውትራ ስህተት ላይ የምትዘፈቀዋን የሰው ልጅ ነፍስ ኢስላም የሚንከባከባት፤ ችላ የማይልና የሚጠብቃት የሆነ ሃይማኖት ነው፡፡ የሰው ልጅ የፈለገውን ያህል በወንጀል አረንቋ ቢዘፈቅ ከልብ በመፀፀት ወደ ፈጣሪው መመለሱ ብቻ የፈጣሪውን ምህረት ማግኛ መንገድ አድርጎለታል፡፡ የአላህ መልእክተኛ እንዳሉት፡

"ሰይጣን አለ ጌታዬ በልእቅናህ ይሁንብኝ ባሮችህን የጥሜት ጎዳና ከመምራት አልወገድም ነፍሳቸው ከአካላቸው እስካልተለየች ድረስ፡፡ አላህም አለ በበላይነቴና በታላቅነቴ ይሁንብኝ ባሮቼ ምህረት እስከጠየቁኝ ድረስ ለነሱ ምህረትን ከማድረግ አልወገድም፡፡"

ሰዎች ተገደው ወይም በስህተት ወይም በመርሳት ለሚፈጽሟቸው ማንኛቸውም ወንጀሎች አላህ ምህረት ይለግሳቸዋል፡፡ የሰዎች የመጨረሻዎቹ የህይወት ፍፃሜ የእድሜ ዘመን እንኳን ቢሆኑ በኢስላም ውስጥ የምህረት በር በየትኛው ጊዜና ቦታ እንዲሁም ሁኔታ ክፍት ነው፡፡ አላህ (ሰ.ወ) ይላል፡፡

**"ጸጸትን መቀበል በአላህ ላይ የሚገባው ለእነዚያ ኀጢአትን በስህተት ለሚሠሩና ከዚያም ከቅርብ ጊዜ ለሚጸጸቱት ብቻ ነው፡፡ እነዚያንም አላህ በእነርሱ ላይ ጸጸትን ይቀበላል፡፡ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው፡፡ ጸጸትንም መቀበል ለእነዚያ ኀጢአቶችን ለሚሠሩ አንዳቸውንም ሞት በመጣበት ጊዜ «እኔ አሁን ተጸጸትኩ» ለሚልና ለነዚያም እነርሱ ከሓዲዎች ኾነው ለሚሞቱ አይደለችም፡፡ እነዚያ ለእነሱ አሳማሚን ቅጣት አዘጋጅተናል፡፡"**

የአላህ መልእክተኛም እንዲህ ይላሉ፡ "አንድ ሰው በሞት አፋፍ ላይ እስካልሆነ ድረስ አላህ የባሮቹን ንስሃ ይቀበላል፡፡ በኢስላም ውስጥ በየትኛውም ሁኔታ ከአላህ እዝነትና ምህረት ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር የለም፡፡ ቁርዓን ከአላህ ተስፋ መቁረጥ የካሃዲያኖች ተግባር መሆኑን ይገልፃል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡

"ከአላህ ምህረት ተስፋ የሚቆርጡ ሰዎች እነሱ እነዚያ ካሃዲዮች ናቸው፡፡" ሰዎች ወደ ፈጣሪቸያቸው ንስሃ ከገቡ በአላህ ችሮታ ምህረት የማግኘታቸው ጉዳይ እርግጥ ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዳብራሩት "ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታዬ እምላለሁ ወንጀል የማትፈፅሙ ፍጥረታት ብትሆኑ ኖሮ አላህ እናንተን አስወግዶ ልሎች ወንጀል የሚሰሩ ሰዎችን ከሰሩም በኋላ ምህረትን የሚለምኑና እሱም ምህረት የሚያደርግላቸው ሰዎቸን ይፈጥር ነበር፡፡"

ሰዎች ከወንጀላቸው ወደ አላህ ንስሃ መግባታቸውና መመለሳቸው በአላህ ዘንድ ምህረት መለገስ ብቻ ሳይሆን የአላህንም ውዴታ ጭምር ያጎናፅፋል፡፡ ይህም በመሆኑ ምክንያት በወንጀል ውስጥ ጠልቀው ለሚኖሩ ሰዎች ንስሃ በማድረግ እንዲቻኮሉ ያደርጋቸዋል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡፡ "አንድ ሰው ጭው ባለ በረሃ ላይ ምግቡን መጠጡን እንዲሁም ለጉዞ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶቹን የተሸከመች ግመሉ ተኝቶ ሲነሳ ተሰወረችበት፡፡ ማፈላለግም ጀመረ ነገር ግን ለከፋ ረሃብና የውሃ ጥም ከመዳረግ ውጪ ምንም አላተረፈም፡፡ ከመሞት ውጪ ሌላ አማራጭ እስከማይኖረው ድረስ ተስፋ በመቁረጥ መጀመሪያ ወደ ነበረበት ቦታ ተመልሶ በመሄድም ተኛ ፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለ ከእንቅልፉ ሲነቃ ስንቅቁን፤ ምግብና መጠጡን የተሸከመችው ግመል

አጠገቡ ቆማ አገኛት፡፡ “አላህ በባሮቹ ከወንጀላቸው ተፀፅተው ሲመለሱ በጣም ይደሰታል ይህ ሰው ግመሉን አጠገቡ ቆማ ሲያገኛት ከሚደሰተው በላይ”

ይሄን መፅሃፍ ስታነብ ኢስላም በየትኛው የህይወት ዘርፍ በግለሰባዊም ሆነ በማህበራዊ ፣ ሃይማኖታዊ ሆኑ አለማዊ ህይወት ውስጥ ምን ያህል ከሰው ልጆች ተፈጥሮ ጋር ተስማሚ ገር እና ምቹ የህይወት መንገድ መሆኑን ትገነዘባለህ፡፡

ካለህ ጊዜ ውስጥ የተወሰነውን የኢስላምን አስተምህሮት ለመማር መድብ፡፡አንዳንድ እውቀት የሌላቸውና የተሞኙ ሙስሊሞች የሚከተሉትን መንገድ በመመልከት አንተም የነሱን ፈለግ አትከተል፡፡

ትክክለኛ የሰው ልጅን ተፈጥሮ እና አስተሳሰብ የሚቃረን ነገር ከኢስላም ያለመሆኑን እወቅ፡፡ሰዎች ደስታን የሚያጎናፅፋቸውን ሃይማኖት ለማግኘት ግራና ቀኛቸውን ይመለከታሉ፡፡ትክክለኛ አስተሳሰባቸውና ተፈጥሮአቸው ወደዚህ ቅን ጎዳና ይጎትታቸዋል ግን ልባቸው እምቢ ትላቸዋለች፡፡ ሰይጣን የሰው ልጅን ለማሳሳትና ለማጥመም የሚሸርበው ሴራ ነው፡፡ሰይጣን ሁሌም ሰዎችን ይህን ትክክለኛ ቅን ጎዳና -ኢስላምን- በመከተላቸው ሊያገኙት የሚችሉትን የሁለት ዓለም ደስታንና ተድላን እንዳይጎናፀፉ ይጋርዳቸዋል ያሞኛቸዋል፡፡ ከጀነት በተባረረም ጊዜ እንዲህ ብሎ ነበር የዛተው፡-

“እርሱም) አለ «በአሸናፊነትህ ይኹንብኝ፤ በመላ አሳስታቸዋለሁ፡፡ ከእነርሱ ምርጥ የኾኑት ባሮችህ ብቻ ሲቀሩ፡፡” ሱረቱ ሳድ-82

የኢስላም ሃይማኖት ተከታይ መሆን አላህ ከባሮቹ ለፈለገው ሰው የሚሰጥ ትልቅ ፀጋ ነው፡፡ እውነትን ለማወቅ ከልብ የመነጨ እውነተኛ ፍላጎት ያለው ሰው አላህ ቅኑን መንገድ እንዲያገኝ ቀላል ያደርግለታል ፡፡ለንደዚህ ዓይነት ነገር ከታደሉ ሰዎች ውስጥ ትሆን ዘንድ አላህን ከጅል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡

በመስለማቸው በአንተ ላይ ይመጻደቃሉ «በስልምናችሁ በኔ ላይ አትመጻደቁ፤ ይልቁንም አላህ ወደ እምነት ስለ መራችሁ ይመጻደቅባችኋል፤ እውነተኞች ብትኾኑ» (መመጻደቅ ለአላህ ነው) በላቸው፡፡

ዶ/ር አብዱረህማን ኢብኑ አብዱልከሪም ሸይሃ

## መግቢያ

ከአዳም ጊዜ አንስቶ ምድርንና በምድር ላይ ያሉትን ፍጥረታት እስከሚወርሳቸው ጊዜ ድረስ ላሉት ነብያት ኢስላም የነብቶች ሁሉ ሃይማኖት እንዲሆን አላህ አድርጎታል፡፡ ይህንኑ ሃይማኖት ለሰው ልጆችና ጂኖች የሕይወት መንገድ ይሆን ዘንድ ወደደ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ይላል፡-

"አላህ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሃይማኖት  ኢስላም ነው፡፡"

ኢስላም የሰው ልጆች አጋር የሌለውን አላህ በብቸኝነት እንዲያመልኩና የሚሰሩትን ስራ ሁሉ የሱን ፍቅርና ውዴታ ብቻ  በመከጀል እንዲሰሩ ጥሪ በማስተላለፍ ነበር የጀመረው፡፡ ይህም ጥሪ የሁሉም ነብያትና መልእክተኞች አስተምህሮት ነበር፡፡ አላህ (ወ.ሰ) ይላል፡፡

"ከዚህ በፊት ለኖህ ለሙሴ ለኢሳ የደነገግነው የህይወት መንገድ ለናንተም ደነገገ…."

ከነብዩ መሃመድ (ሰ.ወ) በፊት ነቢያት ለተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እና ዘመን ነበር የሚላኩት፡ ፡አንደኛው ነብይ አልፎ ሌላኛው እስኪተካ ድረስ ያለው ጊዜ በመርዘሙ ምክንያት ሰዎች ነብያቶች ካስተማሩት አስተምህሮት መንገድ ውጪ ሲሆኑ፣ ከአላህ ውጪ ሌሎችን ማምለክ ሲጀምሩ፣ በምድር ላይ ግፍና በደል ሲነግስና ሲስፋፋ አላህ ቀደም ብሎ የነበረውን መጥፎ ሁኔታ ተሃድሶ የሚያመጣ ሌላ ነብይ ይልካል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡

"ለእያንዳንዱ ህዝብ ሰዎች አላህን እንዲገዙና ከጣኦት እንዲርቁ ያስተምሩ ዘንድ መልእክተኞችን ልከናል፡፡" ሙሃመድን (ሰ.ዐ) የመጨረሻውና   የነብያቶችና መልዕክተኞች መደምደምያ አድርጎ ላካቸው፡፡ ፡ይህ ሙሃመድን (ሰ.ዐ)  ይዘውት የመጡት መንገድ የመጨረሻና ለሰው ዘር ሁሉ ለጥቁሩም፤ ለነጩም፤ ለአረቡም፤ አረብ ላልሆነውም ያለምንም ልዩነት አብሳሪና አስጠንቃቂ እንዲሆን የተሰጠ የሕይወት መመሪያ  እንዲሆን አድርጎታል፡፡

አላህ እንዲህ ይላል፡-  "እኛ ለሰው ልጆች ሁሉ አብሳሪና አስጠንቃቂ ትሆን ዘንድ ላክንህ፡፡" የነብዩ መሃመድ አስተምህሮት ከሱበፊት ከነበሩት ነብያት በተለየ መልኩ ለሁሉም ዘመን፤ ለሁሉም ቦታ እና ሁሉንም የሰው ዘር በአላህ የተመረጠ የህይወት መንገድ በመሆኑ ምክንያት ቀድሞ የነበሩ ነብያት ይዘው ከመጡት መንገድ ለየት ያሉ ልዩ መገለጫዋ ሊኖሩት የግድ ይለዋል፡፡እነዚህም ልዩ መገለጫዎችም ውስጥ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የህይወት ልምድና ተሞክሮ ከግምት የሚያስገባ፤ያለምንም ዘርና ቀለም ልዩነት ከአጥናፍ አጥናፍ  ለሰው ልጆች ሁሉ ምቹና ተስማሚ እንዲሆን ለሰዎች የእዝነት መንገድ ሊሆን ይገባዋል፡አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡ "አንተን ለአለማት እዝነት አድርገን ላክንህ"፡፡

ይህም የመጨረሻው የሕይወት መንገድ ሙሉ እና ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የግለሰብ እና የቡድን ህይወትን እንዲሁም በዙሪያው የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን የእርስ በርስ ግንኙነት የሚዳስና የሚመራ መሆን ይኖርበታል፡፡አላህ ይናገራል፦

ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡

አንድ እምነት ከሰው ልጆች ተፈጥሮ ጋር ያለው ተስማሚነት ፣ምቹነት፣ ገራገርነት ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት እዲኖረው ከሚያስችሉት ዋና ዋና ምክንያቶች ከሆኑ የእስልምና የእምነት መሰረቶች፣ የአምልኮ ስነስርዓቶቹ፣ህግና ደንቦቹ ከየትኛውም ሃይማኖት በተለየ መልኩ ከሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ማንነት ላይ የተገነቡ ናቸው፡፡የኢስላም ሃይማኖታዊ ስርዓቶችን በተግባር ለማዋል የማንንም ሰው የተለየ አቅምና ብቃት እንዲሁም ተሰጥኦ የማይፈልጉ በመሆናቸው በየትኛው ቦታ እና ጊዜ ለሚገኝ የሰው ዘር የኢስላምን እምነት ለመቀበልም ሆነ የእምነት ስርዓቱን ተግባራዊ ለማድረግ ቀላልና ምቹ እንዲሆን አድርጎታል ነው፡፡ይህ ባህሪ ለሰው ልጅ ተፈጥሮ ምቹ እና ቀላል መሆኑ ኢስላም የተገነባበት የመሰረት ድንጋይ እና ዋና መገለጫው ነው ፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እንደሚለው ፡-

*"አላህ ነፍስን ከምትችለው በላይ አያስገድድም"*

የአላህ መልዕክተኛ ይላሉ፡- "እኔ የተውኩላችሁ መንገድ ብቻ ተከተሉ ከናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦች የጠፉት በነብያቸው ላይ ያላስፈላጊ ጥያቄ በማንሳታቸውና እነሱን በመቃረናቸው ነው፡፡ አንድን ነገር እንዳትሰሩት ከከለከልኳችሁ ሙሉ ለሙሉ ተከልከሉ፡፡እንድትፈጽሙት ያዘዝኳችሁ ነገር አቅማችሁ በፈቀደ ልክ ፈጽሙ፡፡"

ኢስላም ለሰው ልጆች ምቹ እና ገር ባህሪው የእምነቱ መሰረት የተገነባበት መርህ ነው፡፡ ይህም የሃይማኖቱ ዋነኛ ክፍል ከሆነው የእምነቱ መርሆች -አቂዳ - አንስቶ እስከ ጥቃቅን የሃይማኖቱ ክፍሎች ያለማክረርና ፅንፈኛ ያለመሆን የእምነቱ መገለጫዎቹ ናቸው፡፡ ሃላል የሆኑትን ነገሮች ክልክል ወይም ሃራም እንዲሁም ክልክል የተደረጉ ነገሮችን ደግሞ ሃላል ወይም የተፈቀደ አያደርግም፡፡ የኢስላም ህግጋት ሰውን ከአቅሙ በላይና ከተፈጥሮው ውጭ የሆነን ነገር በማሸከም ለችግር ለጭንቀትና መከራ የሚዳርግ ሳይሆን ድክመቱንና ጎዶሎ ጎኑ ለመሙላትና ለማከም የመጣ ስርዓት ነው፡፡የሰዎችን ተፈጥሮአዊ ማንነት፣ ስሜታዊነትና፤ እና የአቅም ውስንነትን በመቃረን ሳይሆን ሰዎች አቅማቸው በፈቀደው ልክ ተግባራዊ ሊያደርጓቸው የሚችሉትን ነገሮች መሰረት ያደረጉ የህይወት መመሪያዎች የተገነባ ሃይማኖት ነው፡፡አላህም ይላል፡

"አላህ በዚህ ሃይማኖት ውስጥ የሰው ልጆችን ለመከራና ችግር የሚዳርግ ነገር አላደረገም፡፡"

የኢስላም ህግጋት ቀላልና ምቹ በመሆናቸው ፣የሰው ልጅ ለጉዳትና ለችግር የሚዳርጉ ነገሮችን በማስወገድ ዙሪያ ላይ ያጠነጠኑ በመሆናቸው ላቅ ወዳለ ስፍራ እንዲደርስ ያለሙና በየትኛውም ህብረተሰብ ውስጥ ለሚገኝ ሰው እድሜና የአመለካከት ልዩነት ሳይገድበው ሃይማኖቱ በተከታዮቹ ልብ ውስጥ ተወዳጅ እና በተግባር ሲኖሩትም መንፈሳቸው የሚረካበትና የሚታደስበት ህይወታቸው የሚሰምርበት አድርጎታል፡፡

ለዚህም የኢስላም ልዩ መገለጫ ብዙዎች ሙስሊም ያልሆኑ ሙሁራን እንዲህ በማለት የምስክር ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ “ የኢስላም ህግጋት ድሆችን እንደሚንከባከበውና እንደሚያበረታታ ሁሉ ሃብታሞችንም አይዘነጋም፡፡ በሽተኞችን በሚያይበት መነፅር ጤነኞችንም ይመለከታል፡፡ ህጻናትን እንደሚንከባከበው ሁሉ የእድሜ ባለፀጋዎችንም ይንከባከባል፡፡ ለሴቶች በሚሰጠው አትኩሮትና ክብር ያህል ወንዶችንም የማይዘነጋ ነው፡፡ የተማሩ ሰዎችን እንደሚንከባከበው ሁሉ መሃይሞችንም አይዘነጋም፡፡መሪዎችን እንደሚከታተለው ሁሉ ተራውን ህዝብንም እንደዚሁ፤ የእስልምና ህግ የጊዜንና የቦታን አመቺነት ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡የአለማችን ህዝቦች በቁጥርም ሆነ በዓይነት በብዙ ነገሮች ከመለያየታቸው ጋር ተያይዞ የህይወት መርሆዎቹ ለሰው ልጅ ሁሉ ሚዛናዊ ተስማሚ እና ምቹ እንዲሁም የሰው ልጅን ተፈጥሮአዊ ድክመቶች ባገናዘበ መልኩ የተገነባ የህይወት መንገድ እንደ ኢስላም ሃይማኖት አለማችን እስካሁን ድረስ አላስተናገደችም፡፡”አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡

“አላህ ለናንተ ማቅለልና ይፈልጋል ሰው ደካማ ሆኖ ነው የተፈጠረውና”

የኢስላም ሃይማኖት ችግርንና መከራን ከማስወገድ አንፃር ያለው የእምነቱ ምቹነትና ገርነት ለተከታዩቹ ብቻ የተገደበ ሳይሆን የአላህ መልዕክተኛ በሆኑት መሃመድ (ሰ.ዐ) ግልፅ በተደረገው ኢስላም ምክንያት ከሱ በፊት የነበሩትን ድንጋጌዎች እንዲቀሉ ተደርጓል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡

“(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው፡- «እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ፡ ፡ (እርሱም) ያ የሰማያትና የምድር ንግሥና ለእርሱ ብቻ የኾነ ነው፡፡ እርሱ እንጂ ሌላ አምላክ የለም፡፡ ሕያው ያደርጋል፡፡ ይገድላልም፡፡ በአላህ በዚያም በአላህና በቃላቶቹ በሚያምነው የማይጽፍ የማያነብ ነቢይ በኾነው መልክተኛው እመኑ፡፡ ቅንንም መንገድ ትመሩ ዘንድ ተከተሉት፡፡» አእራፍ 158

መለኮታዊ ከሆኑ ህግና ደንቦች በተጨማሪ ኢስላም ለሰው ልጆች ልምድና ተሞክሮ ከፍተኛ ቦታ መስጠቱ ሃይማኖቱ ለሰው ልጆች ምቾትና ተግባራዊነት ማሳያ ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ሙዓዝ ኢብኑ ጀበልን ወደ የመን በላኩት ጊዜ የተናገሩት ንግግር ይህንን እውነታ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ እንዲህ በማለት “ሰዎች ዘንድ እንድትፈርድ ብትጠየቅ እንዴት አድርገህ ነው የምትዳኛቸው” ብለው የአላህ መልዕክተኛ በጠየቁት ጊዜ እሱም “በአላህ መፅሃፍ እፈርዳለሁ” አለ “ መረጃውን

ከአላህ መፃህፍ ባታገኘስ" ብለው ጠየቁት "በአላህ መልእክተኛ ሱና" አላቸው ከሱስ ባታገኝ አሉት እሱም "የግል ልምድና ተሞክሮዬን በመጠቀም እፈርዳለሁ" አለ፡፡ የአላህ መልዕክተኛም ሙአዝን ደረቱን መታ መታ በማድረግ እንዲህ አሉ፡፡ "ለዚያ የአላህ መልዕክተኛ (ሙሃመድ) የሚወደውን ነገር የአላህ መልክተኛ መልክተኛ የሆነው (ሙዓዝ) እንዲያስብ ላደረገው ጌታዬ ምስጋና ተገባው" በማለት ኢስላም የሰው ልጆችን በሂደት ያከበቱትን የትምህርትና የልምድ ተሞክሮ የሚቀበል ሃይማኖት በመሆኑ ለየትኛውም ጊዜና ቦታ ተስማሚና ከሁኔታዎች መለዋወጥ ጋር አብሮ መጓዝ የሚችል ሃይማኖት መሆኑን ያመለክታል፡፡

ኢስላም ይዟቸው የመጡት ጠቅለል ያሉ የእምነት መርሆዎችና ህግጋት የተገነቡበት መሰረት ሁሉንም የሰው ዘር የሚያጠቃልሉና እስከ ዝንተዓለም ማገልገል የሚችሉ ናቸው፡፡ስለሆነም የእምነቱ ግንድ መርሆችና የአምልኮ ተግባራት ጊዜና ቦታ በተለዋወጡ ቁጥር እነሱም አብረው መቀየርና መለዋወጥ አያስፈልጋቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል የእያንዳንዱ ሰላት ቁጥር የሚሰገድበት ጊዜ፣ ዘካ እና የሚከፈለው መጠን፣ፆም እና የሚጾምበት ወቅት፣ ሃጅ የሚደረግበት ወቅት እና አጠቃላይ የአደራረግ ስርዓቱ እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ የእምነቱ ክፍሎች ስንመለከት በየትኛው ቦታና ዘመን ለሚኖር የእምነቱ ተከታይ ሁሌም አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ ናቸው፡፡

ዘመን አመጣሽ አዲስ የሆኑ ጉዳዮች በሚመጡ ጊዜ አዲሱ ክስተት ቁርአንና ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ሱንና ውስጥ ይፈተሻል፡፡በቁርአንና በሱንና ውስጥ ከተገኘ በቁርአንና በሱንና ሚዛን ታይቶ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡በቁርአንና በሱንና ውስጥ ካልተገኘ ብቃትና የአላህ ፍራቻ ያላቸው የኢስላም ሊቃውንቶች በጉዳዩ ላይ ጥናትና ምርምር እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡መሰረታዊ መፍትሄ የሚሆን የዘመኑን የህብረተሰብ ችግር ያገናዘበ እና መፍትሄ የሚጠቁም ስራ ይሰራሉ፡፡የነዚህ ታላላቅ ኡለሞች መነሻ ቁርአንና ሱንናን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ከቁርአንና ሱንና የመነጩ ወሳኝ መሰረቶችን የሸሪአ መሰረተ ሃሳቦችን ታሳቢ ያደረገ ይሆናል፡፡ለምሳሌ (ነገሮች በመሰረቱ የተፈቀዱ ናቸው፡፡) ፤(ውድ እና በጣም አስፈላጊ ነገሮችን ማስጠበቅ፡፡)፤(አዋኪ ነገሮችን ማራቅና ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፡፡)፤(ጉዳትን ማስቀረት፡፡) ፤ (ከአቅም በላይ የሆኑ ነገሮች በሚከሰቱ ጊዜ የተከለከሉ ነገሮች ይፈቀዳሉ፡፡)፤(ዋና ዋና ነገሮች በየደረጃቸው ይቀመጣሉ፡፡)፤ (ጉዳትን መመከት ጥቅምን ከማሳደድ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡) ፤ (ከአንድ በላይ ምርጫ የሌላቸው ሁለት ጎጂ ነገሮች ቢከሰቱ ቀለል ያለው ጎጂ ይመረጣል፡፡) ፤ (ጎጂ ነገር በሌላ ጎጂ አይለወጥም፡፡) ፤ (የብዙሃንን ጥቅም ከግለሰብ /ከነጠላ ጥቅም እናስቀድማለን፡፡) ፤ ከዚህም ሌላ ያሉ ተመሳሳይ የሸሪአ መሰረተ ሃሳቦችን ያማከለ ጥናትና ምርምር በሸሪኣ ሊቃውንት ይካሄዳል፡፡

ኢጅቲሀድ ይደረጋል ሲባል በስሜት መነዳት ፍላጎትን ማስተናገጃ ቀዳዳ መፈለግ ማለት አይደለም፡፡ኢጅቲሃድ ማለት ለሰው ልጅ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን ማፍለቅ ነው፡፡ከሸሪአ ድንጋጌ ጋር የሚሄዱ የማይጣረሱ ጠቃሚ ውጤቶችን ማምጣት ነው፡፡ይህም የኢስላም ብቸኛ መለያ የሆነውን ከዘመን ዘመን የመሻገር ተልዕኮ እውን ማድረጊያ ብቸዓ መንገድ ኢጅቲሀድ ነው፡፡ይህ ንግግር ግብታዊ አይደለም የሸሪአን ምንጮች ቁርአንን እና ሱንናን የተከታተለ ሰው የኢስላምን ምቹነት እና ዘላለማዊነት ይረዳል፡፡

# ኢስላም- የሰው ልጅ ምቹ የህይወት መንገድ

ስለ ኢስላም ሃይማኖት ለሰው ልጆች ምቹና ገር የመሆን ባህሪው ስንናገር ይሄ ባህሪው የሃይማኖቱ ቅርንጫፍ በሆኑ ጉዳዮች ብቻ የታጠረ ሳይሆን አጠቃላይ ኢስላም በሚያጠቃልላቸው ጉዳዮች ሁሉ የተገነባበት ዋና ግንድ ባህሪ ነው። የአላህ መልክተኛ ይሄን በማስመልከት እንዲህ ይላሉ "ከሃይማኖታችሁ በጣም ተወዳጁ ለሰዎች በጣም ገርና ምቹ የሆነው ነው።" በመልዕክተኛው አንደበት እንዲህ የተነገረለት ሃይማኖት እንዴትስ የእምነቱ መሰረት ገራገርና ምቹነት የቅርንጫፍ ጉዳዮች ሳይሆን የእምነቱ ዋና መሰረት መሆን ይሳነዋል።

በሌላ ንግግራቸው (ሰ.ዐ.ወ) " አላህ ዘንድ በጣም ተወዳጅ የሆነው የሃይማኖታችሁ መንገድ በጣም ቀጥ ያለውና ለሰዎች ቀላልና ምቹ የሆነው ነው።" ቡካሪ እንደዘገቡት

ኢስላም ለሰው ልጆች የአብሮነት የመቻቻልና ምቹ የሆነ የህይወት መንገድ ነው። ሚዛናዊ የህይወት መንገድ። አላህም እንዲህ ሲል ገለፀው፡-

"እንደዚሁም (እንደመራናችሁ) በሰዎች ላይ መስካሪዎች ልትሆኑና መልክተኛውም በናንተ ላይ መስካሪ ይሆን ዘንድ ምርጥ ሕዝቦች አደረግናችሁ፡፡" በቀራህ 143

በፖለቲካውም ሆነ በውጭ ግንኙነት ዘርፍ ኢስላም ለሰው ልጆች ምቹ እና ገር ሃይማኖት ነው። አላህ ይናገራል "እነዚያ በሃይማኖታችሁ ምክንያት የተዋጓችሁና ከአገር የማያስወጣችሁ ለነሱ መልካም እና ፍትሃዊ ትሆኑ አንድ አይከለክለችሁም አላህም ፍትሃዊዎችን ይወዳልና።

"ከእነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካላወጡዋችሁ (ከሓዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደእነርሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም፡፡ አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና፡፡" አልሙምተሂናህ 8

ኢስላም በሰው ልጆች መካከል ያለውን ትስስር እኩልነትን መሰረት ያደረገ ሃይማኖት ነው። አላህ ይላል፡ "እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፡፡ እንድትተዋወቁም ነሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፡፡ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡ አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው፡፡

" እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፡፡ እንድትተዋወቁም ነሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፡፡ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡ አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው፡፡" ሁጁራት 13

ኢስላም እጹብ ድንቅ የሆኑ የስነምግባር መርሆዎች ባለቤት ነው። አላህ እንዲህ ይላል

"ገርን ጠባይ ያዝ፡፡ በመልካምም እዘዝ፡፡ ባለጌዎቹንም ተዋቸው፡፡" አል-አእራፍ 199

“እነዚያን በደስታም ሆነ በችግር ጊዜ የሚመፀውቱ፣ቁጣቸውንም ዋጥ የሚያደርጉ ከሰዎችም ይቅርታ የሚያደርጉ አላህ መልካም ሰሪዎችን ይወዳል።” በሌላኛው የቁርዓን አንቀፅ አላህ እንዲህ ይላል።“ለመጥፎ ነገር ከሷ በላጭ በሆነ መልካም ተግባር መልስ በዚህ ምክንያት በአንተና በሱ መሃከል የተፈጠረውን ጠላትነት ወደ ቅርብ ጓደኝነት ይቀየራል።”

የኢስላም በአምልኮአዊ ተግባራትም ቢሆኑ በሰው ልጆች አቅምና ችሎታ መፈፀም የሚችሉ ናቸው። አላህ እንዲህ ይላል፡

እነዚያም ያመኑና መልካሞችን የሠሩ ነፍስን ችሎታዋን እንጂ አናስገድድምና፤ እነዚያ የገነት ሰዎች ናቸው፡ ፡ እነርሱ በርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው፡፡” አእራፍ 42

ኢስላም በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ዙርያ ያስቀመጣቸው መርሆች ለሰው ልጅ ምቹ እና ተስማሚ ናቸው። አላህ ይናገራል።

“እነዚያ አራጣን የሚበሉ ሰዎች እነዚያ ሰይጣን እንተጠናወተው ሰው ቀጥ ብለው አይቆሙም። እንዲህ የሆኑትም ንግድ እንደ አራጣ ነው ማለታቸው ነው። አላህ ንግድን ሲፈቅድ አራጣን እርም አደረገ….”

በማህበራዊ ግንኙትም ኢስላም ለስላሳ የህይወት እና የአኗኗር ዘይቤ የሚከተል ሃይማኖት ነው፡ ፡ አላህ ይናገራል፡-

“ለባሮቼም በላቸው፡- ያችን እርሷ መልካም የኾነችውን (ቃል) ይናገሩ፡፡ ሰይጣን በመካከላቸው ያበላሻልና፡፡ ሰይጣን ለሰው ግልጽ ጠላት ነውና።”አል ኢስራ 53

በትምህርት ስልጠና የሚከተለውም መንገድ እንደዚሁ ነው የአላህ መልዕክተኛ ይላሉ

“አግራሩ እንጂ አታከባብዱ አበስሩ እንጂ ሰው እንዲረቅ አታድርጉ” ኢብኑልሂባን

ኢስላማዊ የህግ ድንጋጌዎች ግለሰቦች በሚኖሩበት ህብረተሰብ ውስጥ ህይወትን የማቅለልና አንዱ ለሌላው የመተሳሰብና የመተዛዘን ባህልና ልምድ እንዲያዳብሩና እንዲያብብ እንዲህ በማለት ያበረታታል፡- “ እዝነት አንድ ሰው ስብእና ውስጥ አይኖርም ሰውየውን ከፍ ቢያደርገው እንጂ። እንዲሁም ከሰው ስብዕና ውስጥ አይወገድም ሰውየውን ዝቅ ቢደርገው እንጂ” ሙስሊም እንደዘገቡት

የአላህ መልእክተኛ በሌላ ንግግራቸው ፡-

“ለሰዎች ምቹ ሁን አላህ ላንተ እንደዚያው ይሆንልሃል”

“አላህ በሁሉም ነገር ገራገርና አዛኝ መሆንን ይወዳል”

በተመሳሳይ መልኩ በህብረተሰብ ደረጃም ለህዝብ ገራገርና ምቹ ለሚሆኑ ሰዎችና የህዝብ መሪዎች የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ በማለት ፀሎት አድርገውላቸዋል።

“ጌታዬ ሆይ በህዝቦቼ ጉዳይ ላይ በአመራርነት ተሹሞ ለጭንቀት የሚዳርጋቸው ሰው እሱንም ለጭንቀት ዳርገው፡፡ በህዝቦቼ ጉዳ ላይ ተሹሞ እዝነት በተሞለው መንገድ ያስተዳደራቸው ሰው ለሱም እዘንለት፡፡” ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

ገራገርነትንም የጀነት መግቢያና ከጀሃነም እሳት የመጠበቂያ መንገድ አድርጎታል፡፡ የአላህ መልእክተ ይሄን በማስመልከት እንዲህ ብለዋል “ገራገር ፣ለስላሳና ተግባቢ በሆነ ሰው ላይ አላህ እሳትን እርም አድርጎበታል፡፡” ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

ነገር ግን አንድ መታወቅ የሚገባው ነገር ኢስላም ለሰዎች ቀላልና ምቹ ሃማኖት ነው ስንል በተለይ አምልኮአዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሃይማኖቱን አስምህሮት፣ደንብና ስርዓትን ቸልተኛና ዝንጉ ወይም መተላለፍ ማለት አይደለም፡፡ ኢስላም ገራገር ነው ስንል የተከለከሉ ነገሮችን መፍቀድ ወይንም የተፈቀዱ ነገሮችን ክልክል ማድረግ ማለት አይደለም፡፡ኢስላም የደነገጋቸው ህግጋቶችና ትእዛዞች ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ጽንፈኛ መሆን ማለት አይደለም፡፡ እንዲሁም በኢስላማዊ መርሆችና የስነምግባር ደንቦች ተግባራዊ በማድረግ ላይ ደካማ መሆን ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ኢስላም ገራገርና እና ለሰዎች ምቹ የሆነ ሃይማኖት ነው ስንል ከፅንፈኝነትና ሰዎችን ለችግር ከመዳረግ ወንጀልን ከመዳፈር የራቀ ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ባለቤት የሆነችው እናታችን አኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡

“የአላህ መልእክተኛ በሁለት ነገሮች ምርጫ ከቀረበላቸው ከሁለቱ በጣም ቀላሉን እንጂ ሌላን አይመርጡም በወንጀል እስካልሆነ ድረስ በወንጀል ነክ በሆኑ ጉዳዮች ግን ከሰዎች ሁሉ በላይ የሚርቁ ነበሩ፡፡”

ወንጀል ነክ የሆኑ ጉዳዮችም ቢሆኑ እንኳን ሰዎችን ለከፍተኛ ጉዳት የሚዳርጉ ነገሮች ከሆኑ በተለየ መልኩ የሚፈቀድበት ደንብና ህግ አለው፡፡

የኢስላም ምቹነትና ገራገርነት ጠቅላላ ገፅታው ከላይ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ በመቀጠልም ይህ የኢስላም ባህሪ በንዑስ ክፍሎች በመከፋፈል በጥልቀት ምን ዓይነት ገጽታ እንዳላቸው በዝርዝር አንቃኛለን፡፡

## ኢስላም የተገነባበት የእምነት መርሆዎች ለመረዳት ቀላል መሆናቸው

የእስልምና የእምነት መርሆች (አቂዳ) እምነቱ የተገነባባቸው የመሰረት ድንጋይ ናቸው፡፡ያለ እነዚህ መርሆዎች የእስልምና ሃይማኖት አይኖርም፡፡ጌታችን አላህ ይሄን በማስመልከት እንዲህ በማለት ተናግሯል፡፡

“አላህ በሱ ላይ ባላንጣ የሚያደርጉትን አይምርም ከዚያ ውጪ የሆነ ማንኛውንም ነገር ምህረት ይሰጣል፡፡”

የኢስላም የእምነት የተገነባባቸው መርሆዎች ለግንዛቤ ካላቸው ቀላልነት አንፃር እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

1. የኢስላም የእምነት መርሆዎች ግልፅና ውስብስ ያልሆኑና ለመረዳትም የማያስቸግሩ ናቸው፡፡ ያልተማረው ሰው ከተማረው ቀድሞ ፤ ህፃነትም ከአዛውንት በፊት በቀላሉ መረዳት የሚችሉት ነው፡፡ ይኸውም በአንድ አላህ ያለምንም ባላንጣ ማመንና ለሱም መገዛት ነው፡፡ ይህ የእምነት በርህ ደግሞ ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል በቀላሉ ሊረዳው የሚችል ነው፡፡ ይህን ለመረዳት የተለየ የሙያና የተሰጥኦ ባለቤት መሆንን አይጠይቅም፡፡ይህን የኢስላም የእምነት በርህ ለመረዳት ከሰው ልጅ አእምሮ የማሰብ አቅም በላይ አይደለም፡፡ የኢስላም የእምነት መርሆዎች የሰውን ልጅ ድንጋይና ዛፍ እንዲሁም እንስሳትን እንዲገዛ በማድረግ አእምሮ ከተሰጠው አቅም በታች ዝቅ የሚያደርግና ክብሩንም የሚያዋርድ የእምነት መርህ የያዘ አይደለም፡፡ የኢስላም የእምነት መርሆችን ለመረዳት ምን ያህል ቀላልና ገር መሆናቸውን ለማሳየት አንድ በርሃ ውስጥ የሚኖር መሃይም ዘላን እንዴት ፈጣሪ መኖሩን ለማወቅ እንደቻለ በተጠየቀበት ወቅት የሰጠውን መልስ መመልከት ብቻ በቂ ነው፡፡ እንዲህም አለ “የግመል ፋንድያ አስቀድሞ የተመለከተ ሰው ለዚህ ምክንያት የሆነውን ግመል መኖሩን ይመሰክራል፡፡የእግር አሻራ የተመለከተ ሰው በአካባቢው መንገደኞች ማለፋቸውን ያረጋግጣል፡ እንዲህ ከሆነ ዘንዳ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ በከዋክብት የተጌጠና ያሸበረቀ ሰማይ መመልከት እዝነቱ ወደር የሌለውና ሁሉንም አዋቂ የሆነ አላህ መኖሩን አያመላክቱምን!!” በማለት በሚስገርም መልኩ ነበር የመለሰው፡፡
2. የኢስላም የእምነት መርሆች በሁሉም ቀደምት የአላህ መልዕክተኞች ከፈጣሪ ስለመላካቸው እና መፅሀፍም እንደተወረደላቸው ተከታዮቹን እንዲያምኑ ይደነግጋል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡

“ መልክተኛው ከጌታው ወደ ርሱ በተወረደው አመነ፡፡ ምእምኖቹም (እንደዚሁ)፡፡ ሁሉም በአላህ፣ በመላዕክቱም፣ በመጻሕፍቱም፣ በመልክተኞቹም ከመልክተኞቹ «በአንድም መካከል አንለይም» (የሚሉ

ሲኾኑ) አመኑ፡፡ «ሰማን፤ ታዘዝንም፡፡ ጌታችን ሆይ! ምሕረትህን (እንሻለን)፡፡ መመለሻም ወዳንተ ብቻ ነው» አሉም፡: በቀራህ 285

3. ኢስላም ሰዎችን ያለመልካም ፈቅዳቸውና ፍላጎታቸው እምነቱን እንዲቀበሉ የማያስገድድ ሃይማኖት ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል "በእምነት ማስገደድ የለም…" በቀራህ በበሰዎች ዘንድ የእምነት ልዩነት መኖሩ አሰቀድሞ አላህ የሻው ነገር በመሆኑ አንድም ሰው ሰዎችን ሙስሊም እንዲሆኑ የማስገደድ መብትና ስልጣን የለውም፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡

"ጌታህም በሻ ኖሮ በምድር ያሉት ሰዎች ሁሉም የተሰበሰቡ ሆነው ባመኑ ነበር፡፡ ታዲያ አንተ ሰዎችን አማኞች እንዲኾኑ ታስገድዳለህን፡፡" ዩኑስ 99

የኢስላም ጥሪ ግልጽ በሆነ መንገድ የደረሰው ሰው የመቀበል ወይም ያለመቀበል መብት የራሱ ነው፡፡የፈለገውን እምነት የመምረጥ ነፃነት አለው፡፡አላህ እንዲህ ይላል፡

«እውነቱም ከጌታችሁ ነው፡፡ የሻም ሰው ይመን፤ የሻም ሰው ይካድ» በላቸው፡፡ እኛ ለበደለኞች አጥሯ በእነሱ የከበበ የኾነችውን እሳት አዘጋጅተናል፡፡ (ከጥም) እርዳታንም ቢፈልጉ እንደ ዘይት ዝቃጭ ባለ ፊቶችን በሚጠብስ ውሃ ይረዳሉ፡፡ መጠጡ ከፋ! መደገፊያይቱም ምንኛ አስከፋች! ካህፍ 29

4. በኢስላም አንድ ሰው አማኝ ለመሆኑ ለመመስከር የሰውየውን ውስጣዊ ማንነት ማወቅ ሳያስፈልግ ግልጽና ውጪያዊ የአማኙን ተግባራትና ንግግሮች በመመልከት ብቻ አማኝ ፍርድ ይሰጣል፡፡ ፡፡ በአንድም ሰው ላይ ፍርድ በመስጠት ሂደት ውስጥ ሰውየው በሚያስበው ነገር ላይ መሰረት ተደርጎ ፍርድ አይሰጥም፡፡ ለምን ቢባል የሰው ልጅ ውስጣዊ ማንነት በፈጣሪና በእሱ መሃከል ብቻ ያለ ጉዳይ ስለሆነና ማንም ሆነ ማን እንዲህ ያለውን የሰዎች ውስጠተ-አለም ማወቅ አይቻለውምና፡፡

   ለዚህም የአላህ መልክተኛ የሰዎች ውስጠተ-አለም እና አስተሳሰብ መሰረት በማድረግ ፍርድ ወይም ብይን የሚሰጡ ሰዎችን አበክረው አስጠንቅቀዋል፡፡በአንድ ወቅት እንዲህ አይነት ድርጊት የፈጸመውን ሰው ምነው ይሄን ከመፈጸሜ በፊት ባልሰለምኩ እስከሚል ድረስ የአላህ መልእክተኛ ገስፀውታል፡፡ ኡሳማ ኢብኑ ዘይድ እንዲህ ይላሉ

   "የአላህ መልእክተኛ ለጦርነት ላኩነ በጦርነቱ መሀከል አንድ ሰው ያዝኩኝ፡፡

እሱም ከአላህ በስተቀር የሚገዙት ጌታ የለም ብሎ እየተናገረ ገደልኩት፡፡ የፈጸምኩት ድርጊት ውስጤን መረጋጋት ስላልሰጠኝ ለአላህ መልእክተኛ አወሳሁላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛም "ከአላህ ውጪ የሚገዙት ጌታ የለም ብሎ እየመሰከረ ገደልከውን? አሉኝ፡፡ እኔም "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ይሄን የተናገረው እኮ እንዳልገድለው ፈርቶ ነው"አልኳቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛም "ይህንን አስቦ ለመናገሩ ልቡን ሰንጥቀህ ተመልክተሃልን" አሉት፡፡ ባጠፋሁት ጥፋት በመፀፀት ምነው አሁን ሰልሜ በነበረ ብዬ እስክመኝ ድረስ ወቀሳውን ደጋገሙብኝ፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በሰዎች ላይ ፍርድ የሚሰጠው በግልፅ የሚታዩ ነገሮችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አቢሰኢዲኒል ኹድሪ እንደተናገሩት፡በአንደ ወቅት አልይ አቢ ጣሊብ ከየመን ከወርቅ የተሰራ እቃ ላኩላቸው፡፡የአላህ መልክተኛም ለአራት ሰዎች እነሱም ኡየይነተ ቢንት ሂስን አቅረዕ ኢብኑ ሃቢስ ወዘይዱል ኸይል አረተኛው ወይ አልቀማ ኢብኑ ኡላሰተ ወይ አሚር ኢብኑ ጡፈይል ሲሆኑ እንዲከፋፈሉ ሰጡአቸው፡ከነብ ሰሃቦች አንዱ ይሄ ስጦታ ለኛ ነበር የሚገባው በማለት ተናገረ፡፡የህ ንግግር ነብዩ ዘንድ ደረሰ፡፡ ነብዩም "በሰማይ ባለው ፈጣሪ የታመንኩ ጠዋትና ማታ የሰማይ ዜና የሚመጣልኝ ሰው እናንተ አታምኑኝም እንዴ" ብለው ተናገሩ፡፡

5. ኢስላም አማኞችን አደጋ ላይ ሊጥላቸው የሚችል አስገዳጅ ሁኔታ ሲገጥማቸው ከሚደርስባቸው አደጋ ለማምለጥ ብለው የሃይማኖቱን መርህ የሚቃረኑ ነገሮችን ቢፈፅሙ በይቅርታ ይታለፋሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ይላል፡

ከእምነቱ በኋላ በአላህ የካደ ሰው (ብርቱ ቅጣት አልለው)፡፡ ልቡ በእምነት የረጋ ኾኖ (በክህደት ቃል በመናገር) የተገደደ ሰው ብቻ ሲቀር፡፡ ግን ልባቸውን በክሕደት የከፈቱ ሰዎች በነሱ ላይ ከአላህ ቁጣ አለባቸው፡፡ ለእነሱም ታላቅ ቅጣት አልላቸው፡፡ ነኽል 106

ይህም የሆነው ግለሰቡ ለችግር እንዳይዳረግ ሲባል ነው፡፡ በአንድ ወቅት አማር አብኑ ያስር ሙሽሪኮች ያዙት፡፡ ነብዩን እስኪሰድብና የነሱን ጣኦቶች በመልካም ነገር እስኪያወድስ ድረስ አንለቅም አሉት፡፡ እንዳሉትም ካደረገ በኂላ ለቀቁት፡፡ ወደ አላህ መልዕክተኛ ሲመጣ "በውስጥህ የሆነ ነገር እየተሰማህ ነገር ያለ ይመስላል " አሉት እሱም "መጥፎ ነገር ነው የአላህ መልዕክተኛ" አላቸው፡፡ "ሙሽሪኮች አንተን እንድሰድብና አማልክቶቻቸውን በመልካም ነገር እስከላወሳሁ አንለቅህም አሉኝ፡፡" እንዳሉትም አደረኩ፡፡ነብዩም " ይሄን ስታደርግ ልብህን እንዴት አገኘኸው" አሉት፡፡እሱም "በትክክለኛው እምነቱ ላይ ተረጋግታ" አላቸው፡፡ እሳቸውም "ይህን ከደገሙብህ አንተም ድገምላቸው" በማለት በቅን ጎዳና ላይ እንዳለ አረጋገጡለት፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ተገዶ ለከፍተኛ አካላዊ ቅጣት የሚዳርገው ከሆነም እንደዚሁ ነው፡፡ ልክ ቢላል ኢብኑ ረባህ (ረ.ዐ) ላይ እንደደረሰው፡፡ ከአብዱላህ አብኑ መስዑድ እንዲህ በማለት አስተላልፈዋል፡፡"እስልምናቸውን በህብረተሰባቸው ዘንድ እምነታቸውን በገሃድ ይፋ ያደረጉት ሰዎች ሰባት ናቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ፣አቡበክር፣ኡማር እና እናቱ ሱመያ፣ ሱሃይብ፣ ቢላልና ሚቅዳድ ናቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ በአጎታቸው አቡጣሊብ አማካኝነት ከለላ ስር ነበሩ፡፡ አቡበከር በህዝቦቹ ጥበቃ ስር ነበር ሌሎቹ ግን ሙሽረኮች የብረት ልብስ እንዲለብሱ በማድረግ በመካ ሃሩር ፀሀይ ላይ ማገዷቸው፡፡ከአምስቱ ዉስጥ ቢላል ኢብኑ ረባህ ሲቀር ሙሽሪኮች እንዲያደርጉ ያስገደዷቸውን ነገር አድርገዋል፡፡ ቢላል ይህን የሚሉትን ነገር ለመፈፀም ፈጣሪው ፊት እና ህዝቦቹ ዘንድ ነፍሱን ማዋረድ አልተቻለውም፡፡ በዚህም ምክንያት በመካ ሳዳናዎች ላይ እያዞሩት ህፃናቶቻቸው ይቀልዱበት ያደርጉ ነበር እሱም አላህ አንድ ነው አላህ አንድ ነው ከማለት አልተወገደም፡፡

6. የኢስላም የእምነት መርሆዎች የሰውን ነፍስ ከፈጣሪ ውጭ ለማንም ነብይ ሆነ መልዕክተኛ፣ አላህ ዘንድ ቅርብ ለሆኑ መላእክትም ቢሆን ከአላህ ውጪ ሌላን እንዳታመልክ ነፃ አውጥቷታል፡፡ ይህም አላህ ሙስሊም በሆነች ነፍስ ውስጥ ከአላህ ውጪ ለማንም እንዳታጎበድድ የሚያስችል እምነት ስለተከለ ነው፡፡ ከአላህ ዘንድ ከሚመጣ ነገር ውጪ የሚፈራ ነገር የለም፡፡ ከአላህ ውጪ የሚጠቅምም የሚጎዳ ነገር የለም፡፡ በዚህ አለም ማንም ይሁን ማን አላህ የፈቀደውና የወሰነው ነገር ሲቀር የመጥቀም ሆነ የመጉዳት ስልጣን የለውም፡ ፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡

"(ከሓዲዎች) ከእርሱም ሌላ ምንንም የማይፈጥሩን፣ እነርሱም የሚፈጠሩን፣ ለነፍሶቻቸውም ጉዳትን ለመከላከል ጥቅምንም ለማምጣት የማይችሉን ሞትንና ሕይወትንም መቀስቀስንም የማይችሉን፣ አማልክት ያዙ፡፡ "ፉርቃን-3

ሁሉም ነገር የስልጣን ሁሉ ባለቤት በሆነው አላህ ቁጥጥር ስር ነው፡፡ አላህ ይላል ፡-

አላህም ጉዳትን ቢያደርስብህ ከእርሱ ሌላ ለእርሱ ገላጭ የለውም፡፡ በጎንም ነገር ቢሻልህ ለችሮታው መላሽ የለም፡፡ ከባሮቹ የሚሻውን በእርሱ ይለይበታል፡፡ እርሱም መሓሪ አዛኝ ነው፡፡ ዩኑስ-107

አላህም ሰዎች በሰዎች ላይ እንዳይንጠለጠሉ፣ ቅዱሳንና ብፁአን አድርገው የመያዝን እኩይ ምግባር ከስር መሰረቱ ለመንቀል የአላህ መልእክተኛ መሃመድ (ሰ.ዐ.ወ) የሰው ልጆች ሁሉ ቁንጮና አላህ ዘንድ ከሰዎች ሁሉ በላይ ላቅ ያለ ስፍራ እያላቸው በማንኛውም ሰው ላይ ሊከሰት የሚችሉ ነገሮች በእርሳቸውም ላይ ሊመከሰት እንደሚችል ከመግለፅ አልተወገዱም፡፡እሳቸው

እንዲህ ከሆኑ ሌሎች ተራ ሰዎች ደግሞ ምን ዓይነት አቅም ሊኖራቸው እንደሚችል ማሰብ አይከብድም፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

«አላህ የሻውን በስተቀር ለእራሴ ጥቅምንም ጉዳትንም ማምጣት አልችልም፡፡ ሩቅንም (ምስጢር) የማውቅ በነበርኩ ኖሮ ከመልካም ነገር ባበዛሁና ክፉም ነገር ባልነካኝ ነበር፡፡ እኔ ለሚያምኑ ሕዝቦች አስፈራሪና አብሳሪ እንጂ ሌላ አይደለሁም» በላቸው፡፡" አእራፍ 188

7. የኢስላም የእምነት መርሆች ቀላልነት፣ ምቹነት እና ሁሉንም የሰው ዘር የመልክ፣ የዘር ፣ የእምነት እና የመደብ ልዩነት ወደኋላ በማሽቀንጠር ፍትህ ሰዎች ሁሉ በእኩልነት ሊያገኙት የሚገባ ተፈጥሮአዊ መብት መሆኑን ያዛል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡

አላህ በማስተካከል፣ በማሳመርም፣ ለዝምድና ባለቤት በመስጠትም ያዛል፡፡ ከአስከፊም (ከማመንዘር)፣ ከሚጠላም ነገር ሁሉ፣ ከመበደልም ይከለክላል፡፡ ትገነዘቡ ዘንድ ይገስጻችኋል፡፡ "ነሕል 90

ፍትሃዊነት ቅርብ ዝምድናም ሆነ ባዳ ላይ ያለ ልዩነት በእኩልነት መተግበር አለበት፡፡ አላህ ይላል፡-

«የየቲምንም ገንዘብ ብርታቱን (አካለ መጠን) እስኪደርስ ድረስ በዚያች እርሷ መልካም በኾነች ኹኔታ እንጅ አትቅረቡ፡፡ ስፍርንና ሚዛንንም በትክክሉ ሙሉ፡፡ ነፍስን ችሎታዋን እንጂ አናስገድድም፡፡ በተናገራችሁም ጊዜ በዘመዶቻችሁ ላይ ቢኾንም እንኳ (እውነትን በመናገር) አስተካክሉ፡፡ በአላህም ቃል ኪዳን ሙሉ፡፡ እነሆ ትገሰጹ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ፡፡» አንዓም 152

8. የኢስላም የእምነት መርሆች የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ የተከበረና የላቀ መሆኑን ይገልፃል፡፡

ኢስላም ሰዎችን ሁሉ ያለ እምነት፣ መልክ፣ ዘር፣ፆታና  የመደብ ልዩነት ከፍጥረት አለሙ ሁሉ በላጭ አድርጎ እንደፈጠራቸው እንዲህ በማለት ይገልፃል፡፡ "የሰው ልጅን አከበረንው በየብስም ሆነ በባህር እንዲጓዝ አደረግነው ከመልካም ነገሮችም ሲሳይ ሰጠነው ከፈጠርናቸው ነገሮቹ ሁሉ በላጭ አድርገን ፈጠርነው"

ጃቢር ኢቡኑ አብላህ ይላል "አንድ ቀን አስክሬን በአጠገባችን አለፈ የአላህ ነብይ ለዚህ አስክሬን አከብሮት ተነስተው ቆሙ እኛም ለሱ ቆምን፡፡ "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ይህ እኮ የአይሁድ አስክሬን ነው?" አልናቸው፡፡ እሳቸውም አስክሬን ሲያልፍ ካያችሁ ቁሙ"፡፡ አሉን ቡካሪ ዘግበውታል፡፡

## የኢስላም ደንቦችና ህግጋት ለሰዎች ያላቸው ቀላልነትና ምቹነት

ደንብና ስርዓት ሰው ግቡን ወይንም ማሳካት የሚፈልገውን ውጤት ላይ ለመድረስ የሚከተላቸው ነገሮች ናቸው። ሰው ግቡን ያሳካ ዘንድ ፣ግልፅ፣ ቀላል ገደብ ያለውና በሰው አቅም ተግባራዊ መደረግ የሚችሉ ደንብና ስርዓት ሊኖረው ግድ የላል።በመቀጠል ኢስላም ለሰዎች ያስቀመጣቸው ህግጋት ፣ደንቦችና ስርዓቶች ለሰዎች ምቹ እና ቀላል መሆናቸውን እንገልጻለን።

1. የኢስላም ህግጋት ምንጮች በቀላሉ ለመረዳት የማያስቸግሩ መሆናቸው ነው። አላህ ይላል፡
   ቁርኣንንም ለመገንዘብ በእርግጥ አገራነው፡፡ ተገንዛቢም አልለን?

የህግጋት ምንጮቹ ግልፅ ናቸው። ምንም አይነት ሚስጥር የለውም። ማንኛውም ሰው እንደ መመሪያ ሊቀበለው ይችላል።ማንኛውም ሰው ለመረዳት የሚያስቸግሩትን ነገሮች ወይም በልቦናው ውስጥ የሚመላለሱ ነገሮችን ግልፅ እንዲሆንለት የመጠየቅ መብት አለው። ነገር ግን ሃይማኖታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ማንኛውም ሰው ዘው ብሎ መልስ የመስጠት መብት የለውም። ባይሆን ሃይማኖታዊ ምላሽ የመስጠት በዘርፉ እውቀት ላላቸው ሰዎች ብቻ የተተወ ነው። አላህ የናገራል፡
ከአንተም በፊት ወደእነሱ ወሕይን (ራእይን) የምናወርድላቸውን ሰዎችን እንጂ ሌላን አልላክንም፡፡ የማታውቁም ብትኾኑ የዕውቀትን ባለቤቶች ጠይቁ፡፡ ነኽል-43

እንዲህ መሆኑ ደግሞ ተገቢ ነው። ለምሳሌ ያህል የታመመ ሰው ወደ ሀኪም እንጂ ወደ ማህንዲስ አይሄድም ።ኢስላም ሃይማኖታዊ በሆኑ ጉዳዮች ውስጥ ያለምንም እውቀት መናገርን ከትልልቅ ወንጀሎች ውስጥ አንዱ አድርጎ ይቆጥራል። ሃይማኖታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ያለምንም እውቀት የሚናገር ሰው ሃላልን ሃራም ያደርጋል (የተፈቀዱ ነገሮችን ክልክል ያደርጋል ወይም በተቃራኒው) መብትን ያስነጥቃል ሰዎችን ለችግር ይዳርጋል። አላህ ይላል፡

«ጌታዬ እርም ያደረገው መጥፎ ሥራዎችን፣ ከርሷ የተገለጸውንና የተደበቀውን ኃጢአትንም፣ ያላግባብ መበደልንም፣ በርሱም ማስረጃ ያላወረደበትን (ጣዖት) በአላህ ማጋራታችሁን፣ በአላህም ላይ የማታውቁትን መናገራችሁን ብቻ ነው» በላቸው፡፡ አእራፍ-33

የአላህ መልዕክተኛም በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የእውቀቱ ባልተቤት ያልሆኑ ሰዎችን መጠየቅ የሚያስከትለውን አሉታዊ ውጤት ገልፀዋል “አላህ እውቀትን የሚያስወግደው ከሰው ልጆች አእምሮ በማስወገድ አይደለም። እውቀት የሚወገደው የእውቀት ባለቤቶች ወይም ምሁራኖች አንድም እንኳን እስከማይቀሩ ድረስ ሳይኖሩ ሲቀር ነው። ያኔ ሰዎች አውራ መሃይሞቻቸውን ይጠይቃሉ። እነሱም ያለምንም እውቀት ድንጋጌን ይሰጣሉ እራሳቸው ጠመው ሌላውን ያጠማሉ፡
፡

ኢስላም ሰዎች በደፈናው እንዲያምኑት የሚያስገድድ ሃያማኖት አይደለም የተድበሰበሱና መጠየቅ የሚከለከልባቸው ነገሮችም የሉትም።ምንአልባት የሰው ልጅ አእምሮ ሊደርስባቸው የማይችላቸው የሩቅ ሚስጥር ጉዳዮች ሲቀር። አላህ እነዚህን የሩቅ ምስጢር ጉዳዮች የሰው ልጅ ለመረዳትና ለመገንዘብ የሚያስችለውን አቅም ስላልሰጠው  አእምሮውም እነዚህን ለመረዳት ውስን በመሆኑና እነዚህን ጉዳዮች በማወቁም ሆነ  ባለማወቁም ምንም አይነት ፋይዳ ስለማይሰጠውም ጭምር ነው። አላህ ይላል "ስለ ሩህ ይጠይቁሃል ሩህም ከጌታዬ ዘንድ ብቻ የሆነ ነገር ነው ከእውቀትም ጥቂትን እንጂ አልተሰጣችሁም በላቸው"

አላህ እንዲህ ይላል "ስለመጨረሻው ሰዓት መቼ እንደምትከሰት ይጠይቁሃል…."

የሩቅ ሚስጥርም ሆነው ነገር ግን ሰዎች በማወቃቸው ጠቀሜታ የሚያገኙባቸው ጉዳዮች  አላህ በእርግጥ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንደበት ግልፅ አድርጓል። እንደ ጀነት፣ እሳት፣ ሂሳብ፣ የቀደሙት ህዝቦችን ከነብያቸው ጋር  የነበረውን  ታሪክ ይመስል። እነዚህን ነገሮች ማብራራት ለወደፊት ትምህርትና ግንዛቤ ስለሚፈጥሩ እነዚህን ነገሮች ሰዎች እንዲውቋቸው ማድረግ ሰዎች መልካም ስራ እንዲሰሩ ያስችላቸዋል።አላህ ይላል፡

የምትንቀለቀልንም እሳት አስጠነቀቅኳችሁ (በላቸው)፡፡ከጠማማ በቀር ሌላ የማይገባት የኾነችን፡፡ አለይል 14-15

2. የኢስላም ህግጋት ጥራት የተገባው ፈጣሪ አላህ ለሰው ልጆች ሁሉ በእኩልነት የሚመለከቱ አድርጓቸዋል ባለስልጣናትና ተራውን ህዝብ፣ ድሃውንና ሀብታምን ፣ባሪያና ሎሌውን ጥቁርና ነጩን የማይለዩ ህጎች ናቸው። ማንኛውም ግለሰብ የፈለገውን ያህል በህብረተሰቡ ዘንድ ላቅ ያለ ደረጃና ስልጣን  ቢኖረውም ህግጋቶቹን መጣስ አይችልም። አላህ ይላል፡

አላህና መልክተኛውም ነገርን በፈረዱ ጊዜ ለምእምናንና ለምእምናት ከነገራቸው ለእነርሱ ምርጫ ሊኖራቸው አይገባም! የአላህንና የመልክተኛውንም ትእዛዝ የጣሰ ሰው ግልጽ የሆነን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ፡፡ " አልአህዛብ 36

ህግጋቶቹንም ሁሉም ሰው ከተራው ህዝብ እስከ  ባለስልጣን ያለምንም ልዩነት ተግባራዊ እንዲያደርጓቸውና እንዲከብሯቸው ደንግጓል። አላህ ይላል፡

"የምእምናን ቃል የነበረው ወደ አላህና ወደ መልክተኛው በመካከላቸው ሊፈርድ በተጠሩ ጊዜ ሰማን፤ ታዘዝንም ማለት ብቻ ነው፡፡ እነዚህም እነሱ የፈለጉትን የሚያገኙ ናቸው፡፡" ኑር-51

በእስልምና ውስጥ ለማንም ሰው ልቅ የስልጣን ባለቤትነትን አልተሰጠም። መሪ እንኳን የያዛቸውን ሁሉም ስልጣኖች ኢስላም ባስቀመጣቸው የሸሪዓ ድንጋጌዎችና ማዕቀፍ የተገደበ ነው፡፡ ይሄ የኢስላም ሸሪዓ ባህሪ ለሰው ልጆች ምቹና ተመራጭ ያደርገዋል። በኢስላም ውስጥ ገደብ

የለሽ ስልጣን እና አምባገነንነት ለማንም አልተደረገም፡፡ እንዲህ አይነት ነገር ቢከሰት እንኳን ማንም ሰው ሊሰማውና ሊቀበለው አይችልም፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ይሄን በማስመልከት እንዲህ ይላሉ፡፡

"አንድ ሙስሊም በሚወደውም ሆነ በሚጠላው ጉዳይ መሪውን የማዳመጥና የመታዘዝ ግዴታ አለበት በወንጀል እስካልታዘዘ ድረስ በወንጀል ከታዘዘ ማዳመጥም ሆነ መታዘዝ የለም፡፡ኢስላም በዚህ መልኩ ጠቅለል ባሉና በልዩ ሁኔታ የሚታዩ ድንጋጌዎችን በማስቀመጥ ጎዶሎ ከሆነው የግለሰቦች ስሜት አርቆታል፡፡ ንኡስ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ግን የኢስላም ህግጋት ግትር አይደሉም፡ ፡ በነዚህ ጉዳዮች ላይ ሙስሊሞች ከሚኖሩበት ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በጥምረት ሊሄዱ የሚችሉ መርሆዎችን ደንብና ስርዓት እንዲያበጁ በሩን ክፍት አድርጎላቸዋል፡፡ እነዚህ ደንቦችና መርሆዎች ኢስላም ከተገነባባቸው ዋናዋና መርሆዎች ጋር የማይቃረኑ መሆን ይገባቸዋል፡፡

3. የኢስላም ድንጋጌዎቹና አስተምህሮቶቹ መለኮታዊ እና ዘላለማዊ በመሆናቸው መለወጥና መተካት አያስፈልጋቸውም፡፡ የኢስላም ደንብና ህግጋቶች እንደ ሰው ልጅ ህግጋት ሳይሆን ከዶሎነትና ከስህተት የጠሩ እንዲሁም ከሰው እውቀትና ተሞክሮ ተፅዕኖ ስር የሚወድቁ ህግጋት አይደሉም፡፡የህግጋቶቹ ባለቤት አላህ በዝንተ ዓለም እውቀቱ ሙሉ የሆነ ጌታ ስለሆነ፡ ፡ የህግጋቶችና ድንጋጌያዎች ምንጭ አላህ ፍጥረታትን ሁሉ ያስገኘ፤ ጠቅላላ ያሉበትን ሁኔታ በጥልቀት የሚያውቅና ጉዳያቸውንም የሚፈቱበት መንገድ ከእሱ በላይ አዋቂ ስለሌለ ማንም ሰው የቱንም ያህል እንኳን በህብረተሰቡ ዘንድ ላቅ ያለ ደረጃ ቢኖረውም የአላህን ህግጋት መቃወም አይችልም፡፡ አላህ በደነገገው ላይ መቀነስም ሆነ ማጉደል አይቻለውም፡፡አላህ ይላል፡

"የማይምንነትን ፍርድ ይፈልጋሉን= ለሚያረጋግጡም ሰዎች ከአላህ ይበልጥ ፍርዱ ያማረ ማን ነው= " ማኢዳ-50

4. በኢስላም ህግጋት ውስጥ በሌሎች እምነት የሚስተዋለውን የመንፈስ አባት የሚባል ነገር የለም፡፡ ኢስላም ከሱ በፊት የነበሩት ህዝቦች ይዘውት የቆዩትን ለቁዱሳኖች የሚሰጥ የተለየ ቦታ እና አማላጅነት አውግዟል፡፡ አላህ ይላል፡

"ንቁ! ፍጹም ጥሩ የኾነው ሃይማኖት የአላህ ብቻ ነው፡፡ እነዚያም ከእርሱ ሌላ (ጣዖታትን) ረዳቶች የያዙት «ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቀርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም» (ይላሉ)፡፡ አላህ በዚያ እነርሱ በእርሱ በሚለያዩበት ነገር በመካከላቸው ይፈርዳል፡፡ አላህ እርሱ ውሸታም ከሓዲ የኾነን ሰው አያቀናም፡፡ " አዙመር 3

5. አላህ (ሱ.ዐ) እንደዚህ ዓይነቱን በሰዎችአማካኝነት የመማለድና እና ወደ ፈጣሪ መቃረብን የመፈለግ ትክክለኛ ምንነት ግልፅ አድርጓል፡፡ እሱም ምንም የማይጠቀምና የማይጎዳ ነው፡፡ ከምንም አያብቃቃቸውም፡፡ እነሱም እንደራሳቸው ፍጡራን እንጂ ሌላ አይደሉም፡፡ አላህ ይላል፡

" እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትገ[3]ቸው ብጤዎቻችሁ ተገዢዎች ናቸው፡፡ እውነተኞችም እንደኾናችሁ ጥሩዋቸውና ለእናንተ ይመልሱላችሁ፤ (መመለስ ግን አይችሉም)፡፡" አእራፍ 194

ኢስላም በአላህና በባሮቹ መሃከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ይሄም የሰው ልጅ ፍላጎቶቹን ለመፈፀምና ከሱም ምህረት ለማግኘት ያለምንም ጣልቃ ገብነት በአላህ ላይ ጥግ ድረስ ማመንና ወደሱ በመጠጋት ብቻ ነው የሚጠበቅበት፡፡ ወንጀልም የፈፀመ ሰው ወደፈጣሪው ብቻና ብቻ ምርኮኛ በመሆንና በመዋደቅ ብቻ ምህረት በየትኛውም ቦታና ጊዜ እንዲሁም ሁኔታ መጠየቅ የሚገባው፡፡ አላህ ይላል፡

"መጥፎም የሚሠራ ሰው ወይም ነፍሱን የሚበድል ከዚያም (ተጸጽቶ) አላህን ምሕረት የሚለምን አላህን መሓሪ አዛኝ ኾኖ ያገኘዋል፡፡ ኒሳዕ 110. በሌላው የአላህ ቃል "ወቃለ ረቡኩም አድኡኒ አስተጂብ ለኩም፡፡"

በኢስላም እራሳቸውን የፈጣሪ ወኪል አድርገው ለወንጀል ምህረት የሚያሰጡ፤ የተፈቀዱና የተከለከሉ ነገሮችን እና ደንብንና ህግጋትን የሚደነግጉ፣ የፈለጉትን ሰው ጀነት የሚያስገቡ ለፈለጉት ደግሞ የሚከለክሉ የሃይማኖትና የመንፈስ አባቶችን አላደረገም፡፡አላህ ዘንድ ሰዎች ሁሉ እኩል ናቸው፡፡ ድንጋጌዎችን የማውጣት ባለሙሉ መብት የአላህ ብቻ ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ " ቀሳውስቶቻቸውና ባህታዊኖቻቸውን ከአላህ ውጪ አምላክ አድርገው ያዟቸው" የሚለውን የአላህን ቃል ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፡፡

"እነዚህ ሰዎች ቀሳውስቶቻቸውን የሚያመልኩ አልነበሩም ነገር ግን አንድን ነገር ሲፈቅዱላቸው እንደተፈቀደ ተቀበሉ፡፡ ክልክል ሲያደርጉባቸው እነሱም ክልክል አድርገው ያዙ፡፡

6. የኢስላም የሰዎችን የጋራ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን እንዲሰፍን ህግጋቶቹና ድንጋጌዎቹ በጋራ ምክር ቤት (ሹራ) እንዲታዩ ማስቀመጡ ነው፡፡ ይሄም ለህዝብ ጥቅም መዋል የሚገባቸው ነገሮች በህዝብ ስም ለግለሰባዊ ጥቅም እዳይውሉ ለማድረግ ነው፡፡ በተለምዶ እንደሚባለው በአንድ አእምሮ ከማሰብ በብዙ አእምሮ ማሰብ ይሻላል ፡፡ አላህ አንዲህ ይላል፡

ከአላህም በኾነች ችሮታ ለዘብክላቸው፡፡ ዐመለ መጥፎ ልበ ደረቅም በኾንክ ኖሮ ከዙሪያህ በተበተኑ ነበር፡፡ ከእነርሱም ይቅር በል፡፡ ለእነርሱም ምሕረትን ለምንላቸው፡፡ በነገሩም ሁሉ አማክራቸው፡፡ ቁርጥ ሐሳብም ባደረግህ ጊዜ በአላህ ላይ ተመካ፡፡ አላህ በርሱ ላይ ተመኪዎችን ይወዳልና፡፡ ኢምራን 159

7. ኢስላም ከቁርዐንና ከነብዩ ሱና አስረጂዎችን ማግኘት በማይቻልባቸው ጉዳዮች ላይ የጥናትና የምርምር ውጤቶችን እንደ አንድ መመሪያ የሚያስተናገድ ሃይማኖት ነው፡፡ ይህ ባህሪው ኢስላም በየትኛውም ጊዜና ቦታ የሚፈጠሩ መልካም ነገሮችን ለመቀበል ዝግጁ የሆነ ሃይማኖት ያደርገዋል፡፡ የኢስላም ሃይማኖት ከጊዜና ቦታ መቀያየር ጋር አብረው ሊቀያየሩ የማይችሉ መሰረታዊና ጠቅለል ያሉ የእምነት መርሆዎችንና የአምልኮ ስርዓቶችን ይዟል፡፡ ሶላትን እና የቁጥሮቻን ብዛት፣ የሚሰገደበት ወቅት፣ዘካን፣ ፆምንና የሚፆምበት ወቅት፣ ሃጅ እና የሀጅ ስነስርዓት እና የመሳሰሉት እንደምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ለሚከሰቱ ክስተቶች በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩን በቁርዐን ውስጥ መፈታት የሚችል ከሆነ ሌላ መረጃ መፈለግ ሳያስፈልግ እንዲፈታ ይደረጋል፡፡ ቁርዓን ውስጥ ካልተገኘ ትክክለኛነታቸው በተረጋገጡ የአላህ መልዕክተኛ ሱና ሌላ ከሱ ወጪ መረጃ ሳያስፈልግ እንዲፈታ ይደረጋል ፡ ፡ በዚህም ውስጥ ሊዳሰሱ ያልቻሉ ጉዳዮች ደግሞ ለፈጣሪ ያደሩና ራሳቸውን ያስገዙ የሃማኖት ሙሁራን የጥናትና ምርምር ስራዎች ያሉበትን ዘመን ቦታና እንዲሁም የህዝብን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚቀርቡ የመፍትሄ ሃሳቦች ተቀባይነት አላቸው፡፡

እነዚህ የመፍትሄ ሃሳቦች ከመሠረታዊ የቁርዓንና የሱና ፅንሰ ሃሳቦች ጋር እና ከሸሪዓ ህግጋትና መርሆዎች ጋር በማይጋጭ መልኩ መፈፀም ይኖርበታል፡፡ ይህ ማለት ግን የሰዎችን ልብወለዳዊ ስሜትና ፍላጎት የተጠናወተው የጥናትና ምርምር ስራዎችን ያጠቃልላል ማለት አይደለም፡፡ የጥናትና የምርምር ስራዎች ስንል ለሰው ልጆች በመልካም ነገር ጥቅም ሊሰጡ በሚችሉ ጉዳዮች ቁርዓንና ሱናን በማይጋጭ መልኩ ብቻ ነው ተቀባይነት የሚኖራቸው፡፡

ለፈጣሪ በየትኛውም ጊዜም ሆነ ቦታ ያደሩ የሃይማኖቱ ምሁራንን የሚያደርጉት ጥናትና ምርምር በሃይማኖቱ እንደ ሶስተኛ አማራጭ የመረጃ ምንጭ ተደረጎ መወሰዱ የኢስላም ሃይማኖት ለየትኛውም ቦታና ዘመን ለሚፈጠር የህብረተሰብ ጥያቄን ማስተናገድ የሚችል እንዲሆን አድርጎል፡፡

8. ኢስላም በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ የማክረርና ፅንፈኝነትን በር ዘግቷል፡፡ እንዲህ የሚለውን የአላህን ንግግር ተግባራዊ በማድግ፡

አላህ በእናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፡፡ በእናንተም ችግሩን አይሻም፡፡ በቀራህ-185

የአላህ መልዕክተኛም "በሃይማኖት ውስጥ ፅንፈኛ ከመሆን አደራችሁን ከናንተ በስተፊት የነበሩት ህዝቦች የጠፉት በፅንፈኝነታቸው ምክንያት ነው፡፡ ኢማሙ አህመድና ነሳኢ ዘግበውታል፡፡

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በሃይማኖት ውስጥ ማክረርና ፅንፈኝነትን ይዘውት ከመጡት ቅን መንገድ እንደማፈንገጥ ቆጥረውታል። አነስ አብኑ ማሊክ እንዲህ ይላል (ረ.ዐ) "ሶስት ሰዎች ስለነብዩ ኢባዳ ለመጠየቅ ወደ ቤታቸው መጡ። በተነገራቸው ጊዜም የነሱን ኢባዳ አጣጣሉ። ያለፈውንና የሚመጣውን ወንጀል ምህረት ከተደረገላቸው ነብይ አንፃር የእኛ ኢባዳ የትናየት ነው በማለት ኢባዳቸውንም አጣጣሉ፡ አንደኛው እኔ ከአሁን በኋላ ለሊቱን ሁሉ እስከመቼውም እሰግዳለሁ አለ። ሁለተኛ እኔ ደግሞ አመቱን ሁሉ ያለማፍጠር እፆማለሁ አለ ሶስተኛው ደግሞ እስከመቼውም አላገባም አለ። ነብዩ ሲመጡ እንዲህ አሏቸው "እናንተ ናችሁ እንዲህ እንዲህ ያላችሁት በጌታዬ ይሁንብኝ እኔ ከናንተ በላይ በጣም አላህን ፈሪያችሁና እና እሱንም ተጠንቃቂያችሁ ነኝ። ነገር ግን እፆማለሁ አፈጥራለሁ፤ እሰግዳለሁ፤ እተኛለሁ፤ እንዲሁም አገባለሁ። ከንደዚህ ዓይነቱ የኔ መንገድ ያፈነገጠ ከኔ ጋር አይደለም። ሲሂሁስ ቡድሪ 2.0 ቁጥር 4776።

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጓደኞቹን እንደዚህ አይነት ፅንፈኝነትና የማክረር ተግባርን እንዲርቁ ያስጠነቅቃቸውም ነበር። አብደላህ ኢብኑ አምር ኢብኑ አልአስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉኝ ብሎ ተናገረ "አንተ አብደላህ ሆይ አንተ አመቱን ሁሉ እንደምትፆም ሙሉ ሌሊት ስትሰግድ እንደምታድር የተነገረኝ ነገር እውነት ነውን ብለው ጠየቁት" እሱም "አዎን አንቱ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ አላቸው።" ከአሁን በኋላ እንደዚህ አታድርግ። አንዳንዴ ፁም ከዚም አፍጥር፤የተወሰነ ሰዓት ተኛ በተቀረው ስገድ። ለአካልህ ባንተ ላይ የማረፍ መብት አለው። ለአይንህ የእንቅልፍ መብት አላት። ለሚስትህ በአንተ ላይ መብት አላት። ከእያንዳንዱ ወር ሶስት ቀን ፁም የእያንዳንዱ ቀን ፆም ምንዳ በአስር ይባዛልሃል። በዚህ ሁኔታ ዓመቱን ሙሉ እንደፆምክ ይቆጠርልሃል አሉት። እሱም በማስከተል "የአላህ መልዕክተኛ እኔ እኮ ከዛ በላይ የመፈፀም አቅሙ አለኝ" አላቸው።" "እንግዲያውስ አንተ እንዳልከው ሳይሆን እንደ ነብዩሏህ ዳውድ አይነት ፆም ፁም ከሱ በላይ እንዳትጨምር አሉት"

አብዱላህ ከሸመገለ በኋላ "ሃይማኖቴን አጠብቃለሁ ብዬ በራሴ ላይ ጠበቀብኝ ምንአለ የአላህ መልዕክተኛ ያቀለሉልኝን ምክሮች በተቀበልኩኝ ኖሮ" በማለት ለፀፀት ተዳረገ-ቡኻሪ ዘግበውታል

ይህ ማለት ግን ኢስላም ወደ አለማዊነት የተዘነበለ ያለምንም ገደብ በምድራዊ ስሜትና ምቾት በመዘፈቅ መኖር ማለት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል። ኢስላም ሚዛናዊና መሃከለኛ ሃይማኖት ነው። አለማዊና መንፈሳዊ ህይወትን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ አቀናጅቶ አንደኛው በሌላኛው ላይ ድንበር ሳያልፍ የሚስተናገዱበት ሃይማኖት ነው። ኢስላም መንፈስንና አካልን

ሚዛናዊ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አበክሮ ያዛል ። ሙስሊም በአለማዊ ጉዳዮች ውስጥ በሚሰምጥበት ሁኔታ ላይ አያለ አላህ ግዴታ ያደረገበትን መንፈሳዊ የአምልኮ ተግባራትን እንዲፈፅም ያዘዋል። አላህ ይላል፡

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በዐርብ ቀን ለስግደት ጥሪ በተደረገ ጊዜ ወደ አላህ ማውሳት ኺዱ፡፡ መሸጥንም ተዉ፡፡ ይህ የምታውቁ ብትኾኑ ለእናንተ በጣም የተሻለ ነው፡፡ " በመንፈሳዊ የአምልኮ ተግባራት ውስጥ ስምጥ ብሎ ሲቀር የስራንና ሲሳይን የመፈለግ አስፈላጊነት ይነገረዋል። አላህ ከዚሁ አንቀፅ በማከተል እንዲህ ይላል፤

"ሶለቲቱም በተፈጸመች ጊዜ በምድር ላይ ተበተኑ፡፡ ከአላህም ችሮታ ፈልጉ፡፡ አላህንም በብዙ አውሱ፡፡ ልትድኑ ይከጀላልና፡፡"

ኢስላም በሰው ልጆች አካል ላይ ጉዳት የሚስከትሉና ለከፋ ብክነት የሚዳርጉ እስካልሆኑ ድረስ ሰዎች በምድራዊ ህይወታቸው መደሰት መዝናናት የሚችሉበትን ስርዓት አበጅቷል" አላህ ይላል

የአዳም ልጆች ሆይ! (ኀፍረተ ገላችሁን የሚሸፍኑትን) ጌጦቻችሁን በመስገጃው ሁሉ ዘንድ ያዙ፡፡ ብሉም፤ ጠጡም፤ አታባክኑም፡፡ እርሱ አባካኞችን አይወድምና፡፡ አእራፍ-31

በኢስላም መንፈሳዊና አለማዊ በሆኑ ነገሮች መሃከል ምንም አይነት ተቃርኖ የለም። አላህ ይላል "ለይሰአለይኩም ጁናሁን አንተብተጉ ፈድለን ሚንረቢ ወኢዛ አፈድትም ሚንአረፋቲን…."

9. አንድ ሙስሊም በህይወቱ ላይ ከፍተኛ አደጋ ይደርስብኛል ብሎ እስከፈራ ድረስ ሰውነቱ ከጉዳት እንዲታደግ የሚያስችለውን ያህል መጠን አላህ ክልክል ያደረጋቸውን ምግቦች እንደ ሞተ እንስሳ፣ የአሳማ ስጋን አስካሪ መጠጥን መመገብና መጠጣት ይፈቅዳል። አላህ እንዲህ ይላል፡

እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከነዚያ ከሰጠናችሁ ጣፋጮች ብሉ፡፡ ለአላህም እርሱን ብቻ የምትገዙ እንደኾናችሁ አመስግኑ፡፡ በናንተ ላይ እርም ያደረገው በክትንና ደምን፣ የእሪያ ሥጋንም፣ በእርሱም (ማረድ) ከአላህ ስም ሌላ የተነሳበትን ነገር ብቻ ነው፡፡ ሽፍታና ወሰን አላፊ ሳይኾን (ለሙብላት) የተገደደ ሰውም በርሱ ላይ ኃጢአት የለበትም አላህ መሓሪ አዛኝ ነውና፡፡ በቀራህራ 172

የዚህን የቁርዓን አንቀፅ ትርጉም በማስመልከት ሰይድ ቁጥብ አላህ ይዘንለትና እንዲህ ይላል "የኢስላም እምነት መርሆዎች የሰው ልጅን እንደ እንስሳት፣ መላዕክት፣ ወይንም እንደ ሰይጣን ሳይሆን እንደ ሰው እውቅና ይሰጣል።የሰውን ልጅ ከሁሉም ድክመትና ጥንካሬው ጋር እውቅና

ይሰጣል። በሰው ውስጥ የሚገኘውን ስሜታዊ የሆነውን ስጋዊ አካሉን፣የሚያስበውን አእምሮውንና፣ ጥልቅ ስሜቱን የሚገልፅበትን መንፈሱን (ሩህ) በአንድነት አስተሳስሮ እንዲኖሩ ያደርጋል። ይህ ብቻም ሳይሆን ሰዎች እንዲፈፅሙት ግዴታ የተደረገባቸው ነገሮችና ትዕዛዞች ያለምንም መከራና ችግር ከሰው የመፈፀም አቅምና ተፈጥሮ ጋር የተሳሰሩ ናቸው። በሌላ አባባል ሰዎች መፈፀም የማይችሉትን ነገር እንዲሰሩት ግዴታ አልተደረገባቸውም።

10.በኢስላም ውስጥ መልካም ስራ ለሰራ ሰው ምንዳው በብዙ እጥፍ ይባዛለታል። ነገር ግን ወንጀል የሰራ ሰው የሚመነዳው የሰራውን ወንጀል አምሳያ ብቻ ነው። አላህ ይላል፡

በመልካም ሥራ የመጣ ሰው ለእርሱ ዐሥር ብጤዎችዋ አሉት፡፡ በክፉ ሥራም የመጣ ሰው ብጤዋን እንጅ አይመነዳም፡፡ እነርሱም አይበደሉም፡፡ አንዓም 160

## የኢስላም ሃይማኖዊ ጥሪ ሰዎቸ ያለው ምቹነትና ገራገርነት›

ኢስላም አለም አቀፋዊ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ላሉ ሰዎች የተሰጠ መልዕክት እንደመሆኑ መጠን ወደ እሱ ጥሪ የሚያደርግበት መንገድ ለስለስ ያለና በጥበብ የተሞላው መሆን ይገባዋል። ለሰዎች መልካም ነገርን ከመውደድና ከመመኘት መንፈስ በመነጨ መቅረብ ይገባዋል።እንዲህ መሆኑ አንደኛው የሌላውን አመለካከት እንዲያከብርና እንዲቀበል፣ የውይይትና የመረዳዳት መንፈስን ይፈጥራል። አላህ እንዲህ ይላል ፡-“ወደ ጌታህ መንገድ በጥበብ እና በጥሩ ተግሳጽ ተጣራ።”

ኢስላም ለሰዎች ጥሪ ሲያደርግ የሚከተላቸው መንገዶች ለሰው ልጅ ተፈጥሮ ምቹና ገር ስለመሆናቸው የሚያሳዩ ገፅታዎቹን እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

1. ኢስላም ወደ እምነቱ መቀላቀል ለሚፈልጉ የሌላ እምነት ተከታዮችያለምንም ቅድመ ሁኔታ በሩን ክፍት አድርጓል። እንዲያውም አላህ ይደሰትባቸዋል ያፅናናቸዋል የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ ““አንድ ሰው ጭው ባለ በረሃ ላይ ምግቡን መጠጡን እንዲሁም ለጉዞ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶቹን የተሸከመች ግመሉ ተኝቶ ሊነሳ ተሰወረችበት።ማፈላለግም ጀመረ ነገር ግን ለከፋ ረሃብና የውሃ ጥም ከመዳረግ ውጪ ምንም አላተረፈም። ከመሞት ውጪ ሌላ አማራጭ እስከማይኖረው ድረስ ተስፋ ቆረጠ በመጀመሪያ ወደ ነበረበት ቦታ ተመልሶ በመሄድም ተኛ ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለ ከእንቅልፉ ሲነቃ ስንቅቁን ምግብና መጠጡን የተሸከመችው ግመል አጠገቡ ቆማ አገኛት። የታሰረችበትን ገመድ በመያዝ እንዲህ በማለት “ አላህ ሆይ አንተ ባሪያዬ ነህ እኔ ጌታህ ነኝ” በማለት ከመጠን ባለፈ ደስታ በመነጨ ትልቅ ስተት ፈፀመ፡ ፡ይህ ሰው ከሚደሰተው በላይ አላህ ባሪያው ከወንጀሉ ወደሱ ተፀፅቶ ሲመለስ በጣም ይደሰታል።” ሙስሉም የዘገቡት

2. ኢስላም ተከታዮቹ ወደ መልካም ነገር የሚያደርጉት ጥሪ በፍቅር በደስተኝነት ላይ የተመሰረተ ጥሪ እንዲያደርጉ አዟል። የአላህ መልዕክተኛ መሪ አድርጎ ለመረጣቸው ሙአዝና አቢሙሰል አልአሽአሪን ለኢስላም ጥሪ ወደ የመን በላኳቸው ጊዜ እንዲህ አሏቸው "አበስሩ ሰውን አታስጨንቁ ነገሮችን አቅልሉ አታከባብዱም አንዱ ሌላውን ይታዘዝ አትለያዩ"

3. ኢስላም ተከታዮቹን ከተቃዋሚዎቻቸው ጋር የሚያደረጉት ውይይት  የተቃዋሚዎቻቸውን ክብርና ደረጃቸውን  በጠበቀ መልኩ እንዲያደርጉ አዟል። አላህ ይላል፡

የመጽሐፉን ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ፡፡ ከእነርሱ እነዚያን የበደሉትን ሲቀር፡፡ በሉም «በዚያ ወደኛ በተወረደው ወደናንተም በተወረደው አመንን፡፡ አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው፡፡ እኛም ለእርሱ ታዛዦች ነን፡፡» አንከቡት 46

አንድን አመለካከት እንዲቀበሉ ማስገደድ የለም ባይሆን የሚያቀርቡትን ማስረጃዎች በአክብሮት በማዳመጥ ውይይት ማካሄድና ተገቢውን ምላሽ መስጠት ነው የሚጠበቀው።

ተቃራኒ አመለካከት ካለው ሰው ጋር የሚደረግ ውይይት ሊከተሉት የሚገባው መንገድ ቅንነት እና ግልፅነት የተላበሰ እንዲሁም ጥሪ የሚደረግላቸው ሰዎች የአስተሳሰብ ደረጃ ጋር ተዛማጅ መሆን ይኖርበታል። ከሞት በኋላ መቀስቀስን እንደምሳሌ ማንሳት ይቻላል። አብደላህ ኢብኑ አባስ እንዲህ ላሉ አሲ ኢብኑ ዋኢል ሙስሊም ባልነበረበት ወቅት ወደ ነብዩ ዘንድ መጣና የተሸፈነ አጥንት በመክፈት እንዲህ አለ "አንተ መሃመድ ይሄ አጥንት ከበሰበሰ በኋላ አላህ ይቀሰቅሰዋልን? አላቸው። ነብዩም "አዎ አላህ ይህንን ይቀሰቅሰዋል ይገድልሃል፣ ይቀሰቅስሃል፣ ከዚያም የጀሃነም እሳት ውስጥ ያስገባሃል።" አሉት። አብደላህ ኢብኑ አባስ፤-

"ሰውየው እኛ ከፍቶት ጠብታ የፈጠርነው መኾናችን አላወቀምን? ወዲያውም እርሱ (ትንሣኤን በመካድ) ግልጽ ተከራካሪ ይኾናልን? ለእኛም ምሳሌን አደረገልን። መፈጠሩንም ረሳ። «አጥንቶችን እነርሱ የበሰበሱ ሲኾኑ ሕያው የሚያደርጋቸው ማነው?» አለ። «ያ በመጀመሪያ ጊዜ (ከኢምንት) ያስገኛት ሕያው ያደርጋታል። እርሱም በፍጡሩ ሁሉ (ኹኔታ) ዐዋቂ ነው» በለው።

የሚለው የቁርአን አንቀጽ በዚህ ምክንያት  እንደወረደ ተናግረዋል። እንዲህ አይነቱ ውይይትን ሎጂካዊና ግልጽ የሆኑ ማስረጃዎችን መሰረት አድርጎ መልስ መስጠት ንፁህ አእምሮና እውነት ፈላጊ ለሆኑ ሰዎች ለጥርጣሬ ምንም አይነት ክፍተት በማይሰጥ መልኩ ማቅረብ እንደሚያስፈልግ ሃይማኖቱ ያስገነዝባል።በእንዲህ ዓይነት መንገድ በሚደረጉ ውይይቶች በስተመጨረሻም ኢስላም ነው የሚያሸንፈው። አላህ በነብዩ ኢብራሂም ታሪክ ውስጥ የሄን ያስተምረናል።

ወደዚያ አላህ ንግሥናን ስለሰጠው ኢብራሂምን በጌታው ነገር ወደ ተከራከረው ሰው አላየህምን= ኢብራሂም «ጌታዬ ያ ሕያው የሚያደርግና የሚገድል ነው» ባለ ጊዜ «እኔ ሕያው አደርጋለሁ እገድላለሁም» አለ፡፡ ኢብራሂም፡- «አላህ ፀሐይን ከምሥራቅ በኩል ያመጣል (አንተ) ከምዕራብ በኩል አምጣት» አለው፡ ፡ ያም የካደው ሰው ዋለለ፤ (መልስ አጣ) አላህም በዳዮች ሕዝቦችን አይመራም፡፡

በቀራህ 258

4. የኢስላም የመማርና ማስተማር ስርዓት ጎጂ ከሆነ ትችትና ወቀሳ አንዱን ከሌላው ከማበላለጥ፣ ከማጥላላትና፣ ከማዳላት የራቀ ነው፡፡

ለባሮቼም በላቸው፡- ያችን እርሷ መልካም የኾነችውን (ቃል) ይናገሩ፡፡ ሰይጣን በመካከላቸው ያበላሻልና፡፡ ሰይጣን ለሰው ግልጽ ጠላት ነውና፡፡ ኢስራዕ 53

5. ለሰዎች ትምህርት ወይም ጥሪ በሚደረግበት ጊዜ ጥሪ ለሚደረግላቸው ሰዎች በፍቅር በእዝነትና በርህራሄ ሊሰጥ ይገባል፡፡ አላህ ይላል፤" እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በኢብራሂም ለምን ትከራከራላችሁ

6. ተውራትና ኢንጂልም ከርሱ በኋላ እንጅ አልተወረዱም፡፡ ልብ አታደርጉምን በላቸው፡፡ እንደዚሁም ጥሪ የሚደርግበት መንገድ በልብ ውስጥ ተፅእኖ መፍጠር በሚችሉ ተወዳጅ ንግግሮች መደረግ እዳለበት ያስተምራል፡፡

7. ጥሪ የሚደረግባቸው መንገዶች ለስላሳና የወቀሳ ቃላትን ከመጠቀም የፀዱ እንዲሆኑ አድርጓል፡ ፡ አላህ ሙሳንና ወንድሙን ሃሩን ወደ ፈርኦን ጥሪ እንዲያደርጉለት በላካቸው ጊዜ ያላቸውን አስታውስ፡፡
   "ወደ ፈርኦንም ሂዱ እሱ ድንበር አልፏልና እንዲገስጹና ጌታውንም ይፈራ ዘንድ ለስለስ ባለ አንደበት ጥሪ አድርጉለት" አላቸው

8. ኢስላም የተለየ እምነትና አመለካከት ካላቸው ሰዎች ጋር በሚያደርገው ውይይት ተወያዮችን አስረጂዎቻቸውንና ምስክሮቻቸውን እንዲሁም የሚያስቡትን ነገር ሁሉ አቅርበው እንዲከራከሩ ነፃነት ይሰጣል፡፡ አላህ ይናገራል "«ከአላህ ሌላ የምትግገዟቸውን አያችሁን? ከምድር ምንን እንደ ፈጠሩ አሳዩኝ፡፡ ወይም በሰማያት ለእነርሱ (ከአላህ ጋር) መጋራት አላቸውን? (ያማልዱናል በማለታችሁ) እውነተኞች እንደ ኾናችሁ ከዚህ (ቁርኣን) በፊት የኾነን መጽሐፍ ወይም ከዕውቀት የኾነ ቅርስን አምጡልኝ» በላቸው፡፡"

9. ኢስላም ተቃራኒ እምነትና አመለካከት ያላቸውን ሰዎች ጥሪ የሚያደርግበት መንገድ አላማ የሚያደርገው የጋራ የሆኑ ጉዳዮችን በማንሳትና ተቃራኒ አመለካከት ያላቸውን አካላት ሊያራርቅ በሚችሉ አጀንዳዎች ዙሪያ ሳይሆን ወደ መቀራረብና መስማማት በሚያደርሷቸው ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት እንዲያካሂዱ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ጥሪ ወይንም ትምህርት የሚሰጥበትም መንገድ አንደኛው በሌላኛው የበላይነት ለማሳየት ሳይሆን ወደ ቅኑ መልካም ጎዳና እንዲመለሱና ሊያደርጋቸው በሚያስችል የውይይት ስልት መካሄድ እንደሚኖርበት ያስቀምጣል፡፡

የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ፡፡ (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ፣ በርሱም ምንንም ላናጋራ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው፤ በላቸው፡፡ እምቢ ቢሉም፡- እኛ ሙስሊሞች መኾናችንን መስክሩ በሏቸው፡፡ አል ኢምራን-64

10. ሰዎች የኢስላምን ሃይማኖት በሚቀበሉበትና በሚቀላቀሉበት ጊዜ ከባድ፣ አስቸጋሪ እና ልዩ የሆኑ ሃይማኖቱን የመቀበል ስነስርዓት አላደረገም፡፡ ሃይማኖቱን ለመቀበል ልዩ ስፍራ በመሄድና የምስክር ቃሉንም በተሰበሰቡ ምእመናን ፊት እንዲደረግ አያስገድድም፡፡ በአጠቃላይ ሃይማኖቱን የሚቀበሉ ሰዎች በፊት ከሚያደርጉት የተለየ ተግባር እንዲፈጽሙ አይጠየቁም፡፡ የሚያደርጉት ነገር ቢኖር ባሉበት ሁኔታና ቦታ ሆነው ለንግግር በጣም ቀላል ትውጉማቸው ግን እጅግ የገዘፉ ቃላቶችን የምስክርነት ቃሉን በመስጠት ብቻ አባል ይሆናሉ፡፡ ይህ የኢስላም ገፅታ ሰው ከፈጣሪው ጋር ያለማንም ጣልቃ ገብነት ግንኙነት የሚፈጥርበት መንገድ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ከአላህ ውጪ በዚህ አለም ሊመለክና ሊገዙት የሚገባው ጌታ የለም ሙሃመድ ደግሞ የአላህ ባሪያና ለሰው ልጆች ከፈጣሪ ዘንድ የተላከ መልዕክተኛ ነው ብሎ በመናገር እና የምስክር ቃል በመስጠት ብቻ የሃይማኖቱ ተከታይ ለመሆን በቂ መስፈርት ነው፡፡ ይህን የምስክርነት ቃል የሰጠ ሰው ከኢስላም ውጪ ካሉ ሃይማኖቶች አመለካከትና እምነት ነፃ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡በማንኛውም ሙስሊሞች ላይ ያለው መብትና ግዴታም በዚህም ሰው ይኖራል፡፡

11. ከአስገራሚ የኢስላም አስተምህሮቶች ውስጥ ወደ ሃይማኖቱ የሚቀላቀሉ ሰዎች እስልምናን ከመቀበላቸው በፊት የሰሯቸውን ሃጢያት ይምራል፡፡ አላህ ይላል ፡- “ለነዚያ ለካዱት በላቸው፡- ቢከለከሉ ለእነሱ በእርግጥ ያለፈውን (ሥራ) ምሕረት ይደረግላቸዋል፡፡ (ወደ መጋደል) ቢመለሱም (እናጠፋቸዋለን)፡፡ የቀድሞዎቹ ሕዝቦች ልማድ በእርግጥ አልፋለችና፡፡ ” የአላህ መልዕክተኛም “ኢስላም ከመስለም በፊት ያለውን ሃጥያት ሁሉ ያብሳል” በማለት ጠቅሰዋል፡፡ ከወንጀል ተፀፅቶ መመለስ ከፀፀቱ በፊት የተሰሩ ወንጀሎችን ያብሳል”

12. ኢስላም ሰዎች እስልምና ከመቀበላቸው በፊት ይሰሩት የነበረውን መልካም ተግባር ከሰለሙ በኋላም ለሰሩት ስራ ሁለት ጊዜ ምንዳ እንደሚከፍላቸው ያስተምራል፡፡ ሃኪም ኢብኑ ሂዛም እንዲህ ይላል (ረ.ዐ) "የአላህ መልዕክተኛን ጠየቅኳቸው፡፡ ከእስልምና በፊት ስሰራቸው የነበሩ መልካም ነገሮች እንደመመፅወት፣ ባሪያ ነፃ ማውጣትን፣ ዝምድናን መቀጠልን የመሳሰሉ ከፈጣሪ ዘንድ ምንዳ ይከፈለኛልን ብሎ ጠየቃቸው" የአላህ ነብይም "ከመልካም ስራዎችህ ጋር ነው አብረህ የሰለምከው" አሉት ቡኻሪ የዘገቡት

13. ከሌሎች መለኮታዊ ሃይማኖት ወጥተው ኢስላምን የሚቀበሉ ሰዎች ሁለት ጊዜ ምንዳ ይከፈላቸዋል አንደኛው ከነቢዩ በፊት በተላኩ የአላህ መልዕክተኞች በማመናቸው ሁለተኛ ደግሞ የሙሃመድን ተልዕኮ በመቀበላቸው ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል ፡-

እነዚያ ከእርሱ በፊት መጽሐፍን የሰጠናቸው እነርሱ በእርሱ ያምናሉ፡፡ በእነሱ ላይ በሚነበብላቸውም ጊዜ «በእርሱ አምነናል፡፡ እርሱ ከጌታችን የኾነ እውነት ነው፡፡ እኛ ከርሱ በፊት ሙስሊሞች ነበርን» ይላሉ፡፡ እነዚያ በመታገሳቸው ዋጋቸውን ሁለት ጊዜ ይስሰጣሉ፡፡ ክፉውንም ነገር በበጎ ምግባር ይገፈትራሉ፡፡ ከሰጠናቸውም ሲሳይ ይለግሳሉ፡ቀሰሰ 52-54

## የእስልምና ሃይማኖት ሙስሊም ካልሆኑ ወገኖች ጋር ያለው የህይወት መስተጋብር

ኢስላም ሙስሊም ካልሆኑ ወገኖች ጋር ሲኖረ የሚገባውን የህይወት መስተጋብር ከመመልከታችን በፊት መግቢያ ይሆነን ዘንድ ሲዊስ ፑንግ የሚባል የምስራቁን አለም እምነት ባህልና ልምድ የሚያጠናው ሰው (Orientalist) የተናገረውን እንመልከት፡፡ ይህ ሰው ምን ይላል፡ "ምዕራቡ አለም ከኢስላማዊ ስልጣኔ ሊማራቸው ከሚገቡ ብዙ ነገሮች ውስጥ አንዱ አረቦች ነገሮችን የማቅለልና ምቹ የማድረግ ባህላቸውን ነው፡፡" (ኡንዙሩል አረብ ወል አውሮፓ ከሚል መጽሃፍ የተወሰደ)

1. ኢስላም ሙስሊም ካልሆኑ ወገኖች ጋር ማንኛውንም አይነት ገንዘብ ነክ የሆኑ ነገሮችን አብሮ መስራት ፈቅዷል፡፡ ንግድን፣ የሽርክና ስራ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡ ይህም የሚሆነው ከሸሪዓ ማዕቀፍ ጋር ተስማሚ በሆነ መልኩና ሁለቱንም አካላት ለችግር የማይዳርግና መብቶቻቸውን በሚያስጠብቅ ሁኔታ መሆን አለበት፡፡ የንግድ ስምምነታቸውም በሁለቱ አካላት መልካም ፍቃደኝነትና ውዴታ እንዲሁም የተስማሙበት ጉዳይ ሁለቱም አካላት ጠንቅቀው ማወቅና መረዳት ይኖርባቸዋል፡፡

   ከእናታችን አኢሻ እንደተነገረው (ረ.ዐ) "የአላህ መልዕክተኛ ካፖርታቸውን በማስያዝ ምግብ ገዝተዋል" ኢስላም የግብይት ተግባርን ጉዳት የሚያስከትሉ ነገሮች እንደ አራጣ ቁማር ማሞኘትን ይመስል ከዛ ውጭ በንግድ አብሮ መኗኗር አይከለክልም፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች ማህበረሰብን ለጉዳት የሚዳርጉ ስለሆኑ ሙስሊም ካልሆኑ ወገኖች ጋር ብቻ ሳይሆን በሙስሊሞች መሃከልም የተከለከሉ ናቸው፡፡ አላህ ይላል፡

   እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አራጣን የተነባበሩ እጥፎች ሲኾኑ አትብሉ፡፡ ትድኑም ዘንድ አላህን ፍሩ፡ ኢምራን 130፡፡ በሌላው የቁርዓን አንቀፅ አላህ እንዲህ ይላል፡

   እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ ቁማርም ጣዖታትም አዝላምም ከሰይጣን ሥራ የኾኑ እርኩስ ብቻ ናቸው፡፡ (እርኩስን) ራቁትም ልትድኑ ይከጀላልና፡፡ ማኢዳህ 90-91

2. ኢስላም ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች አምልኮ የሚፈፅሙባቸው ቦታች ላይ መስገድ ይፈቅዳል፡ ፡ አባሙሳ ዲሚሽቅ (ሶሪያ) ውስጥ ነህያ ተብሎ በሚጠራ የአምልኮ ስፍራ ላይ ሶላት መስገዳቸው ተነግሯል፡፡ ሙስሊም ባልሆኑ ወገኖች የአምልኮ ስፍራ ፎቶግራፍና ሃውልት ባለበት ቦታ ላይ ለመስገድ ሌላ አማራጭ ቦታ እስካልተገኘ ድረስ የተጠላ ከመሆኑ ጋር መስገድ ይፈቀዳል ፡፡ ኡመር አንድ የክርስትና እምነት ተከታይ ለሆነ ሰው እንዲህ አሉት "እኛ ወደ እናንተ ማምለኪያ ስፍራ የማንመጣው በስእላ ስእሎችና ሃውልቶቻቻችሁ ምክንያት ነው፡፡
3. ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች የተለየ ተልዕኮ እስከሌላቸው ድረስ መስጊድ እንዲገቡ ኢስላም ይፈቅዳል፡፡ የመካ አጥር ጊቢ ውስጥ ሲቀር፡፡

የአላህ መልዕክተኛ ሙስሊም ያልሆኑ ልኡካንን መዲና በሚገኘው መስጂዳቸው ውስጥ ይቀበሉና ያስተናግዱ ነበር፡፡ መስጂድ ከመግባት አልከለከሏቸውም፡፡ እንዲያውም የአላህ መልዕክተኛ ሲማም ኢብኑ አሳልን ከመስለሙ በፊት መዲና መስጂድ ውስጥ አስረውታል፡፡ (ረ.ዐ)

4. ኢስላም ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች ሲታመሙ መጠየቅ፣ ይሻላቸው ዘንድ ፈጣሪን መለመን ይፈቅዳል ከአነሰ እንደተናገረው (ረ.ዐ) እንዲህ አለ፡
   "አንድ ነቢዩን የሚያገለግል አይሁዳዊ ልጅ ነበር፡፡ ታመመና ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሊጠይቁት መጡ፡ ፡ "ስለም" አሉት ይህ ልጅ አጠገቡ ወዳለው አባቱ ተመለከተ፡፡ አባቱም የቃሲም አባት የሚሉህን ተቀበል አለው፡፤ልጁም ኢስላምን ተቀበለ፡፡ ነብዩ ይህን ልጅ ከእሳት ላወጣው ጌታዬ ምስጋና ይግባው እያሉ ከቤት ወጡ" ቡኻሪ
5. ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች ሲሞቱ ለሞተባቸው ሰዎች ማስተዛዘን እና ማፅናናት ኢስላም ይፈቅዳል፡፡ አቢ ሁረይራህ ከነብዩ እንደተናገረው "እናቴ ምህረት ታገኝ ዘንድ ጌታዬን እንድለምንላት ፈቃድ ጠየቅኩት አልፈቀደልኝም መቃብሯን እንድጎበኝ ፈቃድ ጠየቅኩኝ ጌታዬም ፈቀደልኝ" አሉ የአላህ መልእክተኛ ሙስሊም ዘግበውታል፡፡
6. ኢስላም ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች ሙስሊሞችን የሚዋጉ እስካልሆኑ ድረስ መርዳትና ስጦታ መስጠት ፈቅዷል፡፡ አብደላህ ኢብኑ አምር  በአንድ ወቅት ቤተሰቡ ውስጥ ፍየል ታርዶ ጠበቀው፡፡ ልክ ሲመጣ ለመሆኑ ይሁዲ ለሆነው ጎረቤታችን ሰጥታችኋል በማለት ደጋግመው ጠየቁ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ሲናገሩ ሰምቻለሁም "መልአኩ ጅብሪል የጎረቤትን ጉዳይ አደራ አደራ በማለት አልተወገደም አደራው ከመብዛቱ የተነሳ አላህ ለጎረቤት የመውረስ መብት ሊሰጣቸው ነው እንዴ ብዬ እስከምጠራጠር ድረስ"
   እንደውም ከዚህ በላይም ችግረኛ ለሆኑ ሙስሊሞች ብቻ የሚሰጠውን ዘካን እንኳን ልቦቻቸውም (በእስልምና) ለሚለማመዱት እንደሚሰጥ የስተምራል፡፡ ይሄ የሚሆነው ዘካ ለነሱ በመሰጠታቸው ለሙስሊሞች ጠቀሜታ የሚያስገኝና መጥፎ ነገሮን የሚያስወግድ ሆኖ  ወይም ወደ ኢስላም እንዲመጡ ሰበብ ይሆናል ተብሎ ሲታመንበት ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡

"ግዴታ ምጽዋቶች (የሚከፈሉት) ለድኾች፣ ለምስኪኖችም፣ በርሷም ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች፣ ልቦቻቸውም (በእስልምና) ለሚለማመዱት፣ ጫንቃዎችንም (በባርነት ተገዢዎችን) ነጻ በማውጣት፣ በባለ ዕዳዎችም፣ በአላህ መንገድም በሚሠሩ፣ በመንገደኛም ብቻ ነው፡፡ ከአላህ የተደነገገች ግዴታ ናት፡፡ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው፡፡ ተውባ 60

ኡመር (ረ.ዐ) ከመስፅሃፍ ባለቤቶች ውስጥ አንድ ደካማ የሆኑ ሰው ሲለምኑ ተመለከተና ሰውዬውን ወደ ሙስሊሞች ንብረት ግምጃ ቤት ጠባቂ ላከውና ጠባቂውንም እንዲህ አሉው "ይሄንና ይሄን የመሰሉ ሰዎች እያየህ ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው የሚበቃቸውን ያህል ከሙስሊሞች ንብረት ግምጃ ቤት ወጪ አድርገህ ስጣቸው አለው፡፡ አላህ እንዲህ ብሎናል በማለት ""ግዴታ ምጽዋቶች (የሚከፈሉት) ለድኾች፣ ለምስኪኖችም… ተወባ 60) የሚለውን የቁርዓን አንቀፅ ካነበቡ በኋላ በቁርዓኑ ውስጥ ፋቀራ ተብለው የተጠቀሱት ሙስሊሞችን ሲሆን መሳኪን ተብለው የተጠቀሱት ደግሞ የመፅሃፉ ባልተቤቶችን ነው በማለት ኡመር (ረዐ) ገልጸዋል፡፡

7. ኢስላም ሙስሊሞችን ሙስሊም ያልሆኑ ዘመዶቻቸውን መቀጠል እንደሚገባቸው ያስገነዝባል፡፡ አስማዕ ቢንት አቡከከር እንዲህ አለች "በነብዩ ዘመን እናቴን ከረጅም ጊዜ በኋላ ሙሽሪክ ሆና አገኘኋት፡፡ ነብዩም እንዲፈርዱኝ እንዲህ በማለት ጠየኳቸው እናቴ የኔን ዝምድና መቀጠል ትፈልጋለች እኔ ከሷ ጋር ዝምድናዬን መቀጠል እችላለሁ አልኳቸው፡፡ አዎ ትችያለሽ አሉኝ" ቡኻሪ
8. ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖችን በመመገቢያ እቃዎቻቸው መጠቀም ልብሳቸውን መልበስ በኢስላም ከተከለከሉ ነገሮች በቀር፤ ከብርና ከወርቅ የተሰሩ ነገሮች፣ የአሳማ ቆዳ እና የውሻ ቆዳ የመሳሰሉት ሲቀር መጠቀም የተፈቀደ ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች ስለተጠቀሙባቸው ብቻ ሳይሆን ሙስሊሞችም እንዲጠቀሙባቸው አይፈቀድምና ነው፡፡ ይህን በማስመልከት አቢ ሰዕለበተል አልኸሸኒ እንዲህ ብሎ ጠየቀ "እኛ የመፅሃፉ ባልተቤቶች በሚኖሩበት ሃገር ነው የምንኖረው፡፡ በእነሱ እቃ መመገብ እንችላለን?" ነብዩም "ሌላ አማራጭ ካገኛችሁ በእነሱ እቃ ላይ አትመገቡ ማግኘት ካልቻላችሁ ግን አጥባችሁ ተመገቡ" ብለው መለሱ፡፡
9. ኢስላም ሙስሊም ካልሆኑ ወገኖች ሚስት ማግባትን ፈቅዷል ሃላል የሆኑ ምግባቸውን መመገብ እንደፈቀደ ሁሉ፡፡ አላህ ይላል፡

ዛሬ መልካሞች ሁሉ ለናንተ ተፈቀዱ፡፡ የእነዚያም መጽሐፍን የተሰጡት ሰዎች ምግብ (ያረዱት) ለእናንተ የተፈቀደ ነው፡፡ ምግባችሁም ለነሱ የተፈቀደ ነው፡፡ ከምእመናት ጥብቆቹም ከእነዚያ ከእናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡት ሴቶች ጥብቆቹም፤ ዘማዊዎችና (ዝሙተኞች) የምስጢር ወዳጅ ያዢዎች ሳትኾኑ ጥብቆች ኾናችሁ መህሮቻቸውን በሰጣችኋቸው ጊዜ (ልታገቡዋቸው የተፈቀዱ ናቸው)፡፡ማኢዳ 5

10. ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች ኢስላምን ከመቀበላቸው በፊት የነበራቸው ትዳር ኢስላምን ከተቀበሉ በኋላም እንዲፀና ኢስላም ያፀድቃል፡፡ ጊላን ኢብኑ ሰለመህ አሰቀፋይ አስር ሚስቶች ኖሮት ኢስላምን ተቀበለ፡፡ ነብዩም "ከአስሩ አራቱን ምረጥ" አሉት ፡፤ቲርሚዚይ

11.ኢስላም የመፅሃፍ ባልተቤቶችን የአላህ ስም ጠርተው እስካረዱ ድረስ የታረደውን እንስሳ ስጋ መብላት ፈቅዷል፡አላህ ይላል "በእርሱም ላይ የአላህ ስም ካልተጠራበት ነገር አትብሉ፡፡ እርሱም በእርግጥ አመጽ ነው፡፡ ሰይጣናትም ወደ ወዳጆቻቸው (በክትን በመብላት) ይከራከሯችሁ ዘንድ ያሾከሹካሉ፡፡ ብትታዘዙዋቸውም እናንተ በእርግጥ አጋሪዎች ናችሁ፡፡

12.ኢስላም ሙስሊም ካልሆኑ ወገኖች ጋር በመልካም ጉርብትና እንድንኗኗር፣ ሰላምና መረጋጋታቸውን እንድንጠብቅ ያዘናል፡፡ አላህ ይላል፡-

"ከአጋሪዎችም አንዱ ጥገኝነትን ቢጠይቅ የአላህን ቃል ይሰማ ዘንድ አስጠጋው፡፡ ከዚያም ወደ መጠበቂያው ስፍራ አድርሰው፡፡ ይህ እነሱ የማያውቁ ሕዝቦች በመኾናቸው ነው፡፡"

13.አንድ ሙስሊም ያልሆነ ግለሰብ በሙስሊም ላይ ወንጀል ፈፅሞ ሲገኝ በሙስሊሞች ሃገር ባለው የፍርድ ስነስርዓት ይዳኛል፡፡ ወንጀል ለተፈፀመባቸው ቤተሰቦች ለተፈፀመው ወንጀል ወይ ይቅርታ እንዲያደርጉ ወይም ካሳ እንዲከፈላቸው ወይንም ለተፈፀመው ወንጀል ተመጣታኝ ቅጣት ተግባራዊ እንዲደረግ ምርጫ ይሰጣቸዋል፡፡አላህ ይላል፡

በእነርሱም ላይ በውስጧ «ነፍስ በነፍስ ዓይንም በዓይን አፍንጫም በአፍንጫ ጆሮም በጆሮ ጥርስም በጥርስ (ይያዛል)፡፡» ቁስሎችንም ማመሳሰል አለባቸው ማለትን ጻፍን፡፡ በእርሱም የመጸወተ (የማረ) ሰው እርሱ ለርሱ (ለሠራው ኃጢአት) ማስተሰሪያ ነው፡፡ አላህም ባወረደው ነገር የማይፈርድ ሰው፤ እነዚያ በደለኞቹ እነርሱ ናቸው፡፡ .ማኢዳህ 45

14.ኢስላም ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖችን ሃይማኖት መስደብም ፣ማነወር፣ ማጉድፍ የሚከለክል ሃይማኖት ነው፡፡አላህ ይላል፡

እነዚያንም ከአላህ ሌላ የሚገዙዋቸውን (ጣዖታትን) አትስደቡ፡፡ ድንበርን በማለፍ ያለዕውቀት አላህን ይሰድቡሉና፡፡ እንደዚሁ ለሕዝቦች ሁሉ ሥራቸውን ደግ አስመሰልንላቸው፡፡ ከዚያም መመለሻቸው ወደ ጌታቸው ነው፡፡ ይሠሩት የነበሩትንም ሁሉ ይነግራቸዋል፡፡ አንአም 108

15.ኢስላም ሙስሊም ካልሆኑ ወገኖች ጋር የሚደረግ ስምምነቶችን ተግባራዊ እንዲደረጉ ያስገድዳል፡፡ አላህ ይላል "እናንተ ምዕመናን ስምምነቶቻችሁን ሙሉ"

ቃልኪዳን እና ቀጠሮን ማክበር እነሱንም ማታለል በጥብቅ እርም የተደረጉ ነገሮች ናቸው፡፡ አላህ ይላል "ቃል ኪዳናችሁን ሙሉ ቃልኪዳን የሚያፈርስ ሰው ተጠያቂ ነው"

16.ኢስላም ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖችን ሃብት ህይወት እና ክብር እንዲከበርና እንዲጠበቅ አድርጓል፡፡እንዲሁም እነሱን መበደል መብታቸውን ማጉደል እንዲሁም ማህበራዊ ግንኙነታቸውንና መስተጋብራቸውን ማበላሸት የተከለከለ ነው፡፡ አላህ ይላል፡

ከእነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካላወጡዋችሁ (ከሓዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደእነርሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም፡፡ አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና፡፡

17. "አላህ እናንተን የማይዋጓችሁና ከሃገራችሁ የማያስወጧችሁ እስከሆኑ ድረስ ለነሱ መልካም እንድትሆኑና ሚዛናዊ እንድትሆኑ አላህ አይከለክላችሁም አላህም ሚዛናዊ የሆኑትን ይወዳል፡ ፡ (ሙምተሂና 8)

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ይላሉ " ንቁ በሙስሊሞች ግዛት ውስጥ በቃል ኪዳን የሚኖርን ሰው የበደለ፣ መብቱን ያጎደለ ፣ አቅሙ መሸከም ከሚችለው በላይ ያስገደደው ወይም ነፍሱ ደስተኛ ሳትሆን አንዳች ነገርን ከሱ የወሰደ ሰው ሰዎች ፈጣሪ ዘንድ ለፍርድ በሚቆሙ ቀን እኔ ነኝ ምስክሩ" ሱነን አቡዳውድ

በሌላ ንግግራቸው " በሙስሊሞች ግዛት ውስጥ በቃል ኪዳን የሚኖርን ሰው የገደለ ሰው የጀነትን ሽታ አያሸትም። የጀነት ሽታ የአርባ ዓመት ጉዞ ያህል እርቀት ላይ ትገኛለች" ቡኻሪ

18. በሙስሊሞች ሃገር ውስጥ ግብር በመክፈል የሚኖሩ ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች በኢስላማዊ አስተዳደር ጥላ ስር እስካሉ ድረስ ማህበራዊ ዋስትና ይሰጣቸዋል። ። የሙእሚኖች መሪ የሆኑት ሁለተኛው ኸሊፋ ኡመር ኢብኑል ኸጣብ   ትልቅ ሽማግሌ ሰዎችን ሲለምን በተመለከቱ ጊዜ እንዳደረጉት። ዑመር ስለሰውዬው ጠየቁ። ሰውየውም ግብር ከሚከፍሉ የህብረተሰብ አካል አንዱ መሆኑን ተገነዘበ። እንዲህም አለ "በወጣትነትን ዘመን ጂዝያን ተቀበልንህ ግን የሚገባህን መብት አልሰጠንህም በእርጅናህም ዘመን ያለእንክብካቤ ጣልንህ ካሉት በኋላ እጁን ይዘው ወደ ቤታቸው በመውሰድ ምግብና ልብስ ከሰጡት በኋላ የሙስሊሞች ንብረት ግምጃ ቤት ልከው ጠባቂውን ይሄን ሰው እና አምሳያዎቹን  ተመልክተህ ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው የሚበቃቸውን ያህል ከግምጃ ቤቱ ስጣቸው" አሉት

አላህ ይላል "ኢነመሰደቀቱ ለልፉቃራኢ መሰኪነ ..." የሚለው አንቀፅ በማንበብ  ፉቀራዕ ማለት ሙስሊሞችን ነው መሳኪን ተብለው የተጠቀሱት ደግሞ የመፅሃፉ ባልተቤቶችን ነው አሉት፡ ፡

19. ኢስላም የእዝነትና የፍቅር ሃይማኖት በመሆኑ የበቀልና የፀብ ሃይማኖት ስላልሆነ ሙስሊም ያልሆኑ የጠላት ወገኖች ጋር እንኳን  በተቻለ መጠን  በይቅርባይነትና በመልካም መኗኗርን ያዛል።ኢስላም ነው። አላህ ይላል፡

ከእነርሱም ይቅርታ አድርግ እለፋቸውም፡፡ አላህ መልካም ሠሪዎችን ይወዳልና፡፡ማኢዳ 13

**በሌላው የቁርዓን አንቀጽ አላህ እንዲህ ይላል፡**

ከመጽሐፉ ባለቤቶች ብዙዎች እውነቱ ከተገለጸላቸው በኋላ ከነፍሶቻቸው በኾነው ምቀኝነት ከእምነታችሁ በኋላ ከሓዲዎች አድርገው ሊመልሱዋችሁ ተመኙ፡፡ አላህም ትዕዛዙን እስከሚያመጣ ድረስ ይቅርታ አድርጉ፤ እለፏቸውም፡፡ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ከሃሊ ነውና፡፡ "በቀራህ 109" **በሌላው አንቀፅ ደግሞ፡**

"ለእነዚያ ለአመኑት ሰዎች (ምሕረት አድርጉ) በላቸው፡፡ ለእነዚያ የአላህን ቀኖች ለማይፈሩት ይምራሉና፡ ፡ ሕዝቦችን ይሠሩት በነበሩት ነገር ይመነዳ ዘንድ (ምሕረት አድርጉ በላቸው)፡፡ አልጃሲያህ 14"

20. *ኢስላም ሙስሊም ላልሆኑ ወገኖች በመልካም መንገድ ጥሪ ሊደረገረላቸው እንደሚገባ ያስተምራል።የተስፋና የአላህን ምህረት የሚጎናፀፉበትን መንገድ በማስታወስ መንገዱን ሁሉ ክፍት አድርጓል። አላህ ይላል፡*

ለነዚያ ለካዱት በላቸው፡- ቢከለከሉ ለእነሱ በእርግጥ ያለፈውን (ሥራ) ምሕረት ይደረግላቸዋል፡፡ (ወደ መጋደል) ቢመለሱም (እናጠፋቸዋለን)፡፡ የቀድሞዎቹ ሕዝቦች ልማድ በእርግጥ አልፋለችና፡፡ አልአንፋል 38"

21. *ኢስላም ገርና ምቹ የመሆኑ ሚስጥር ለሰው ልጆች መልካም ነገር እንዲገጥማቸውና እንዲያገኙ መውደድ መመኘት የእምነት ምልክት ነው። እስላም የሰላምና የፍቅር ሃይማኖት ነውና። የአላህ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ይላሉ*

*"አንተ ያ አቡሁረይራህ ብትሰራቸውም ብትተዋቸውም ምንም ልዩነት የማያመጡ ነገሮች ከመስራት ተቆጠብ ከሰዎች ሁሉ በላጭ አላህን የሚገዛ ባሪያ ትሆናለህ በራስህ፤ ባለህ ነገር ተብቃቃ ሰዎች ዘንድ የተመሰገንክ ትሆናለህ፤ ለራስህ የምትወደውን ነገር ለሰዎች ውደድ ጥሩ አማኝ ትሆናለህ፤ከጎረቤትህ ጋር ጉርብትናህን አሳምር ሰላም ትሆናለህ፤ መሳቅን ቀንስ አብዝቶ መሳቅ ቀልብን ይገድላል።*

## የኢስላም አምልኮአዊ ተግባራት ለሰዎች ያላቸው ተስማሚነት

ኢስላማዊ ግዴታ የሆኑም ሆነ ያልሆኑ የአምልኮ ስነስርዓቶች ለሰዎች ቀላልና ገር በሆኑ መርህ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ይሄ ኢስላምን ከሌሎች ሃይማኖቶች ለየት የሚያደርገው ባህሪው ነው፡ :

ይህ የኢስላም ባህሪ ሁሉም ሙስሊም በአምልኮ ስነስርዓቶች ውስጥ ባለው መንፈሳዊ ጥንካሬ፣ አቅምና ችሎታው ልክ ከፈጣሪው ጋር በሚኖረው ግንኙነት ልክ የመንፈስ እርካታ እና መረጋጋት እንዲጎናፀፉ ለማስመቸት ነው" አላህ ይላል፡

"(እነሱም) እነዚያ ያመኑ ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው፡፡ ንቁ! አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ፡፡ አልረዕድ 28

በአምልኮአዊ ስነስርዓቱ ውስጥ የሰው ልጅ አቅም ሊሸከመው ከሚችለው በላይ አይገደድም፡፡ የአላህ ነብይ እንዲህ ይላሉ "አደራችሁን በአቅማችሁ ልክ የሆነን ነገር በመስራት አላህ አይሰለችም እናንተ እስከምትሰለቹ ድረስ፡፡"

ከዚህ በመቀጠል ኢስላማዊ የአምልኮ ስነስርዓቶች ምን ያህል ለሰው ልጆች ምቹ ገርና ከሰው ልጆች ተፈጥሮ ጋር የሚስማሙ መሆናቸውን እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

1. ኢስላም የሚያዛቸው ትእዛዞች እና የአምልኮ ስነስርዓቶች ከተፈጥሮ ጋር የተስማሙ እና የሰው ልጅ የመፈፀም አቅምን ያገናዘቡ ናቸው፡፡ ሰውን ከአቅሙ በላይ አያስገድድም፡፡ ከሰው ከተፈጥሮ ጋር የሚቃረን ነገር እንዲፈፅም አያዝም፡፡እንዲያውም አላህን በማምለክ እንኳን ቢሆን ሰዎችን ለከፋ ችግር የሚዳርጉ ተግባራትን መፈፀም ተቀባይነት የለውም፡፡አነስ (ረ.ዐ) እንደተነገረው ከአላህ መልዕክተኛ እንደተናገረው ነብዩ አንድ ሽማግሌ አባት ሁለት ልጆቹን ተሸክመውት ሲያንቀሳቅሱት ተመለከቱት፡፡ "ይሄ ምንድነው ብለው ጠየቋቸው፡፡ ልጆቹም አባታችን በእግሩ መሄድን ስለት ገብቶ ነው" አሉት፡፡ ነብዩም " አላህ ከእንደዚህ አይነቱ ነፍሱን ከሚቀጣ ሰው የጠራ ነው" ብለው እግሩ እንዲሄድ አዘዙት፡፡ ቡኻሪ እንደዘገቡት
2. አላህ ባሮቹ በበሽታም ይሁን በጉዞ ምክንያት መስራት ያልቻሉትን መልካም ስራ በደህናው ጊዜ እና ጉዞ ላይ ባልሆኑበት ጊዜ ሲሰሩት የነበረውን ስራ ምንዳ ይከፍላቸዋል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ "አንድ ሰው በሚታመምበት ወይንም ከሚኖርበት አካባቢ ርቆ ሲሄድ ጤነኛ በነበረበት ጊዜና መንገደኛ ባልሆነበት ጊዜ ይሰራቸው የነበሩ ስራዎችን ምንዳ ይመዘግብለታል፡፡ እንደውም የኢስላም ምቹነትና ገራገርነቱ አምልኮአዊ የሆኑ ጉዳዮች ከፈጣሪ ዘንድ ከፍ ያለ ምንዳ የሚያስገኙት ስራዎችን በማክበድ ሳይሆን በማቅለል ላይ ነው፡፡ የአላህ

መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ “አላህሰዎች ከወንጀል ሙሉ በሙሉ ሲርቁ እንደሚወደው ሁሉ ከባድ ከባድ የሆኑትን ሳይሆን እንደ ማቅለያ የተደረጉት ስራዎች ሲሰሩ በጣም ይወዳል፡፡

3. አምልኮአዊ ተግባራት እና ትእዛዞች አንዳንዴ መፈፀም ከሚገባቸው መንገድ በታች እንደ ሁኔታው ሲቀነሱ አለበለዚያ ሊተው ይችላሉ፡፡

በዚህ ክፍል ያሉ ንዑስ ጉዳዮች እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡

## 1. በንፅህና (ጠሃራ) ዙሪያ የኢስላም ያለው ምቹነት እና ቀላልነት

በኢስላም ውስጥ ግላዊና አካባቢዊ ንፅህና ለአብዛኛዎቹ የአምልኮ ስነስርዓቶች ፈጣሪ ዘንድ ለተቀባይነታቸው መሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ውሃን ብንመለከት ማንኛውም ሙስሊም በቀንና ሌሊት የሚገኙ አምስት ስግደቶችን ለማከናወን፤ ከነሱ ውጪ ያሉትንም ግዴታ ያልሆኑ ስግደቶች ለመስገድ፤ ለአብዛኛው ሃይማኖታዊ ድርጊቶች እንደ ጁምዓ እና በበዓለት ቀን የሚደረጉ ስግደቶችን ማከናወንን ይመስል ከጀናባ መንፃትና የግል ንፅህናን (ጡሃራን) መጠበቅ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

ነገር ግን በውሃ የግል ንፅህናን (ጡሃራ) የመጠበቅ ያለው አስፈላጊነት በከፍተኛ ሁኔታ አግዝፎ ከመመልከት የተነሳ ሰዎች ላልተፈለገ ችግርና ጭንቀት ሲዳረጉ ይስተዋላል፡፡ ከዚያም አልፎ ተርፎ ጡሃራ ዋናውን የኢባዳ ክፍል ለማከናወን አጋዥ የሆነ ተግባር ሆኖ ሳለ ሰዎች ለዋና ዋና የአምልኮ ስነስርዓቶች ከሚሰጡት ቦታ በላይ ለጡሃራ የሚሰጡት ቦታ ላቅ ያለ ነው፡፡ በንፅህና ጉዳዮችች ላይ አብዝቶ በመጠመድ ዋና ዋና ኢባዳዎች ላይ ከመድረሳቸው በፊት የመድከምና የመሰላቸት ባህሪ ይስተዋልባቸዋል፡፡

ኢስላም የአምልኮ ተግባራትን ለመፈፀም መደረግ ያለባቸው የንፅህና ስነስርዓት ገጽታ በተመለከተ ምንያህል ቀላልና የሰዎችን ምቾት በሚጠብቁ መልክ እንዳስቀመጠ ከዚህ በታች መመልከት ይቻላል፡፡

1. ኢስላም ውሃን በመሰረቱ ከየትም ይምጣ ከየትም ይገኝ ጣዕሙ መልኩና ሽታው እስካልተቀየረ ጊዜ ድረስ ንፅህናውን ይቀበላል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፡፡“ውሃን ምንም አይነት ነገር ንፅህናውን አያሳጣውም መልኩ ሽታው እና ጣዕሙ እስካልተቀየረ ጊዜ ድረስ፡፡
2. የቤት እንስሳት ጠጥተውት የተረፈን ውሃ ንፁህ እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡ስለዚህም ለመጠጥና ለንፅህና አገልግሎት መተጠቀም ይቻላል፡፡ ኢብኑ አቢ ቀታዳህ አገልጋይ የነበረቸው ከብሻ ከዕብ ቢንት ማሊክ እንደተናገረችው በአንድ ወቅት አባ ቀታዳህ ወደ ብቤቷ ገብቶ ዉዱ ማድረጊያ ውሃ አቀረብኩለት፡፡ከውዱዕ ማድረጊያው ውሃ ለመጠታት ድመት ስትመጣ እሱም ውሃውን የያዘውን እቃ አስጠጋላትና ጠጣች፡፡አባ ቀታዳህም እሱን በአግርሞት ስመለከተው

አየኝና “የወንድሜ ልጅ ተገረምሽ እንዴ” አለኝ አለች፡፡አዎን አልኩት፡፡እሱም አለ፡፤ የአላህ መልዕክተኛ ድመት የምትነጅስ አይደለችም፡፡እሷ በእናንተ መሃከል የምትዟዟር እንስሳ ናት ብለው ተናግረዋል አለኝ ብላ ተናገረች፡፡በሰሂሀይን ውስጥ የተገኘ

3. ውሃ በማይገኝበት ጊዜ ወይንም ውሃን ለመጠቀም አስቸጋሪ ሁኔታ ሲፈጠር ውሃ ማጣትን ፣ በበሽታ ወይንም በቁስልን፣ በከፍተኛ ብርድ ምክንያት በውሃ ዉዱ ማድረግ ሳይቻል ሲቀር ወይንም ወይንም የውሃን መጠን ለመጠጥና ለሌሎች መሰል ተግባራት ለመፈፀም በቂ ሆኖ ካልተገኘ በውሃ ፋንታ በአፈር መጠቀም ከፈጣሪ ዘንድ የተሰጠ ማቅለያ ነው፡፡ አላህ ይላል “እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እናንተ የሰከራችሁ ኾናችሁ የምትሉትን ነገር እስከምታውቁ የረከሳችሁም ስትኾኑ መንገድን አላፊዎች ካልኾናችሁ በስተቀር (አካላታችሁን) እስከምትታጠቡ ድረስ ስግደትን አትቅረቡ፡፡ በሽተኞች ወይም በጉዞ ላይ ብትኾኑም፥ ወይንም ከእናንተ አንዱ ከዓይነምድር ቢመጣ፥ ወይንም ሴቶችን ብትነካኩና ውሃን ባታገኙ፣ ንጹሕ የኾነን የምድር ገጽ አስቡ፡፡ ፊቶቻችሁንና እጆቻችሁንም (በርሱ) አብሱ፡፡ አላህ ይቅር ባይ መሓሪ ነውና፡፡
”

4. ውዱዕ በሚደረግበት ጊዜ እግርን በመታጠብ ፋንታ በጫማ ላይና እራስን በማበስ ፋንታ አማይማ ላይ ማበስን ፈቅዷል፡፡ ነገር ግን ቅደመ ሁኔታዎች በአግባቡ መሟላት አለባቸው፡፡ ይህም የሆነው ውዱዕ ባደረጉ ቁጥር በተለይ በብርድ ጊዜ ጫማቸውንና አማይማቸውን በመፍታትና በማሰር እንዳይቸገሩ ሲባል ነው፡ ከጂዕፈር ኢብኒ ዐምር ኢብኒ ኡመያህ አልደረሪ ከአባቱ እንደተናገረው ነብዩ ውዱዕ ሲያደርጉ ጫማቸውና ኢማማቸው ላይ ሲያብሱ ተመለከትኩ” አለ ሰሂህ ኢዝኑ ኹዙይማህ፡፡ኢስላም በሰዎች ላይ ፅንፈኝነትን ማክረርንና ያለ ማቅለልን አጥብቆ ይቃወማል፡፡ ጃቢር እንደተናገረውበአንድ ወቅት ጉዞ ላይ እያለን ከመሃከላችን አንድ ሰው ድንጋይ መትቶትጭንቅላቱን ተፈነከተ፡፡በእንደእያው ሁኔታ እያለ ኢህቲላም ሆነ፡፡ጓደኖቹንም ፡፤” በአፈር መጠቀም እችላለሁ” በማለት ጠየቀ፡፡እነሱም “አንተ በውሃ መታተብ ስለምትችል አፈር መጠቀም አትችልም” አሉት፡፡ይህ ሰው በውሃ ታጠበ፡፡ ጭንቅላቱ ውስጥ ውሃ በመግባቱ ምክንትያት ለሞት ዳረገው፡፡ወደ ነብዩ ስንመለስ ተነገራቸው፡ ፡ ነብዩም “ገደሉት አላህ ይግደላቸውና ማን አለ የማያውቁትን ነገር በጠየቁ ኖሮ፡፡በተሰነመቀው የጭንቅላት ክፍል ላያ በአፈር ማበስና የተቀረውን የሰውነቱን አካል መታጠብ የበቃው ነበር” ብለው ደጋግመው ተናገሩ፡፡

5. ኢስላም በመሬት ላይ አምልኮታዊ ግዴታዎችን ለመፈፀም ይመች ዘንድ በየትኛውም ስፍራ መሬትንመስረቱ ጠሃራ (ንፁህ) አድርጎታል፡፡ ነጃሳ እስካልነካውና  የመፀዳጃ ስፍራ እና የመቃብር ስፍራ እስካልሆነ ድረስ፡፡ ኢስላም ሰዎች እንዳይቸገሩ በማሰብ ሰላትን ጥቂት ስፍራዎች ብቻ ላይ እንዳይፈጸም ከልክሏል፡፡ እንደ ገበያ፤ የአምልኮ ሥፍራዎችን ቦታዎች ይመስል፡፤ነብዩ እንዲህ ይላሉ "ከኔ በፊት ለማንም ያልተሰጡ አምስት ነገሮች ተሰጥቻለሁ" ሁሉም ነብይ ለህዝቦቹ ሲላክ እኔ ለሁሉም ሰው ዘር ተላኩኝ፤ የጦር ምርኮን መውረስ ከኔ በፊት ለማንም አልተፈቀደም፤ ምድር ንፁህ ጥሩ እና የመስገጃ ስፍራ ተደርጎልኛል፡የስግደት ወቅት የደረሰበት ማንኛውም ሰው በደረሰበት ቦታ መስገድ ይችላል፡፡ የጠላት ጦር ለመዋጋት የአንድ ወር ጊዜ ያህል ርቀት ሲቀረው አላህ በጠላቶቹ ላይ ሽብርና ፍራቻ ይለቅባቸዋል፡፡ እንዲሁም ማማለድ ተሰጠኝ"
6. በምንጠቅምባቸው ስፍራዎች ላይ ነጃሳ የሆነ ነገር ሲገኝ ይሄንን ለማንፃት/ጠሃራ ለማድረግ ምንም አይነት አስቸጋሪነት የለውም፡፡ በጣም ቀላል በሆነ መንገድ ከነጃሳው እንዲጠራ ይደረጋል፡፡ነብዩ መስጊድ ውስጥ ገብቶ ሽንቱን ከሸናው ሰውዬ ታሪክ ይህን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ገጠሬ ነብዩ መስጂድ ገብቶ ሽንቱን ሸና፡፡ ሰዎችም በዚህ ድርጊቱ ተጯጯሁበት፡፡ የአላህ መልዕክተኛም "ተዉት ሽንት የነካውን ቦታ ውሃ አምጥታችሁ ድፉበት እኔ የተላኩት ለማግራራት እንጂ ሰውን ለማስጨነቅና፣ ለማስቸገርና ለማደናበር አይደለም" ብለው ለተሰበሰቡት ሰዎች ነገሯቸው፡፡
7. ኢስላም በጠሃራ ላይ ካደረገው ምቹነትና ገርነት አንዱ ስጋቸውና ደማቸው የሚበሉ እንስሳት ደሙ የሚፈስ  እስካልሆነ ድረስ ሽንታቸውና እበታቸው ልብስንም ሆነ ስፍራን የማይነጅሱ ጠሃራ ማድረጉ ነው ፡፡ የግመል ሽንትንና እበትንም አያጠቃልልም፡፡

   ጃቢረ ኢብኑ ሳሙረተ እንደተናገረው አንድ ሰው ነብዩን እንዲህ ብሎ ጠየቃቸው "የፍየልንና የበግ ስጋ ከበላሁ በኋላ ውዱዕ ማድረግ ይጠበቅብኛል?" አለ "ነብዩም ከፈለክ አድርግ ካልፈለክም ተወው" አሉት፡፡ በማስከተልም "የግመል ስጋ ከበላሁ በኋላስ?" ብሎ ጠየቀ፡፡ ነብዩም "የግመል ስጋ ከበላህ ውዱዕ ማድረግ ይኖርብሃል" አሉት፡፡ አሁንም ጠየቀ "በፍየልና በጎች ማደሪያ ቦታ መስገድ እችላለሁ?" ብሎ ጠየቀ፡፡ የአላህ መልዕክተኛም አዎን ብለው መለሱለት፡፡ በስተመጨረሻም "ግመሎች በሚያድሩበት ስፍራስ?" አለ፡፡ ነብዩም እሱ አይቻልም ብለው መለሱለት፡፡

## 2. ኢስላም ስግደትን (ሶላትን) በተመለከተ ለሰዎች ምቹና ቀላል እንዲሆን የተደረገበት ገፅታዎች

ሶላት አንድ ባሪያ ለፈጣሪው ክብር ራሱን ዝቅ የሚያደርግበትና የሚያዋርድበት፤ከፈጣሪው ጋር በማንሾካሾክም በልቡ ውስጥ የፈጣሪን ቅርበት፣ ፍቅርና የፅና እምነት በልቡ ውስጥ እንዲሰርፅና በፈጣሪና በባሪያው መካከል የሚገናኙበት ድልድይ እንዲሆን ከአላህ የተሰጠ ትልቅ ፀጋ ነው፡፡ በእያንዳንዱ ቀንና ሌሊት በሚፈፅሙ አምስት ሶላቶች የሰላት ጥሪ በሚደረግበት ወቅት ባሮች ከአለማዊ ህይወታቸው ለእፍታ ያህል እንዲርቁ በማድረግ በመስጂድ ውስጥ ከፈጣሪያቸው ጋር ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ግንኙነቶችና ቁርኝት የሚፈጥሩበት ነው፡፡ ሶላት ሙስሊሞች እርስበርሳቸው የሚተዋወቁበትን፣ በመካከላቸው ፍቅርና አብሮነት እንዲጎለብት፣ እርስ በርሳቸው ያሉበትን ግለሰባዊ፣ ቤተሰባዊና ማህበራዊ ጉዳዮቻቸውን የሚያነሱበት፣ የሚጠያየቁበት፣ የሚረዳዱበት መድረክም ጭምር ነው፡፡ ሶላት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በእኩልነት ህፃኑንና አዋቂውን፤ሃብታምና ድሃው፤ ብርቱና ደካማው፤በህብረተሰቡ ውስጥ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ሰዎች ፤ ትከሻ ለትከሻ ተገጣጥመው ወደ አንድ አቅጣጫ በመዞር አንድ ዓይነት እንቅስቃሴ በማድረግ ለፈጣሪያቸው የሚተናነሱበትና ጥልቅ ትስስር የሚፈጥሩበት ነው፡፡ወደ ኢስላም ሃይማኖት ለመግባባት ከሚያስችሉ የኢስላም መሰረቶች ከሁለቱ የምስክነት ቃል ከመስጠት ቀጥሎ ሁለተናውና ዋናው የኢስላም ምሶሶ ነው፡፡ አነስ ኢብኑ ሚሊክ የአላህ ነብይ እንዲህ ብለዋል ብሎ ተናግሯል "አንድ ባሪያ መጀመሪያ ሂሳብ የሚደረገው ሰላት ነው፡፡ ሰላቱ ያማረ እንደሆነ ሁሉም ስራዎቹ ያምራሉ/ይስተካከላሉ፡፡ ሶላቱ የተበላሸ እንደሆነ ሁሉም ሥራዎቹ ይበላሻሉ፡፡ ሶላት በቀናን ሌሊት ከሚገኙ አምስት ወቅቶች ብቻ እንዲፈፀም መደረጉ ማንናውም ሙስሊም ያለምንም ችግር ከልብ በመነጨ ፍቅርና ያለመሰላቸት ተግባራዊ እንዲያደርጋቸው ያስችለዋል፡፡

## ኢስላም ለሙስሊሞች ግዴታ የሆኑ ሰላቶቹን ሰዎች ምቹ በሆነ መንገድ ያለ ምንም መጨናነቅ እንዲፈፅሟቸው ያስቀመጠበትን መንገድ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

1. ኢስላም ሶላትን ለሰጋጆች በጣም ምቹና አስቸጋሪ እንዳይሆን ያደረገበትን መንገድ ስንመለከት አንድ ሙስሊም ሰላት እንዲሰግድ የሚታዘዘው አቅሙና ችሎታው በፈቀደ ደረጃ ነው ምንም እንኳን ቆሞ መስገድ ከግዴታዎች አንዱ ቢሆንም፡፡ ነገር ግን ቆሞ መስገድ ያልቻለ ሰው ቁጭ ብሎ እንዲሰግድ ቁጭ ማለት ቢቸገር ተኝቶ፣ ተኝቶ መስገድ ቢከብደው ባለበት ሁኔታ ሆኖ በምልክት እንዲሰግድ ይደነግጋል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ይላሉ

“የታመመ ሰው ቆሞ መስገድ ከቻለ ቆሞ መስገድ ይስገድ፡፡ ካልቻለ ቁጭ ብሎ ይስገድ፡፡ ቁጭ ብሎ ስጁድ ማድረግ ካልቻለ አካላዊ ምልክት በማድረግ ሱጁዱን ከሩኩዕ ትንሽ ዝቅ ያደርጋል፡፡ በዚህ መልክ ካልቻለ በቀኝ ጎኑ ጋደም በማለትና ወደ ቂብላ በመዞር ይስገድ፡፡ በጎኑ ተጋድሞ መስገድ ካልቻለ እግሮቹን ወደ ቂብላ አቅጣጫ በማድረግ በጀርባው ተኝቶ ይስገድ”

2. ኢስላም ሰላትን ሁሌም በአንድ መልክ ብቻ የሚከናወን ግትር ተግባር ሳይሆን ከእለት ተእለት የሰዎች እነቅስቃሴ እና የህይወት ገጠመኝ ጋር ተስምሚ በሆነ መንገድ መፈፀም እንዲችል ተደረጓል፡ ለምሳሌ በሰላምና በጦርነት ጊዜ የሚፈፀም የስግደት አፈፃፀም ይለያል፡፡አላህ ይላል “በሶላቶች (በተለይ) በመካከለኛይቱም ሶላት ላይ ተጠባበቁ፡፡ ታዛዦች ኾናችሁም ለአላህ ቁሙ፡ ከአደጋ ከፈራችሁም (በጦርነት ጊዜ) እየሄዳችሁም እየጋለባችሁም ስገዱ፡፡
3. ኢስላም ሰዎች ሰላትን ለመስገድ በማይመቹ ሁኔታዎች ውስጥ ሲሆኑ ለመስገድ በሚቸጋገሩበት ጊዜ የተለያዩ የማቅለያ መንገዶችን አስቀምጧል፡፡ ለምሳሌ ጉዞ ላይ ለሆነ ሰው ሰላትን በተለመደው ጊዜና ሁኔታ ለመስገድ አስቸጋሪ ስለሚሆን በዚህ ሁኔታ ሰላትን በተለመደው አይነት እንድንፈጽም አላዘዘንም እንዲያውም ሰዎን በጉዞ ላይ በጊዜ ለመስገድ ያለውን አስቸጋሪነት እንዲሁም በጉዞ ላይ ለድካምና እንግልት ስለሚጋለጡ ጉዞ ላይ የሆነ ሰው አራት አራት የሚሰገዱትን ሰላቶ ሁለት ሁለት አድርጎ እንዲሰግድ በተለየዩ ጊዜያት ለየብቻ የሚሰገዱትን ሰላቶች በማጣመር እንዲሰገዱ ተመቻችቷል፡፡

   ወአን የዕላ ኢብኑ ኡመያ ኡመር ኢብኑል ኽጣብን እንዲህ አልኩት “በጦነት ጊዜ ከሃዲያን ለችግር ይዳርጉናል ብላችሁ ከፈራችሁ ሰላታችሁን ማሳጠር በናንተ ላይ ችግር የለውም” የሚለውን የቁርዓን አንቀጽ አነበብኩለትና አሁን ግን በሰላም ነው የምንኖረው ስለዚህ እንዴት ሰላትን ማሳጠር ይቻላል ብሎ ጠየቃቸው፡፡ ኡመርም “አንተ ያገኘኸውን ነው እኔም ያገኘሁት ሌላ የተለየ ነገር የለኝም” አሉት፡፡ ስለዚህ ጉዳይ የአላህ መልዕክተኛን ጠየቅኳቸው “ይሄ ፈጣሪ ላናን ያደረገው ምፅዋት ነው፡፡ የሱን ምፅዋት ተቀበሉ”፡፡ አሉኝ ሙስሊም የዘገቡት
4. ኢስላም ሰላትን ጉዞ ላይ ላለ ሰው ብቻ ሳይሆን በበሽታ፣ ሃይለኛ ብርድ ሲኖር፣ አስቸጋሪ ጉዳይ ሲገጥም በተለያዩ ጊዜ የሚሰገዱ ሰላቶችን በአንድ ወቅት አጣምሮ መስገድን ፈቅዷል፡፡ ፈአን ኢብኑ አባስ እንዲህ አለ “የአላህ መልዕክተኛ መዲና ውስጥ ጉዞ ላይ ሳንሆን እና ምንም የጠላት ጥቃት ፍራቻ ሳይኖር የዙህርንና የአስር ሰላትን በአንድ ወቅት አጣምረው ሰግደዋል” አለ፡፡አቡዙበይር ሰኢድን ለምንድነው እንዲህ ያደረጉት ብዬ ጠየቅኩት፡፡ ሰኢድም አንተ እኔን የጠየቅከኝን ጥያቄ ኢብነ አባስን ጠይቄዋለሁ አለ፡፡ኢብኑ አባስም በህዝባቸው ውስጥም አንድም ሰው እንዳይቸገር በመፈለግ ነው” ብለው መለሰልኝ፡፡

5. ኢስላም ሶላት የሚሰገድባቸውን ወቅቶች ለሁሉም ሙስሊም ለችግር በማይዳርግ መልኩ ጊዜው እንዲራዘም አድርጓል፡፡ ጃቢራ ኢብኑ አብዱላሂ አለ “መልአኩ ጅብሪል ወደ ነብዩ ዘንድ ፀሀይ ዘንበል ስትል መጣና “ተነስና የዙህርን ሰላት ፀሀይ ሳትዞር ስገድ” አላቸው፡፡ ፀሀይ አንድ ሰው ቁመት ያህል ጥላ እስከሚደርስ ድረስ ቆይቶ ለአስር መጣ “ተነስና አስርን ስገድ” አለው፡፡ ፀሀይ እስክትጠልቅ ጠብቆ መጣና “ተነስና መግሪብን ስገድ” አለው ተነስተው ሰገዱ፡ ፡ የፀሀይ ጮራ እስከሚጠፋ ጊዜ ጠብቆ መጣ “ተነስና የኢሻን ሰላት ስገድ” አላቸው፡፡ ተነስተው ሰገዱ፡፡ ከዚያም የማለዳ ጎህ ሲቀድ “ተነስና የሱብሂን ሰላት ስገድ” አላቸው፡፡ ነብዩም ተነስተው ሰገዱ፡፡ ከዚያም በማግስቱ የሰው ጥላ የሰውዬውን ቁመት ልክ ሲሆን መጣና “ተነስና ዙህርን ስገድ” አላቸው ከዚህም የሰውዬ ጥላ ሁለት እጥፍ ሲሆን መጣና “አንተ መሀመድ ተነስና የአስርን ሰላት ስገድ” አላቸው፡፡ ፀሀይ ስትጠልቅ መጣና “ተነስና የመግሪብን ሰላት ስገድ አላቸው፡፡ የሌሊቱ የመጀመሪያ አንድ ሶስተኛ ከተገባደደ በኋላ መጣና “ተነስና የኢሻን ሰላት ስገድ አላቸው” ቢጫው ወጋገን ቢታይ መጣና “ተነስና የሱብሂን ሰላት ስገድ” አላቸው ከዚያም እንዲህ አላቸው፡፡ “በእነዚህ ሁለት የጊዜ ስፋት  ሁሉ የሰላት ወቅት ነው” ነሳኢ እንደዘገቡት
6. አንድ ሰው ሰላትን በመርሳት ቢጨምር ወይም ቢያጎድል ሙሉውን ሰላት በአዲስ መልክ መልሶ እንዲሰግድ አይጠበቅም፡፡ እንዲያደርግ የሚጠበቀው ነገር በሚረሳበት ጊዜ የሚደረጉ ሁለት ሱጁዶችን ብቻ ያደርጋል፡፡ ይሄም ሰላትን በጣም ቀላልና ምቹ ለማድረግና የሙስሊምን ኢባዳ ለማበላሸት በጣም የሚጓጓውን ሰይጣን ለማባረር እና ፊጣሪን ለማስወደድ ነው፡፡
ከአቢሰኢድኒል አልኹድሪ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ተናግረዋል አሉ፡፡ “በአንድ ሰው በሰላት ውስጥ እያለ ሶስት  ወይንም አራት ረካአ መስገዱን የተጠራጠረ ሰው እርግጠኛ ነኝ ብሎ ባመነበት ነገር ላይ ይፅናና ከማሰላመቱ በፊት ሁለት ሰጁዶችን ያድርግ፡፡እነዚህ ስጁዶች አምስት ረካዳ ሰግዶ ከሆነ ለስህተቱ ማካካሻ ይሆነዋል፡፡በትክክል አራት  ሰግዶ ከሆነ ሰይጣንን ያባርረዋል፡፡
7. አንድ ሙስሊም ሰላት የሚሰግድበትን አቅጣጫ ማወቅ ካልቻለና የሚነግረው ሰው ካላገኘ ይህ ይሆናል ብሎ በገመተው አቅጣጫ ተቀጣጭቶ መስገድ ይችላል፡፡ አላህ ይላል “...አልበቀራህ 115...”
8. ኢስላም በጋራ የሚሰገዱ ሰላቶችን ስግደት ማርዘም ይከለክላል፡፡
ከአቡሁረይራ እንደተነገረው ነብዩ እንዲህ ብለዋል “አንድ ሰው በሰላት ሰዎችን የሚመራ ከሆነ ሰላቱን አያስረዝመው፡፡ ምክንያቱም ተከትለው ከሚሰግዱ ሰዎች መሃል ውስጥ አቅመ ደካማ፣

በሽተኛ እና አረጋዊያን ሊኖሩ ይችላልና። ነገር ግን አንድ ሰው ብቻውን በሚሰግድበት ጊዜ የፈለገውን ያህል ሰላቱን ያርዝም" ቡኻሪ

## 2. የኢስላም በአምልኮ ተግባራት ውስጥ ያለው ምቹነት -ዘካህ

ዘካህ በሙስሊሞች ላይ የተደነገገበት ዋናው ሚስጥር ድህነትን ከኢስላማዊ ማህበረሰብ ውስጥ ማስወገድ እና በድህነት ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ማህበራዊ ቀውሶችን ለመታደግ ነው። ስርቆትን፣ ግድያን፣የሰዎችን ክብርን ያለመጠበቅን ይመስል። ዘካህ ድሆችንና የተቸገሩ ሙስሊሞችን በመርዳትና መሰረታዊ ፍላጎታቸውን እንዲያገኙ በማገዝ፣ከልመና ውርደት በመታደግ የመረዳዳትና የመደጋፍ መንፈስን በሙስሊም ማህበረሰብ ውስጥ እንዲሰርፅ ለማድረግ የሚያስችል ነው።

በዘካህ ግዴታነት ውስጥ ኢስላም ለሰዎች ያመቻቻቸው ባህሪያት እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

1. በዘካ አከፋፈል ውስጥ ኢስላም በሰዎች ላይ ጫና በማይፈጥር መልኩ ገርና ምቹ ካደረጋቸው ነገሮች ውስጥ ዘካህ እንዲከፍሉ የሚጠየቁት ሰዎች ዘንድ በጣም ተወዳጅ ካልሆኑ ንብረታቸው ውስጥ ነው። ቀደም ብሎ በተገለፀው በሙአዝ ኢብኑ ጀበል ሃዲስ ውስጥ ነብዩ "አደራህን ዘካህ ስትቀበል እነሱ ዘንድ በጣም ውድ የሆኑ ንብረቶቻቸውን አትንካ" ብለዋል። ቡኻሪ እንደዘገቡት
2. ዘካህን እንዲከፈል የሚጠየቀው መጠን ዘካን ለመክፈል ግዴታ መድረስ ያለበት የሃብት መጠን አንፃር ሲታይ በጣም አነስተኛ ነው። ይሄም ብቻ ሳይሆን ዘካ እንዲወጣበት ግዴታ መሙላት ያለበት የሃብት መጠን አንድ አመት የሞላው መሆን አለበት። የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ "ወርቅ ላይ ሃያ ዲናር እስኪሞላ ድረስ ዘካ የለውም። ሃያ ዲናር ከሞላና ይህ ሃያ ዲናር አንድ አመት ከሞላው ግማሽ ዲናር ዘካህ ማውጣት ይኖርበታል። ከዚያ በላይ ከጨመረ በመጀመሪያ የሂሳብ ቀመር ልክ አውጣ። ዘካ ማውጣት የግድ የሚሆንበት ንብረት መጠን አንድ ዓመት እስካልሞላ ዘካህ መክፈል አይኖርብህም።
3. ኢስላም በዘካህ ላይ ካቀለላቸው ነገሮች ውስጥ በድህነትም ሆነ በእዳ ምክንያት ዘካ መክፈል የማይችሉ ሰዎችን ነፃ አድርጓል። የአላህ መልዕክተኛ ይላሉ "ዘካህ በሃብታም ላይ እንጂ በሌላ ሰው ላይ አይኖርም።" አህመድ .።ይሄም ብቻ አይደለም እንዲያውም እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ዘካን የመቀበል መብት አላቸው። አላህ እንዲህ ይላል "…. ተውባህ 60…."

4. ዘካ ማውጣት ለተቀባዩ ብቻ ሳይሆን ለሚሰጠውም ሰው ብዙ ትሩፋቶች አሉት፡፡ ዘካ በሚያወጣው ሰው ላይ ሸክም አይደለም፡፡ ዘካ በማውጣቱ ምክንያት የሚያገኘው ትሩፋት ልቦናው ወደ እንዲሰጥ ያስችለዋል፡፡ አላህ ይላል "ከገንዘቦቻቸው ዘካን ተቀበል ነፍሶቻቸውን እንድታጠራቸው ዘንድ፡፡ እነሱም ዱዓ አድርግላቸው ያንተ ዱዓ ለነሱ እርጋታ ይሰጣቸዋል" ተውባህ 103

## 3. ኢስላም የአምልኮ ተግባራት ያደረገው ምቹነት - ፆም

የረመዷን ወር እንዳንዱ ሙስሊም መፆም ግዴታ ከተደረገባቸው ሚስጥሮች ውስጥ በድህነትና በችግር የሚኖሩ ወንድቹን ስሜት እና የሚኖሩበትን ህይወት መረዳት እንዲያስችለው እና ስለነሱ እንዲጠይቅ እንዲያዝንና መልካም እንዲውልላቸው ለማድረግ ነው፡፡ ፆም ያልተፈለጉ መጥፎ ተግባራትና ስነምግባር የምትመራንን የነፍስ ስሜታዊ ፍላጎት ለመቆጣጠር የሚደረግ ትግልም ጭምር ነው፡፡ ፆም መፆም ግዴታዊ ተግባር ቢሆንም ለሰዎች ምቹ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እንዲደረግ ያስተምራል፡፡ ለሰዎች እንዲመች ከተደረገበት ባህሪያቶቹ ውስጥ፡

1. ፆም በዓመት ውስጥ አንድ ወር -የረመዳን-ወር ብቻ ነው እንድንፆም የታዘዘዝነው፡፡ አላህ ይላል፡

"(እንድትጾሙ የተጻፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (አንቀጾች) ሲኾን ቁርኣን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው፡፡ ከእናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይጹመው፡፡ በሽተኛ ወይም በጉዞ ላይ የኾነም ሰው ከሌሎች ቀኖች ቁጥሮችን (በልኩ) መጾም አለበት፡፡ አላህ በእናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፡፡ በእናንተም ችግሩን አይሻም፡፡ ቁጥሮችንም ልትሞሉ አላህንም ቅኑን መንገድ ስለመራችሁ ታከብሩትና ታመሰግኑት ዘንድ (ይህን ደነገግንላችሁ)፡፡ በቀራህ 185

2. ኢስላም ሙስሊሞች ባልተገደበ ፆም ምክንያት ለችግር እንዳይዳረጉ ፆም የሚጀመርበትን እና የሚያበቃበትን ጊዜያት ደንግጓል፡፡ እነዚህ የተወሰኑ ጊዜዎች መጨመርም ሆነ መቀነስ አይፈቅድም፡፡ የፆም ወቅት ከፈጅር እስከ ፀሃይ እስክትጠልቅ ጊዜ ባለው ጊዜ ብቻ እንዲሆን ገድቦአል፡፡ አላህ ይላል፡-

በጾም ሌሊት ወደ ሴቶቻችሁ መድረስ ለናንተ ተፈቀደላችሁ፡፡ እነርሱ ለናንተ ልብሶች ናቸው፤ እናንተም ለነርሱ ልብሶች ናችሁ፡፡በቀራህ 187

3. ፆምን ያለማቋረጥ መፆም ለጉዳት ስለሚዳርግ ኢስላም ያለማቋረጥ መፆምን ከልክሏል፡፡ የአላህ መልእክተኛ ይላሉ "በኢስላም ውስጥ ፆምን ያለማቋረጥ መፆም የለም" ኢብኑ ሂባን

4. *ፆምት ከሌሎች የአምልኮ ተግባራት በተለየ ሁኔታ በሚስጥርየሚሰራ ስራ በመሆኑ አላህ የፆመኛ ሰው ምንዳ በጣም ትልቅና ያልተደገበ አድርጎታል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ "አላህ ብሏል የአዳም ልጅ ስራ ሁሉ ለራሱ ነው ፆም ሲቀር፡፡ እሱ ለኔ ነው፡፡ እኔው ነኝ ምንዳውን የምከፍለው፡፡ ፆም ጋሻ ነው፡፡ አንዳችሁ ፆመኛ በሆናችሁበት ቀን መጥፎ ንግግርን አይናገር፡፡ አንድ ሰው ቢሰድበው ወይም ሊጋደለው ቢሞክር እኔ ፆመኛ ነኝ ይበለው፡፡ የሙሃመድ ነፍስ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ የፆመኛ ሰው የአፍ ጠረን ከሚስክ ሽታ በላይ ጥሩ መዓዛ አለው፡፡ ፆመኛ ሰው ሁለት የሚደሰትባቸው ነገሮች አሉት፡፡ በሚያፈጥር ሰዓትና ጌታውን በሚገናኝበት ጊዜ በመፆሙ ይደሰታል፡፡"*
5. *ኢስላም ፆምን ካቀለለባቸው መንገዶች አንዱ በበሽተኛና ጉዞ ላይ ላለ ሰው ያለመፆም መብት ተሰጥቷቸዋል፡፡ መፆም በሚችልበት ጊዜና ሁኔታ ያልፆሟቸውን ቀናት እንዲፆሙ ተደርጓል፡፡ አላህ ይላል፡*

እንድትጾሙ የተጻፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (አንቀጾች) ሲኾን ቁርኣን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው፡፡ ከእናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይጹመው፡፡ በሽተኛ ወይም በጉዞ ላይ የኾነም ሰው ከሌሎች ቀኖች ቁጥሮችን (በልኩ) መጾም አለበት፡፡ አላህ በእናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፡፡ በእናንተም ችግሩን አይሻም፡፡ ቁጥሮችንም ልትሞሉ አላህንም ቅኑን መንገድ ስለመራችሁ ታከብሩትና ታመሰግኑት ዘንድ (ይህን ደነገግንላችሁ)፡፡." በቀራህ 185

6. *ፆም ለሰዎች አስቸጋሪ እንዳይሆን ከተደረጉበት ገፅታዎች ውስጥ በእርግዝና እና በማጥባት ላይ ያሉ እናቶች ፆም እራሳቸውንን ህፃን ልጃቸውን ለጉዳት ይዳርጋል ብለው ከፈሩ መፆም አይገደዱም፡፡ ባይሆን በሚመቻቸው ጊዜ ያልፆሙትን ቀናት እንዲፆሙ ይደረጋል፡፡ አረጋዊያንም እንደዚሁ ነው ባይሆን ላልፆሙበት ቀን ድሃን ማብላት ይጠበቅባቸዋል፡፡*
   *አላህ በማንኛውም የአምልኮ ስነስርዓቶች በመፈፀም ሂደት ውስጥ ከአቅም በላይ የሆኑ ነገሮችን ተግባራዊ ለማድረግ መሞከርን ይከለክላል፡፡ ጃቢር ኢብኑ አብዲላህ (ረ.ዐ) እንዲህ ይላል፡፡ ነብዩ በአንድ ወቅት ጉዞ ላይ እያሉ ሰዎች ተሰብስበው ለአንድ ሰው ጥላ እያደረጉለት ተመለከቱ የአላህ ነብይ "ይህ ሰው ምን ሆኖ ነው" ብለው ጠየቁ፡፡ ሰዎቹም "ይህ ሰው ፆመኛ ነው" አሉ፡፡ ነብዩም "መንገደኛ ወይም ጉዞ ላይ ሆናችሁ መፆም እንደመልካም ስራ አይቆጠርም፡፡*

7. ያመኛ ሆኖ ረስቶ  ቢበላና ቢጠጣ ፆሙ አይበላሽም፡፡ ፆሙን መፍታት የለበትም፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ይላሉ ፆመኛ ሆኖ ረስቶ የበላ ወይንም የጠጣ ሰው ፆሙን ይሙላ፡፡ አላህ ነው የበላውና የጠጣው፡፡ ቡኻሪ ዘግበውታል፡፡

## ኢስላም በአምልኮአዊ ስነስርዓቶች ላይ ያስቀመጠው የምቹነትና ገራገርነት ባህሪ - ሃጂ

ከተቀደሱ የሃጅ ግቦች ውስጥ የአላህን አንድነት ማሳያ  እና እሱንም ማስታወስና ማላቅ ነው፡፡ በሀጅ ወቅትም ሀጃጆች በተደጋጋሚ የሚዘመምሩት መዝሙርም - አቤት ጌታዬ ሆይ፤አቤት አምሳያ የሌለህ የሆንክ ጌታ፤ምስጋናና ፀጋ ላንተ የተገባ ነው፤ ላንተም አምሳያ የሌለህ ስትሆን- የሚያመለክተው  ይሄንን ነው፡፡ይህም ማለት ጌታችን ሆይ የጥሪህን ምላሽ ለመስጠት፤ ውዴታህን ለማግኘት ከጅለን፤ በብቸኝነትህ አምነን፤ ካንተ ውጪ ከሆኑ ነገሮች ሁሉ አንተ ብቻ ለአምልኮት የተገባህ መሆንህን  ለማረጋገጥ ነው እዚህ ስፍራ የመጣነው፡፡እዚህ ስፍራ በተከበረና በተናቀ፤ በጥቁርና ነጭ፤በአረብና አረብ ባልሆኑ ሰዎች መሃከል  ያለምንም ልዩነት በእኩልነት አላህ ዘንድ የሚቆሙበት ነው፡፡የሚበላለጡባቸው ነገር ቢኖር አላህን የመፍራት ደረጃቸው ነው፡፡ሀጅ በየትኛውም አለም የሚገኙ ሙስሊሞች  ወንድመማማቾች መሆናቸውን የሚያስመሰክር ክስተት ነው፡፡የሃጅ ስነስርዓትን ለመፈፀም አላህ ቀላልና የተመቸ ካደረገበት ባህሪዎቹ ከብዙ በጥቂቱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. ኢስላም ሀጅ እንዲፈጸም ግዴታ ያደረገው በእድሜ ዘመን አንድ ጊዜ ብቻ ነው ይህም የሆነው የሃጅ ተግባራት ለመፈፀም በባህሪያቸው ከፍተኛ ድካምና እንግልት ስላላቸው ነው፡፡ ሃጅ በየዓመቱ እንዲደረግ ግዴታ ቢሆን ኖሮ መካ ይሄን ሁሉ የሙስሊም ቁጥር በአንድ ጊዜ የማስተናገድ አቅም አይኖራትም ነበር፡፡

   አቡሁረይራ እንዲህ ይላሉ" እናንተ ሰዎች ሆይ ሃጅ ማድረግን አላህ በናንተ ላይ ደንግጓል እናም ሀጅ አድርጉ" በማለት ነብዩ ንግግር አደረጉልን፡፡" አንድ ሰው   "በእያንዳንዱ ዓመት ነው የምናደረገው አንቱ የአላህ መልእክተኛ" ብሎ ጠየቀ ፡፡ሶስት ጊዜ እስከሚደጋግመው ድረስ ሳይመልሱለት ዝም አሉት፡፡ ከዚያም የአላህ መልዕክተኛ  "አዎ ብለው ኖሮ በእያንዳንዱ ዓመት ሀጅ ማድረግ ግዴታ ይሆንባችሁ ነበር ደግሞም አትችሉትም ነበር" አሉ፡፡" ከዚያም በማስከተል እንዲህ አሉ "እኔ እንድትሰሩ የተውኩላችሁን ነገር ላይ ተዉኝ፡፡ ሌላ ነገር አትጠይቁኝ ከናንተ በስተፊት የነበሩ ህዝቦች የጠፉት ያላስፈላጊ ጥያቄዎችን በመጠየቃቸውና ነብዮቻቸውን በመቃወማቸው ነው፡፡ አንድ ነገር እንድትሰሩ ካዘዝኳችሁ የቻላችሁትን ያህል ስሩ፡፡ እንዳትሰሩ የከለከልኳችሁን ነገር ሙሉ በሙሉ ተከልከሉ፡፡

2. ሃጅ ከኢስላም መሰረቶች አንደኛው ከመሆኑ ጋር ሀጅ ለመፈፀም በቂ ገንዘብ እና አካላዊ አቅምና ጥንካሬ የሌለው ሰው ሀጅ መፈፀም ግዴታ አይሆንበትም፡፡በሽተኛ የሆነም ሰው ምንም እንኳን በቂ ገንዘብ ቢኖረውም ሃጅ የማድረግ ግዴታ የለበትም፤፡ እንደዚሁ መሰረታዊ የህይወት ጣጣዎቹን እና ሀጅ ለማድረግ የሚስፈልጉ ወጪዎችን መሸፈን የማየችል ሰው የሃጅ ግዴታነት እሱን አይጨምርም፡፡ አላህ ይላል፡

   ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መኼድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው፡፡ አልኢምራን 97

3. በሃጅ ስነ-ስርዓት ውስጥ ለሚፈጠሩ ጉድለቶችና ክፍተቶች ማካካሻ እንዲኖራቸው መደረጉ ኢስላም የሃጅን ስራ ቀላልና ገር እንዲሆን ያስቻለበት አንደኛው መንገድ ነው፡፡ አላህ ይላል "ሐጅንና ዑምራንም ለአላህ ሙሉ፡፡ ብትታገዱም ከሀድይ (ከመሥዋእት) የተገራውን (መሰዋት) አለባችሁ፡፡ ሀድዩም እስፍራው እስከሚደርስ ድረስ ራሶቻችሁን አትላጩ፡፡ ወአቲሙሉ ሃጅ ወልኡምረታ ፊኢን ኡህሱርቱ ፈመስተይሰረ ሚነል ሀድይ…." በቀራህ

4. ኢስላም ሃጅ ለሚያደርጉ ሰዎች እርግጠኛ መሆን ያልቻሏቸውን ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳዮች ሲገጥማቸው ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ሃጃቸውን ማድረግ እንደሚችሉ ያስቀምጣል፡፡ ኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ተናገረች፡፡ የአላህ መልዕክተኛ------- ዱባአቲ ቢንቱ ዙበይር የምትባል ሴት ቤት ገቡና "ሃጅ ማድረግ ያሰብሽ ትመስያለሽ" አሏት፡፡ እሷም "በጌታዬ ይሁንብኝ ህመም እየተሰማኝ ነው እንጂ አዎ አስቤአለሁ" አለች፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ቅድመ ሁኔታ አስቀምጠሽ ሃጅሽን አድርጊ" አሏት፡፡ በማስከተልም እንዲህ ብለሽ ተናገሪ "ጌታዬ ሆይ ሃጅ የማደርገው ሃጄን እንዳልቀጥል የሚያደርግ አስገዳጅ ጉዳይ እስከሚገጥመኝ ጊዜ ነው" (ቡኻሪ)

5. ኢስላም ሃጅን የወንጀል ማስተሰሪያ እና ማጥፊያ አድርጎታል፡፡ አቡሁረይራ እንዳወሩት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል "ይሄን ቤት ሃጅ ሲያደርግ ግብረስጋዊ ግንኙነትና ወንጀል ካልፈፀመ ልክ እናቱ እንደወለደችው ቀን ሆኖ ይመለሳል፡፡" ቡኻሪ

## ኢስላም ለሴቶች ያለው መመቸት

ሴት ልጅ በኢስላም ሃይማኖት ላቅ ያለ ስፍራ አላት። መብቶቿንም አስጠብቋል።ለሴት ልጅ ብቻ ሳይሆን ለሴት ልጅ ክብር የሚሰጥ ሰው የሙሉ መልካም ስብዕና ባለቤት እና የሰዎች ሁሉ ፈርጥ አድርጎ ይቆጠራል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይላሉ "የሙሉ እምነት ባለቤት የሆኑ አማኞች እነዚያ ላቅ ያለ መልካም ስነምግባር ያለቸው ናቸው። ከናንተ ውስጥ ምርጥ ሰው ማለት ለሴቶች መልካም የሆነ ነው። ኢስላም መልካም ስራዎችን እና ደግ መዋልን ለወንዶች ይልቅ ለሴቶች ያስቀድማል፡ ፡ የአላህ መልዕክተኛም "ለሴቶች መልካም ዋሉላቸው" ብለዋል።

ኢስላም ለሴቶች ካደረጋቸው መልካም ነገሮች ውስጥ፡-

1. ለሴት ልጅ ጥሎሽ መክፈል በወንዱ ላይ ግዴታ አድርጓል። አላህ ይላል

ሴቶችንም መህሮቻቸውን በደስታ ስጡ፡፡ ለእናንተም ከእርሱ አንዳችን ነገር ነፍሶቻቸው ቢለግሱ መልካም ምስጉን ሲኾን ብሉት፡፡ ኒሳዕ 4

2. ሴቶች የመጀመሪያ ቀን ስጋዊ ተራክቦ ከመፈፀማቸው በፊትም ሆነ ምናልባት ከተፋቱ ደግሞ ከፍቺ በኋላ ወንዱ ሊከፍላት የሚገባውን የጥሎሽ መጠን እንድትቀበል መብቷ አድርጓል። አላህ ይላል፡

ለእነርሱም መወሰንን በእርግጥ የወሰናችሁላቸው ስትኾኑ ሳትነኳቸው በፊት ብተፈቷቸው ካልማሩዋችሁ ወይም ያ የጋብቻው ውል በእጁ የኾነው (ባልየው) ካልማረ በስተቀር የወሰናችሁት ግማሹ አላቸው፡፡ ምሕረትም ማድረጋችሁ ወደ አላህ ፍራቻ በጣም የቀረበ ነው፡፡ በመካከላችሁም ችሮታን አትርሱ፤ አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና፡፡ በቃራህ 237

3. ኢስላም አንድ ሴት ከባሏ ጋር ከተፋታች በኋላ ለተወሰኑ ወራት ቤቷን ጥላ እንድትሄድ አይፈቅድላትም። በዚህ ምክንያት ባልና ሚስት በሰከነ መንፈስ እራሳቸውን እንዲመለከቱና እንዲረጋጉ እድል ስለሚሰጣቸው ትዳራቸውን በአዲስ መልክ መገንባት ያስችላቸዋልና ነው። አላህ ይላል፡

አንተ ነቢዩ ሆይ! ሴቶችን መፍታት ባሰባችሁ ጊዜ፤ ለዒዳቸው ፍቱዋቸው፡፡ ዒዳንም ቁጠሩ፡፡ አላህንም ጌታችሁን ፍሩ፡፡ ግልጽ የኾነችን ጠያፍ ካልሠሩ በስተቀር ከቤቶቻቸው አታውጡዋቸው፤ አይውጡም፡፡ ይህችም የአላህ ሕግጋት ናት፡፡ የአላህንም ሕግጋት የተላለፈ ሰው በእርግጥ ነፍሱን በደለ፡፡ ከዚህ (ፍች) በኋላ አላህ (የመማለስ) ነገርን ምናልባት ያመጣ እንደኾነ አታውቅም፡፡ ጠላቅ1

4. አንዲት ሴት ከባሏ ጋር ከተፋታች በኋላ በባሏ ቤት ለተወሰኑ ወራት በምታሳልፍበት ጊዜ ወንዱ መሰረታዊና አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎቿን እንዲሸፍንና ሌሎች ተገቢ መብቶቿን

እንዲያሟላላት ይጠበቃል፡፡ ለሷም መልካም የሆነ እንክብካቤ እንዲያደርግላት ያስተምራል፡፡ አላህ ይላል፡

ከችሎታችሁ ከተቀመጣችሁበት ስፍራ አስቀምጧቸው፡፡ በእነርሱም ላይ ልታጣብቡ አትጉዷቸው፡፡ የእርግዝና ባለቤቶችም ቢኾኑ እርጉዛቸውን እስኪወልዱ ድረስ በእነርሱ ላይ ቀልቡ፡፡ ለእናንተም (ልጆቻችሁን) ቢያጠቡላችሁ ምንዳዎቻቸውን ስጧቸው፡፡ በመካከላችሁም በመልካም ነገር ተመካከሩ፡፡ ብትቸጋገሩም ለእርሱ ሌላ (ሴት) ታጠባለታለች፡፡ ጠላቅ 6

5. ኢስላም ሚስት ቤቷ ውስጥ ረዳትና አጋዥ እንዲኖራት እስከፈለገች ድረስ ባል ይሄን የሚሟላት ሃላፊነት አለበት፡፡ አላህ ይላል፡

እናቶችም ልጆቻቸውን ሙሉ የኾኑን ሁለት ዓመታት ያጥቡ፡፡ (ይህም) ማጥባትን መሙላት ለሻ ሰው ነው፡፡ ለእርሱም በተወለደለት (አባት) ላይ ምግባቸውና ልብሳቸው በችሎታው ልክ አለበት፡፡ ነፍስ ችሎታዋን እንጂ አትገደድም፡፡ ወላጂት (እናት) በልጅዋ ምክንያት ለርሱ የተወለደለትም (አባት) በልጁ ምክንያት አይጎዳዱ፡፡ በወራሽም ላይ እንደዚሁ ብጤ አለበት፡፡ (ወላጆቹ) ከሁለቱም በኾነ መዋደድና መመካከር (ልጁን ከጡት) መነጠልን ቢፈልጉ በሁለቱም ላይ ኃጢአት የለባቸውም፡፡ ልጆቻችሁንም ለሌሎች አጥቢዎች ማስጠባትን ብትፈልጉ ልትሰጡ የሻችሁትን በመልካም ኹኔታ በሰጣችሁ ጊዜ (በማስጠባታችሁ) በእናንተ ላይ ኃጢአት የለባችሁም፡፡ አላህንም ፍሩ፤ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች መኾኑን ዕወቁ፡፡ አልበቀራህ 233

6. ኢስላም ሴት ልጅ በትዳር ውስጥ ልጆችን ካፈራች በትዳርም ውስጥም ሆነ ከተፋች በኋላ ቢሆን መሰረታዊ የሆኑ ለህይወት አስፈላጊ ነገሮችን በወንዱ በኩል እንዲሟላላት ይደነግጋል፡፡ አላህ ይላል፡

የችሎታ ባለቤት ከችሎታው ይቀልብ፡፡ በእርሱም ላይ ሲሳዩ የተጠበበበት ሰው አላህ ከሰጠው ይቀልብ አላህ ነፍስን የሰጣትን እንጅ አያስገድድም፡፡ አላህ ከችግር በኋላ ምቾትን በእርግጥ ያደርጋል፡፡ ጠላቅ 7

7. ከኢስላም በፊት መውረስ አይችሉም ነበር፡፡ ኢስላም ለሴቶች የመውረስ መብት አጎናፀፋል፡፡ አላህ ይላል፡

ለወንዶች ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተዉት (ንብረት) ፋንታ (ድርሻ) አላቸው፡፡ ለሴቶችም ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተዉት ከእርሱ ካነሰው ወይም ከበዛው ፋንታ አላቸው፡፡ የተወሰነ ድርሻ (ተደርጓል)፡፡ ኒሳዕ-7

8. ኢስላም ሴቶችን ህይወታቸውን ምቾት እንዲሰማቸው ካደረገባቸው መንገዶች አንዱ በወር አበባና በወሊድ ጊዜ ግዴታ የሆኑ ኢስላማዊ ተግባራትን ሶላትን ፆምን ይመስል ከመስራት እንድታርፍ አድርጓታል፡፡ በነዚህ ጊዜያት ላልተፈጸሙ ስግደቶች ምትክ የሆኑ ስግደቶችን

እንድትሰግድ አይጠበቅባትም፡፡ ፆም ግን መፆም ያልቻለችባቸውን ቀናት ከወር አበባና ወሊድ ነፃ በሆነችባቸው እና ለሷ ምቹ በሆኑ ጊዜያት በማመቻቸት መፆም ይገባታል፡፡

ሙአዘተ የምትባል እንደተናገረችው በወር አበባ ጊዜ ሴት ያልፆመቻቸውን ቀናት እንድትተካ ሲደረግ ሶላቷን እንድትተካ ያልተደረገመት ምክንያት ምንድነው ብዬ አኢሻን ጠየኳት አለች፡ ፡ "አንቺ አሃሩርያ ከሚባል ስፍራ ነው የመጣሽው እንዴ" አለችኝ፡፡ ሴትየዋም "አይደለሁም " ለመጠየቅ ያህል ነው አልኳት፡፡ አኢሻም እንዲህ አለች "የወር አበባ ይከሰትብን ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ፆምን እንድንተካ ስንታዘዝ ሶላትን ግን እንድንተካ አልታዘዘንም በማለት መለሰችላት"፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በወር አበባ ላይ ያለች ሴት በሃጅ ስነስርዓት ወቅት ያለውን የመሰናበቻ ጠዋፍ (ከዕባን የመዞር ስነስርዓት) የማከናወን ግዴታ የለባትን፡፡

9. ኢስላም ለሴቶች ገርና ተፈጥሮአዊ ፍላጎታቸውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ካደረገባቸው መንገዶች አንዱ በወር አበባ ጊዜ የግብረስጋ ግንኙነት ሲቀር በወር አበባ ባልሆነችባቸው ጊዜ ባል ከሚስቱ ሚስትም ከቧላ ጋር ምቾትና እርካታ ሊሰጣት የሚችሉ ነገሮችን ሁሉ ማድረግ እንድትችል ፈቅዶላታል፡፡ ከአነስ እንደተነገረው አይሁዶች ሚስቶቻቸው በወር አበባ ላይ ሲሆኑ አብረዋቸው አይበሉም አብረዋችም አይተኙም ነበር፡፡ የነብዩ ባልደረቦች ስለዚህ ጉዳይ ጠየቁ፡፡ አላህም ይህን የተመለከተ እንዲህ የሚል የቁርዓን አንቀጽ አወረደ፡፡

ከወር አበባም ይጠይቁሃል፡፡ እርሱ አስጠያፊ ነው፡፡ ሴቶችንም በወር አበባ ጊዜ ራቋቸው፡፡ ንጹሕ እስከሚኾኑም ድረስ አትቅረቡዋቸው፡፡ ንጹሕ በኾኑም ጊዜ አላህ ካዘዛችሁ ስፍራ ተገናኙዋቸው፡፡ አላህ (ከኃጢኣት) ተመላሾችን ይወዳል፤ ተጥራሪዎችንም ይወዳል በላቸው፡፡ አልበቀራህ 222

የአላህ መልዕክተኛም እንዲህ አሉ "በወር አበባ ጊዜ ከሚስቶቻችሁ ጋር ግብረስጋ ግንኙነት ሲቀር ሁሉንም ነገር ማድረግ ትችላላችሁ"

10. ኢስላም ሴቶችን ለችግር እንዳይዳረጉ ከተቀመጡ መንገዶች ሌላኛው ሴቶች ጦር ሜዳ ውስጥ የመሳተፍ ግዴታ የለባቸውም፡፡ እናታችን አኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ አለች፡፡ "አንቱ የአላህ መልዕክተና ሴቶች የጦር ሜዳ ላይ ትግል ውስጥ እንዲሳተፉ ይገደዳሉን" ብላ ጠየቀች፡፡ ነብዩም "አዎን መገዳደል የሌለበት ትግል አለባቸው እነሱም ሃጅ እና ኡምራ ማድረግ ነው" ብለው መለሱላት፡፡ አህመድ ዘግበውታል፡፡

11. ኢስላም ሴትን በፍቃዷ እስካላደረገችው ጊዜ ድረስ የውጭ ስራ እንድትሰራ የቤተሰብ ሃላፊነቶችን እንድትሸከም አያስገድዳትም፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ይላሉ "በሴቶቻችሁ አላህን ፍሩ፡፡ እነሱን በአላህ ቃል ኪዳን ነው ያገባችኋቸው፡፡ የአላህን ስም በመጥራት ነው ብልቶቻቸው ሃላል ያደረጋችሁት፡፡ የምትጠሉት የሆነ ሰው ወደ ቤታችሁ እንዳይገባ

አይፍቀዱ። እንደዚያ አድርገው ከሆነ ለጉዳት በማይዳርጋቸው መልኩ ግረፏቸው። በእናንተ ላይ እነሱን የመመገብ የማልበስ ግዴታ አለባችሁ።

**<u>ኢስላም በገንዘብ ነክ ዙሪያ ላይ ያስቀመጣቸው ምቹ ስርዓቶች</u>**

ገንዘብ ሰዎችን የእለተ ተእለት እንቅስቃሴ የሚከውኑበት እና ሚገበያዩበት መሳሪያ ነው። ገንዘብ በሰዎች መሃከል የሚደረግ የእለተ ተእለት የግብይትና ዝውውር ስራ ስለሆነ አንድ ሰው ከሌላው ከጉድለት ስህተትና ጥፋት ነፃ በሆነ መልኩ ሁል ጊዜ ማካሄድ ሊከብድ ይችላል። አንዱ የሌላውን መብት ሊጥስ የሚችልባቸው መንገዶች ብዙ ስለሆኑ በሰዎች መሃከል የመቻቻልና የመተሳሰፍ ልምድ ይኖር ዘንድ ኢስላም ገንዘብ ነክ በሆኑ ጉዳዮችም ለሁሉም ወገን ምቹ ሊሆን በሚችል መንገድ ያስተናግዳል። ኢስላም ንግድንና ገንዘብ ነክ የሆኑ ጉዳዮችን በማስመልከት የሚከተሉትን ግዴታዎች አስቀምጧል።

1. ኢስላም የግብይት ስርዓት በመተሳሰብና በመቻቻል እንዲፈፀም ያዛል። የጋራ ብልፅግና ሊያመጣ በሚችል መልኩ መካሄድ እንዳለበት ያሳስባል። የአላህ መልዕክተኛ ይላሉ "ሲሸጥ ወይንም ሲገዛ የገዢንም ሆነ የሻጭን የጋራ ምቾትና ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ የተገበያየ ሰው አላህ ያዝንለት።"
2. በንግድና ገንዘብ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ከተቀመጡ ጉዳዮች ሌላኛው በዕዳ ምክንያት ለችግር የተዳረገ ሰው የችግር ጊዜውን አልፎ ዕዳውን መክፈል እስከሚችል ድረስ የእፎይታ ጊዜ መስጠት እንደሚገባና ከተቻለ ደግሞ ዕዳውን ይቅር ማለት (መሰረዝ) እንደሚገባ ኢስላም አበክሮ ይመክራል። አላህ ይላል፡-

   "የድኽነት ባለቤት የኾነም (ባለዕዳ) ሰው ቢኖር እማግኘት ድረስ ማቆየት ነው። (በመማር) መመጽወታችሁም ለእናንተ በላጭ ነው። የምታውቁ ብትኾኑ (ትሠሩታላችሁ)።"

   የአላህ መልዕክተኛ አበዳሪዎች ባለእዳዎቻቸውን እዳቸውን መመለስ እስኪችሉ ድረስ መታገስና የጊዜ ገደብ እንዲያረዝሙላቸው አማኞችን ሲያነሳሱ እንዲህ ይላሉ "እዳ ያለበት ሰው ያለበትን ዕዳ መክፈል እስኪችል ጊዜ የታገሰ ሰው በእያንዳንዱ ቀን ሰደቃ ይቆጠርለታል፡ ፡ ከተባለው ጊዜ መክፈል ሳይችል ከቀረ መክፈል እስከሚችልበት ቀን ድረስ የታገሰ ሰው በእያንዳንዱ ቀን የብድሩን መጠን ያህል ሰደቃ እንዳደረገ ይቆጠርለታል" ኢብኑ ሂባን ዘግበውታል
3. ኢስላም በማንኛውም የህይወት ገጠመኞቻችን ገራገርና ይቅርባይና ለሌሎች ሰዎች የምቾትና ደስታ ምንጭ እንድንሆን ይቀሰቅሳል ያበረታታል።

የአላህ መልዕክተኛ ይላሉ "ከናንተ በስተፊት አንድ ሰው አላህ ዘንድ ሂሳብ ተደረገ። ምንም አይነት መልካም ስራ አልነበረውም። ነገር ግን ሰውየው ሃብታም ነበርና ብድር ላበደራቸው ሰዎች ብድራቸውን መክፈል ከተቸገሩ ብድሩን እንዲሰርዙላቸው ሰራተኞቹን ያዛቸው ነበር" አላህም እንዲህ አለ።" እኛ ለይቅርባይነት ከማንም በላይ የተገባን ነንና እሱን ይቅር በሉት ብሎ መላኢኮቹን ያዛል።ሙስሊም ዘግበውታል

4. ኢስላም በሰዎች መሃከል የሚኖር የእቃ የመዋዋስና የገንዘብ መበዳደር በመተሳሰብና በመተዛዘን መሆን እንዳለበት ያበረታታል። አቡሁረይራ እንደተናገሩት አንድ ሰው መጣና የተዋሱትን እቃ እንዲመልስላቸው ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) አስጨንቆ ጠየቃቸው የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ሰውየው ላይ መጥፎ እርምጃ ለመውሰድ እስከሚያስቡ ድረስ። የአላህ መልዕክተኛም "ተዉት ለንብረት ባለቤት የፈለገውን የመናገር መብት አለው" አሏቸው። ከዚያም በማስከተል የሱ የሆነውን አይነት ስጡት" አሉ። ሰሃቦቹም አንቱ የአላህ መልዕክተኛ የሱ አይነት አምሳያ እንጂ እራሱን አናገኝለትም" አሉ። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) የሚመስለውንም ቢሆን ስጡት ከናንተ ውስጥ ምርጥ ሰው ማለት ብድርን የተሻለ አድርጎ የመለሰ ነው።
5. ገዢ ወይም ሻጭ ግብይት ከፈፀመ በኋላ ከሁለት አንዳቸው ተፀፅተው ግብይታቸውን ማፍረስ ቢፈልጉ መመላለስ እነዳለባቸው ኢስላም ሰዎችን ያበረታታል።የአላህ መልእክተኛ ይላሉ "ግብይት ከተፈፀመ በኋላ ግብይቱን በመፀፀት ለማፈፍረስ የፈለገን ሰው በእሺታ የተቀበለ ሰው የቂያም ቀን ሸክሙን አላህ ያቀልለታል።
6. በንግድ ልውውጥ ወቅት የመምረጥ መብት ለሁለቱም ወገኖች ኢስላም መብት ሰጥቷል። የአላህ መልዕክተኛ ይላሉ "ሁለት ተገበያዮች በግብይት ወቅት እስከሚለያዩ ድረስ የመግዛት ወይም የመሸጥ መብት ለሁለቱም የተጠበቀ ነው። ግልፅ በሆነ መንገድ ተማምነው ግብይት ከፈፀሙ ንግዳቸው የተባረከ ይሆናል። ከዋሹና አንዱ ሌላኛውን ካታለለ በንግድ የሚያገኙትን በረካ አላህ ይነሳቸዋል። ቡኻሪ

<u>የኢስላም የወንጀለኛ መቅጫ ህግጋት ለሰው ልጆች ያላቸው ምቹነትና የማረጋጋት አቅም</u>

ኢስላም እንደ ሌሎች ሃይማኖቶች ሁሉ የወንጀል መቀጣጫ ህጎችን ደንግጓል። እነዚህንም ህግጋቶች ተግባራዊ በማድረግ የማህበረሰቡን ሰላም መረጋጋትና ደህንነት እንዲጠመቅ ያደርጋል፡ ፡መጥፎ ገሮችም በማህበረሱ ውስጥ እንዳይዛመቱ ያደርጋል። የኢስላም የወንጀለኛ መቅጫ ህግጋት የሰዎችን ህይወት ይታደጋል። የሰዎች መብትና ክብር እንዲሁም ንብረትና ሃብት እንዲጠበቅ ያደርጋል። ድንበር የሚያልፉትንና ስርዓት አልበኞችን አደብ እንዲገዙ ይበቀላል። በአጠቃላይ

የኢስላም የመቀጣጫ ህግጋት የሰዎችን ምድራዊ ሕይወት መስተጋብር ያማረና የሰከነ አንደኛው በሌላኛው ላይ ድንበር እንዳያልፍና እንዳይበዳደሉ ያደርጋል። በእነዚህ የወንጀለና መቅጫ ህግጋት ምክንት ግፍንና በደልን ያስተካክላል ወይም እንዳይከሰቱ ይቀንሳል። ለዚህም ኢስላም ለእያንዳንዱ ወንጀል ተመጣጣኝ የሆኑ የመቅጫ ህግጋትን አስቀምጧል።

ሰውን አውቆ የገደለ ሰው እንዲቀጣ ይደነግጋል። አላህ እንዲህ ይላል

እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በተገደሉ ሰዎች ማመሳሰል በናንተ ላይ ተጻፈ፡፡ ነጻ በነጻ ባሪያም በባሪያ ሴትም በሴት (ይገደላሉ)፡፡ ለእርሱም (ለገዳዩ) ከወንድሙ (ደም) ትንሽ ነገር ምሕረት የተደረገለት ሰው (በመሓሪው ላይ ጉማውን) በመልካም መከታተል ወደርሱም (ወደ መሓሪው) ገዳዩ በመልካም አኳኋን መክፈል አለባቸው፡፡ ይህ ከጌታችሁ የኾነ ማቃለልና እዝነት ነው፡፡ ከዚህም በኋላ ሕግን የተላለፈ ሰው ለርሱ አሳማሚ ቅጣት አለው፡፡ አልበቀራህ 178

ሰውን አውቆ የገደለ ሰው የተገዳይ ቤተሰቦች ይቅርታ ወይም ምህረት እስካላደረጉ ድረስ በሞት እንዲቀጣ ይደነግጋል። የስርቆት ወንጀልን የፈጸመ ሰው እጁ እንዲቆረጥ ኢስላም ይደነግጋል። አላህ እንዲህ ይላል፡

ሰራቂውንና ሰራቂይቱንም በሠሩት ነገር ለቅጣት ከአላህ የኾነን መቀጣጫ እጆቻቸውን ቁረጡ፡፡ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡ አልማኢዳህ 38

አንድ ሰው የስርቆት ወንጀል በመፈፀሙ ምክንያት እጁ እንደሚቆረጥ እርግጠኛ ከሆነ ከስርቆት ተግባር ይርቃል። እጁም ከመቆረጥ ይድናል። የሰዎች ሃብትና ንብረትም ከስርቆት ይጠበቃል። ባለትዳር ሳይሆን የሴትን ልጅ ክብር ዝሙት በመፈፀም የደፈረ ሰው በግርፋት ይቀጣል። አላህ ይላል፡

ዝሙተኛይቱና ዝሙተኛው ከሁለቱ እያንዳንዳቸውን (ያላገቡ እንደኾኑ) መቶ ግርፋትን ግረፉዋቸው፤ በእነርሱም በአላህ ፍርድ ርኅራኄ አትያዛችሁ፡፡ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ እንደኾናችሁ (አትራሩ)፡፡ ቅጣታቸውንም ከምእምናን ጭፍሮች ይገኙበት፡፡ ኑር 2

እንዲህ መደረጉ የሰዎች ዝርያ እንዲጠበቅና ሃብትና ንብረታቸው አግባብነት በሌለው ሰው እንዳይወረስ ይጠብቃል። የሰውን ክብር በመሳደብ የሚያጎድፍ ወይም የሚያነውር ሰው እንደዚሁ በግርፋት ይቀጣል። አላህ ይላል፡

እነዚያም ጥብቆችን ሴቶች (በዝሙት) የሚሰድቡ ከዚያም አራትን ምስክሮች ያላመጡ ሰማኒያን ግርፋት ግረፏቸው፡፡ ከእነርሱም ምስክርነትን ሁልጊዜ አትቀበሉ እነዚያም እነሱ አመጸኞች ናቸው፡፡ ኑር 4

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ወንጀሎች በግለሰብና በማህበረሰብ ውስጥ የሚያስከትሉትን

መጥፎ አሻራዎች መሰረት ያደረገ ተመጣጣኝ የወንጀለኛ መቅጫ ህግጋቶችን ደንግጓል። ለእያንዳንዱ ወንጀል የተመለከተ መቅጫ ህግ ከመደንገጉም በተጨማሪ ኢስላም ጠቅለል ያሉ የወንጀለኛ መቅጫ መርሆዎችን አስቀምጧል። አላህ ይላል

የመጥፎም ነገረ ዋጋ ብጤዋ መጥፎ ናት፡፡ ይቅርም ያለና ያሳመረ ሰው ምንዳው በአላህ ላይ ነው፡፡ እርሱ በደለኞችን አይወድም፡፡ አልሹራ

በሌላኛው የቁርዓን አንቀፅ በተመሳሳይ አላህ እንዲህ ይናገራል፡

ብትበቀሉም በርሱ በተቀጣችሁበት ብጤ ተበቀሉ፡፡ ብትታገሱም እርሱ ለታጋሾች በእርግጥ በላጭ ነው፡፡” ኒህል 126

ይህ ሆኖ ሳለ ወንጀለኛን ለመቅጣት ሊሟሉ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና ማዕቀፎች አሉ።ኢስላም ያስቀመጣቸው የህግ ማዕቀፎች ምን ያህል የግለሰቦችንም ሆነ የማህበረሰቡን ሰላም መረጋጋትና ደህንነት እንዲጠመቅ ምቹ እንዲሆኑ ያስቻለውን ባህሪ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. የወንጀል መቅጫ ህግጋት የሰዎችን ሰላምና መረጋጋት ከመጠበቅ አንፀርም ሆነ በወንጀለኞች ላይ በሚደረገው የፍርድ ሂደት ኢስላም ፍትሀዊ ነው። ከዚህ ባህሪው አንዱ ኢስላም የግለሰብ መብቶችን የተላለፈ ሰው በተመለከተ የመቅጫ ህግጋቶቹ ግትር አይደሉም።በበዳይና በተበዳይ መሃከል የሚኖረው ግንኙነት ቅጣትን ብቻ መሰረት ያደረገ ሳይሆን ይቅርታ መደራረግን እንዲሁም በመግባባት ቀድሞ የነበራቸውን ሰላም የመፍጠርን በር አልዘጋም። አላህ ይላል

የመጥፎም ነገረ ዋጋ ብጤዋ መጥፎ ናት፡፡ ይቅርም ያለና ያሳመረ ሰው ምንዳው በአላህ ላይ ነው፡፡ እርሱ በደለኞችን አይወድም፡፡” ሹራ 40

2. የአላህን መብቶች ከመተላለፍ ጋር በተያያዘ ወንጀለኛ ሰው እራሱ ወንጀል መፈፀሙን እስካላጋለጠ ድረስ ለፈፀመው ወንጀል ቅጣት ተግባራዊ አይደረግበትም። ምክንያቱም ወንጀሉ የተፈፀመው በአላህና በባሪያው መካከል ነውና። አቡ ሁረይራህ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፈው የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል። “ሁሉም ኡመቶቼ ይቅርታ ይደረግላቸዋል እነዚህ ወንጀልን በይፋ ወይንም በግልፅ የሚሰሩ ሲቀሩ ወይንም ወንጀልን አደባባይ ላይ የሚያወጡት ሲቀሩ። አንድ ሰው ወንጀልን በሌሊት ይሰራል፣ ከነጋም በኋላ ለሰዎች ትላንትና እኮ እንዲህ እንዲህ ሰራሁ እያለ ይናገራል በእርግጥ ጌታው በሌሊት የሰራውን ስራ ደብቆለት እያለ እሱ በጠዋት ተነስቶ አላህ የደበቀለትን አደባባይ ላይ ያወጣል። ሙተፈቁን አለይሂ።

ኢስላም የወንጀለኛ መቅጫ ህግጋትን ተግባራዊ ከማድረግ በስተጀርባ ያለው ዓላማ የማህበረሰቡን መብት ሰላምና መረጋጋት በማስከበር ምቹና የተረጋጋ ህይወት እንዲኖሩ ለማስቻል ነው።ሰውን

የሚገድል ሰው እራሱ እንደሚገደል ካወቀ፣ የሰረቀ ሰው እጁ እንደሚቆረጥ ከተረዳ፣ ዝሙት የፈፀመ ሰው እንደሚገረፍ ከተገነዘበ፣ የሰውን ክብር በስድብ የሚያጎድፍ እንደዚሁ እንደሚገረፍ ካወቀ እነዚህን ተግባራት ከመፈፀም ይታቀባል፡፡ እሱም ሌሎችም ሰዎች ሰላም ይሆናሉ፡፡ አላህ እንዲህ ባለ ጊዜ እውነት ተናግሯል

ለእናንተም ባለ አእምሮዎች ሆይ! በማመሳሰል (ሕግ) ውስጥ ሕይወት አላችሁ፡፡ ትጠነቀቁ ዘንድ (ገዳይን መግደል ተደነገገላችሁ)፡፡ አልበቀራህ 179

አንዳንድ ሰዎች የተወሰኑ ኢስላም የደነገጋቸውን የወንጀል መቅጫ ህግጋት ዘግናኝና ጭካኔ የተሞላባቸው እንደሆኑ ይናገራሉ፡፡ ለዚህ ምላሹ አንድ ጤነኛ አእምሮ ያለው ማንኛውም ሰው ወንጀል በህብረተሰብ ውስጥ ጉዳትና አሉታዊ ተፅእኖ እንደሚፈጥር የማይካድ ሃቅ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ስለዚህም እነዚህን ወንጀሎች ለማስቆም እና በማህበረሰቡ ውስጥ እንዳይስፋፉ ለማድረግ የወንጀለኛ መቅጫ ደንቦችና ህግጋት መኖራቸው የግድ ይላል፡፡ የልዩነት ምንጭ የሚሆነው የቅጣቱ ይዘት በተመለከተ ይሆናል፡፡ የትኞቹ የወንጀለኛ መቅጫ ህግጋት ናቸው ወንጀልንና ድንበር አላፊነትን የመታደግ አቅም እንዳላቸው እያንዳንዱ ሰው እራሱንና አካባቢውን በመመልከት መጠየቅ ይችላል፡፡ ኢስላም ወንጀልን ለመከላከልና ብሎም ለማስወገድ የደነገጋቸው ህግጋቶች ናቸው ስኬታማ ወይንስ እነዚያ ወንጀል እንዲበራከት እንጂ የማይከላከሉ የሰው ልጅ የደነገጋቸው ህግጋቶች ናቸው ውጤታማ? ከሰውነታችን አካል ውስጥ አንዱ የተበላሸ አካል ካለና እሱን ቆርጠን ካስወጣነው የተቀረው የሰውነታችን ክፍል ሰላምና ጤና የሚያገኝ ከሆነ የተበላሸውን የሰውነት ክፍል ቆርጦ ማስወገድ በየትኛውም ሚዛን ነው ጭካኔ ነው የሚያሰኘው፡፡ ኢስላምም እንደዚህ ነው፡፡

## ኢስላም በጦርነትና በምርኮኛ አያያዝ ላይ ያለው ገርነት

ከሰው ልጆች ማህበረሰባዊ ተፈጥሮ ውስጥ ህዝቦች በመስማማት በመፈቃቀር በመግባባት የሚኖሩበት ጊዜ እንዳለ ሁሉ አንዳንዴ ደግሞ በአመለካከት፣የግዛት ማስፋፋትና ፣ በሃይማኖት መለያየት እንዲሁም ለኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሲባል ለክርክርና ለጦርነት መዳረጋቸው አልቀረም፡፡ አላህ ይላል "ለእነዚያ «ጌታችን አላህ ነው» ከማለታቸው በስተቀር ያለ አግባብ ከአገራቸው የተባረሩ ለሆኑት (ተፈቀደ)፡፡ አላህ ሰዎችን ከፊላቸውን በከፊሉ መገፍተሩ ባልነበረ ኖሮ ገዳማት፣ ቤተክርስቲያኖችም፣ ምኩራቦችም በውስጣቸው የአላህ ስም በብዛት የሚወሳባቸው መስጊዶችም፤ በተፈረሱ ነበር፡፡ አላህም ሃይማኖቱን የሚረዳውን ሰው በእርግጥ ይረዳዋል፡፡ አላህ ብርቱ አሸናፊ ነውና፡፡"

በኢስላም ጦርነት የሚደረግበት ዋነኛ ምክንያት የግዛት ማስፋፋት፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማግኘትና፣ የበላይነት ለመቀዳጀት ሳይሆን ሰብአዊነት ተልኮ ያለው ነው፡፡ አላህ ይላል

እንደነዚያ ለትዕቢትና ለሰዎች ይዩልኝ ሲሉ ከአላህም መንገድ ለማገድ ከአገራቸው እንደወጡት አትኹኑ፡፡ አላህም በሚሠሩት ሁሉ (በዕውቀቱ) ከባቢ ነው፡፡ "....አንፋል 48...."

በኢስላም ሃይማኖት ጦርነት ለማካሄድ መሰረታዊ መንስኤው ጦርነትን መከላከልና የተበደሉትን መርዳት ነው፡፡ አላህ ይላል፡-

በአላህ መንገድና ከወንዶች ከሴቶችና ከልጆችም የኾኑትን ደካሞች እነዚያን፡- «ጌታችን ሆይ! ከዚች ባለቤቶችዋ በዳይ ከኾኑት ከተማ አውጣን ከአንተም ዘንድ ለእኛ አሳዳሪን አድርግልን ከአንተ ዘንድም ለእኛ ረዳትን አድርግልን» የሚሉትን (ለማዳን) የማትጋደሉት ለእናንተ ምን አላችሁ" ኒሳእ 75...

በኢስላም ጦርነት ለማካሄድ መሰረታዊ ምክንያት ሰብአዊነት ነው ካልን ዘንድ በጦርነት ወቅት የሚፈጸሙ ነገሮች ከሰው ልጅ ሰብዓዊ ተፈጥሮ ጋር ተስማሚና ምቹ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ኢስላማዊ የጦርነት መርሆች ህግና ስርዓቶች ለሰው ልጆች ፍትሃዊነት፣ እና የሁሉንም መብት በተገቢው መንገድ የሚጠብቅ ሃይማኖት መሆኑን እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

1. ኢስላም ጠላቶች እንደሚሉት የሽብርና የጥላቻና የበደል ሃይማኖት አይደለም፡፡ አላህ በቁርዓኑ "እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን (ከሓዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ፡፡ ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና፡፡"

   እያለ ድንበር አላፊነት እንዳይኖር እያዘዘ እንዴት ኢስላም የሽብርተኝነት፣ የጭካኔና የስርዓት አልበኝነት ሃይማኖት ሊሆን ይቻለዋል፡፡

2. ኢስላም በጦርነት ጊዜ ከሚከተላቸው ለሰው ልጆች ምቹና ሰላማሚነት አንፃር በደህናው ጊዜ ቀርቶ ከጠላቶቹ ጋር በጦርነት ጊዜም እንኳን የጠላት ወገኖች ከተስማሙ ከጦርነት ይልቅ የሰላምን መንገድ መከተል የሃይማኖቱ መርህ ነው፡፡ ይህም ኢስላም የሰዎችን ደም በማፍሰስ የሚረካ አየደለም፡፡ አላህ ይላል ፡-

"ወደ ዕርቅም ቢያዘነብሉ ወደ እርሷ አዘንብል፡፡ በአላህም ላይ ተጠጋ፡፡ እነሆ እርሱ ሰሚ ዐዋቂ ነውና፡፡"

3. ኢስላም ሙስሊሞችን ከማይዋጉና ከሙስሊሞች ጋር የሰላም ስምምነት ካላቸው ህዝቦች መዋጋት ተከታዮቹን አያዝም፡፡ አላህ ይላል

እነዚያ በእናንተና በእነርሱ መካከል ቃል ኪዳን ወዳላቸው ሕዝቦች የሚጠጉና ወይም እናንተን ለመጋደል ወይም ወገኖቻቸውን ለመጋደል ልቦቻቸው የተጨነቁ ኾነው የመጧዋችሁ ሲቀሩ፤ (እነዚያንስ አትጋደሉዋቸው)፡፡ አላህም በሻ ኖሮ በእናንተ ላይ ኀይል በሰጣቸውና በተጋደሉዋችሁ ነበር፡፡ ቢተዋችሁና ባይጋደሉዋችሁም ወደ እናንተም እርቅን ቢያቀርቡ አላህ ለእናንተ በነሱ ላይ (የመጋደል) መንገድን አላደረገም፡፡" ኒሳዕ 90

4. በኢስላም ውስጥ የሚካሄዱ ጦርነቶች ከሰብአዊነት ይዘታቸው እንዳይወጡ የራሳቸው የሆነ ደንብና ስነስርዓት እንዲሁም የጦርነት ማዕቀፍ እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡ በጦርነት ውስጥ በቀጥታ የሚሳተፉትን እና ረዳቶቻቸውን እንጂ ከዚህ ውጪ ያሉትን መግደል የተከለከለ ነው፡፡ ሽማግሌዎች፣ ህፃናት፣ ሴቶች፣ በሽተኞች፣እና በበሽተኞችንና ቁስለኞችን የሚያክሙ ሃኪሞች፣ እውነተና ባህታዊ የሆኑ ሰዎችን መግደል የተከለከለ ነው፡፡ኢስላም የጦር ቁስለኞችን ማሰቃት፣በጦርነት የተገደሉ ሰዎችን አካላት መቆራረጥ ይከለክላል፡፡ በተመሳሳይ ኢስላም በጦርነት ወቅት መኖሪያ ቤቶችን ማውደም፣ የውሃ ማስመሮችን ወንዞችን ማበላሸት፣ እንዲሁም በጦርነት ወቅት የሚሸሹ የጠላት ሃይሎችን እያሳደዱ መግደል ይከለክላል፡፡ እነዚህ ከላይ የገለፅናቸው ነገሮች እና ሌሎችንም ጨምሮ የአላህ መልዕክተኛው ሙሀመድ ሆኑ ቅን የእሳቸው አራቱ ተተኪዎች የጦር መሪዎቻቸውን ወደ ጦር ሜዳ ሲልኩ የሚሰጧቸው የምክር አቅጣጫዎች ነበሩ፡፡

የአላህ መልዕክተኛ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) እነዚያን ከሚወደው መካ ከተማ ያባረሩትን፣ እራሱን ቤተሰቦቹንና የእምነት አጋሮቹን ለከፋ መከራና ችግር አረመኔያዊ ጫካኔ የዳረጉትን፣ እሱንና

ጓደኞቹን ለስደት የዳረጉትን ፣ከዚም አልፎ ተርፎ ጓደኞቹን በአሰቃቂ ሁኔታ የገደሉትን እሱን ራሱን ለመግደል የተቻላቸውን ያህል ያሴሩትን የመካ ህዝቦች በፍጹም የበላይነትና ድል አድራጊነት አሸንፈው ከተቆጣጠሩ በኋላ እነዚሁኑ ህዝቦች ያስተናገዱበት መንገድ የኢስላም ሃይማኖት ለሰው ዘር ሁሉ ምን ያህል የሰላም፣ የሰብዓዊነትና የይቅርባይነት ሃይማኖት እንደሆነ ዓይነተኛ ማሳያ መሆኑን ታሪክ ይመሰክራ፡፡እነዚህን አረመኔያና የጭካን ድርጊት የፈፀሙበትን ሰዎች እንዲህ ነበር ያሏቸው፡ " ከአሁን በሁዋላ እናንተ ነፃ ናችሁ…አቡሱፍያን ቤት የገባ ሰው ሰላም ይሆናል፣ በሩን የዘጋ ሰው ሰላም የሆናል፣የጦር መሳሪያውን የጣለ ሰው ሁሉ ሰላም የሆናል" ነበር ያሉት ሙስሊም የዘገቡት

5. ኢስላም የጠላት እስረኞችን ሰብአዊ መብት የሚያከብር ሃይማኖት ነው፡፡ ኢስላም እስረኞችን ማሰቃየት፣ ማዋረድ፣ ማሸበር፣ ማፌዝ፣ እስኪሞቱ ድረስ ምግብና መጠጥ ማዕቀብ መድረግ ይከለክላል፡፡ እንደውም እነሱን በአክብሮትና መልካም እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ያዛል፡፡ አላህ ይላል፡-

ምግብንም ከመውደዳቸው ጋር ለድኻ፣ ለየቲምም፣ ለምርኮኛም ለእስረኛም ያበላሉ፡፡ «የምናበላችሁ ለአላህ ውዴታ ብቻ ነው፡፡ ከእናንተ ዋጋንም ማመስገንንም አንፈልግም፡፡ ሱረቱል ኢንሳን 8-9"

የኢስላም የሃይማኖቱ በየትኛውም ዘመን ያሉ ተከታዮቹንም እንደሀ ያለውን ከምርኮኞች አያያዝ አጥብቀው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይመክራል፡፡ የሙስዳብ ኢብኑ ኡመይር ወንድም የሆነው አቢአዚዝ ኢብኑ ኡመይር እንዲህ ይላል እኔ በበድር ጦርነት ከተማረኩት ምርኮኞች አንዱ ነበርኩኝ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ "ለሙርኮኞች መልካም ዋሉ" ብለው ተናገሩ፡፡ እኔ ከአንሷሮች (የመዲና ሙስሊሞች) ጋር አብሬ ነበርኩ፡፡ ቁርስና እራት ሲመጣላቸው የነብያቸውን ምክር ተግባራዊ በማድረግ ለራሳቸው ቴምር እየበሉ እኔን ዳቦ ያበሉኝ ነበር፡፡ ፡፡ ሙእጀሙል ሰጊር

6. ኢስላም ምርኮኞችን አንዳንድ ጊዜ ያለምንም ካሳ አንዳንዴ ደግሞ በገንዘብ ካሳ ወይንም ደግሞ የእስረኞች ለውውጥ በማድረግ የሁሉንም አካል የጋራ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲፈፀም ያዛል፡፡ አላህ ይላል ፡-

   "እነዚያንም የካዱትን (በጦር ላይ) ባገኛችሁ ጊዜ ጫንቃዎችን በኀይል ምቱ፡፡ ባደካማችኋቸውም ጊዜ (አትግደሏቸው ማርኳቸው)፡፡ ማሰሪያውንም አጥብቁ፡፡ በኋላም ወይም በነጻ ትለቋቸዋላችሁ፤ ወይም ትበዟቸዋላችሁ፡፡ (ይህም) ጦሪቱ መሳሪያዋን እስከምትጥል ድረስ ነው፡፡ (ነገሩ) ይህ ነው፡፡ አላህም ቢሻ ከእነርሱ (ያለጦር) በተበቀለ ነበር፡፡ ግን ከፊላችሁን በከፊሉ ሊሞክር (በዚህ አዘዛችሁ)፡፡ እነዚያንም በአላህ መንገድ ላይ የተገደሉትን ሥራዎቻቸውን ፈጽሞ አያጠፋባቸውም፡፡"

7. ኢስላም ሙስሊሞች በጦር አሸንፈው በመቆጣጠሯቸው ከተሞች ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦችን በመልካም እንዲኗኗሯቸው ይመክራል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ለቂብጦች መልካም መዋል እንደሚያስፈልግ እንዲህ በማለት ተናግረዋል "ግብፅን በቁጥጥር ስር ካዋላችሁ ለቂብጦች (በግብፅ የሚገኙ ክርስቲያኖች) መልካም ሁኑ፡፡ ለነሱ መጠበቅንና እዝነት አላቸውና፡፡"

በጦነት የተሸነፉና በሙስሊሞች ቁጥጥር የወደቁ ህዝቦን ክብራቸውን መጋፋት፣ ንብረታቸውን መዝረፍ፣ እነሱን ማዋረድ፣ ሃገራቸውን ማውደም በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ ባይሆን ኢስላም በመልካም መኗኗርን፣ በመልካም ማዘዝን፣ በመጥፎ ነገር መከልከልንና ፍትህን ማስፈንን ያዛል፡፡ ከነብዩ በኋላ የነበሩ ሙስሊሞችም የነብያቸውን ምክር ተግባራዊ አድርገዋል ለዚህ አይነተኛ ምሳሌ የሚሆነው ኡመር ኢብኑል ኸጣብ (ረ.ዐ) በይተል በቅዲስን በተቆጣጠሩ ጊዜ ለህዝቦቿ ቃል የገቡትን ነገር ብቻ ማንሳት ይበቃል፡፡ ኡመርም እንዲህ አለ "በአላህ ስም እጅግ አዛኝና ሩህሩህ በሆነው የአላህ ባሪያና የሙዕሚኖች መሪ ከሆነው ኡመር ኢብኑል ኸጣብ ለበይተል  መቅዲስ ህዝቦች የተሰጠ ወይም የገባ ቃልኪዳን ነው፡፡ በህይወታቸው፣ በሃብትና ንብረታቸው ላይ እንዲሁም በአምልኮ ስፍራዎቻቸው በሰላምና መረጋጋት እንዲኖሩ በእምነታቸው ምክንያት የጥላቻ መንፈስ በነሱ ላይ እንዳይኖር እና በሱ ምክንያት እንዳይጎዱ ቃል ገብቶላቸዋል፡፡ይህ ሁሉ የሆነው ኡመር ኢብኑል ኸጣብ የፈለገውን አይነት ማዕቀብና ቅድመ ሁኔታ የማድረግ ስልጣንና አቅም ባለቤት ሆኖ እያለ ነው፡፡ ኸረ ለመሆኑ እንዲህ አይነት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ወታደራዊ  ፍፁም የበላይ የሆነ ሀገር በጦርነት ለተሸነፉ ህዝቦች እንዲህ አይነት በሰላም በፍትሃዊነትና በመቻቻል የማስተዳደር ታሪክ አለማችን አስተናግዳ ታውቃለችን?

ይህ የሚያመለክተው ነገር ቢኖር ጦርነት በእስልምና የሰው ልጆችን ሰብኣዓዊ መብት ለመጠበቅ የሚደረግ እንጂ አለማዊ ፀጋዎችን ለማግበስበስ የሚደረግ ያለመሆኑን ነው፡፡

## ኢስላም ወንጀል የሰራ ሰው ምህረት የሚረግበት መንገድ ቀላልና ከሰው ልጆች ተፈጥሮ ጋር ተስማሚ ስለመሆኑ

የሰው ልጅ ከፈጣሪው ጋር ሆነ ከሚኖርበት ማህበረሰብ ጋር ከስህተት የማይጠራና ከወንጀልም ንፁህ ለመሆን የማይችል ፍጥረት ስለመሆኑ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ በማለት የተናገሩት ንግግር ያመለክታል "የሰው ልጅ ሁሉ ተሳሳች ነው። ከተሳሳቾች ሁሉ በላጬ ግን ከወንጀላቸው ተፀፅተው የሚመለሱት ናቸው።"

የሰው ልጅ ወንጀል እንዲሰራ ምክንያት አንዱ ከዚህ በፊት በነበረው የሰውና የሰይጣን የትግል ታሪክ የሚመነጭና እሱም ሰውን ከቅኑ ጎዳና ለማሳሳት የተቻለውን ሁሉ ለማድረግ ቃል በገባው መሰረት ነው። አላህ ይላል "

(ኢብሊስ) አለ «ጌታዬ ሆይ! እኔን በማጥመምህ ይኹንብኝ ለነርሱ በምድር ላይ (ኀጢአትን) እሸልምላቸዋለሁ፡፡ ሁሉንም አጠማቸዋለሁም፡፡» ሂጅር 39..."

ወንጀልንና ምህረትን በተመለከተ ኢስላም ካስቀመጣቸው ለሰው ልጅ ገር እና ለተግባራዊነታቸውም ምቹ ከሆኑ ባህርያቶች መካከል፡

1. የሰው ወንጀል የፈለገውን ያህል በወንጀል ቢዘፈቅና እድሜ ልኩን ወንጀል በመስራት ኖሮ በማያዳግም መልኩ ከልብ ተፀፅቶ አላህን እንዲምረው እስከለመነው ድረስ አላህ ወንጀልን መሃሪ የሆነ ጌታ ነው። ከቢሰኢዲኒል አልኹድሪ እንደተናገረው የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል።ሴይጣን "ጌታዬ ሆይ የሰው ልጆች በህይወት እስካሉ ድረስ እነሱን ከማጥመም አልወገድም" አለ፡ ክብሩ ከፍ ያለው ግታችን አላህም አንዲህ አለ "ባሮቼ ምህረት እስከጠየቁኝ ድረስ ለነሱ ምህረት ከማድረግ አልወገድም" ሙሰነድ ኢማው አህመድ። የአላህ መልዕክተኛም እንዲህ ይላሉ። "ወንጀል ባትሰሩ ኖሮ እናንተን አስወግዶ ሌሎች ወንጀል የሚሰሩ እና ለሰሩት ወንጀልም ጌታችን ሆይ ማረን ብለው አላህን የሚለምኑና አላህም የሚምራቸውን ህዝቦች ይፈጥር ነበር"
2. ኢስላም የተውበትን/ተፀፅቶ መመለስን በር በማንኛውም ወቅትና ሁኔታ በሩ ክፍት አድርጎታል። አላህ ይላል "...

ከበደሉም በኋላ የተጸጸተና ሥራውን ያሳመረ አላህ ጸጸቱን ከእርሱ ይቀበለዋል፡፡ አላህ መሓሪ አዛኝ ነውና፡፡" ማኢዳህ 39

የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ። አላህ በቀን ወንጀል ለሚፈጽሙ ሰዎች በሌሊት የምህረት እጁን ይዘረጋል። እንዲሁም በሌሊት ወንጀል ለሚፈጽሙ ሰዎች በቀን የምህረት እጁን ይዘረጋል። ፀሃይ በመጥለቂያዋ እስከምትወጣ ድረስ" ሙስሊም

የተውበት በር የሚዘጋበት ሁኔታ እጅግ በጣም ጠባብ ነው፡፡ አላህ ይላል “ጸጸትን መቀበል በአላህ ላይ የሚገባው ለእነዚያ ኀጢአትን በስህተት ለሚሠሩና ከዚያም ከቅርብ ጊዜ ለሚጸጸቱት ብቻ ነው፡፡ እነዚያንም አላህ በእነርሱ ላይ ጸጸትን ይቀበላል፡፡ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው፡፡”

በሁለት ሁኔታዎች ሲቀር የተውበት በር አይዘጋም፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይገልፁታል፡፡ “አላህ የሰው ልጅን በሞት ሲቃ ውስጥ እስካልሆነ ድረስ ተውበትን ይቀበላል፡፡ ” ቲርሚዚ ዘግበውታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ተናገሩ “ፀሃይ ከመጥለቂያዋ እስካልወጣች ድረስ አንድ ሰው ንስሃ ቢያደርግ አሏህ ንስሃውን ይቀበለዋል” ሙስሊም

3. ኢስላም የንስሃን ጉዳይ በጣም ቀላል አድርጎል፡፡ ተውበት በባሪያና በፈጣሪው መሃከል ያለማንም አማላጅ ወይም ጣልቃገብነትና ያለምንም አስቸጋሪነት እንዲፈፀም አድርጎታል፡፡ ባሪያው የሰራውን ወንጀል በማሰብ እጆቹን ወደ አላህ በመዘርጋት ከፈጣሪው ምህረትን መለመን ይገባዋል፡፡ አላህ ይላል፡-

መጥፎም የሚሠራ ሰው ወይም ነፍሱን የሚበድል ከዚያም (ተጸጽቶ) አላህን ምሕረት የሚለምን አላህን መሓሪ አዛኝ ኾኖ ያገኘዋል፡፡” አል ኒሳዕ 110-111

4. ከወንጀል እውነተኛ መመለስን ለሚመለሱ ሰዎች እንዲሁም በሰሩት ወንጀል ከልብ ተፀፅተው ወደ ወንጀል ላይመለሱ ቁርጠኛ እርምጃ የሚወሰዱ ሰዎች አላህ (ሱ.ወ) የሰሩትን ወንጀል ወደ መልካም ምንዳ ይቀይርላቸዋል፡፡ አላህ ይናገራል “….ፉርቃን 70…”

   ኢስላም ወንጀለኛ ለሆኑ ሰዎች ከወንጀላቸው ይመለሱ ዘንድ የምህረትን በር በመክፈት እንዲሁም በአላህ ላይ አንድም የሱ ፍጡር በወንጀሉ ምክንያት ከጌታው ተስፋ እንዳይቆርጥ አእምሮዋቸውን እና መንፈሳቸውን የሚናገር ሃይማኖት ነው፡፡

   ኢስላም የሰዎች ወንጀል የቱንም ያህል ግዙፍ ቢሆን አላህ ወንጀላቸውን የሚምርና የሚያዝንላቸውም ጌታ እንደሆነ ያስተምራል፡፡ አላህ ይላል፡-

በላቸው «እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ፡፡ አላህ ኃጢአቶችን በመላ ይምራልና፡፡ እነሆ እርሱ መሓሪው አዛኙ ነውና፡፡ …ዙመር 53…”

ይህ የሚሆነው የተፈፀመው ወንጀል በአላህና በባሪያው መሃከል ሲሆን ነው፡፡ የሰዎች መብት በመተላለፍ የተፈፀ ወንጀል ከሆነ ግን ያጎደሉትን ወይንም የወሰዱትን የሰዎች መብት መመለስና ይቅርታ መጠየቅ የግድ ይላል፡፡

5. ኢስላም አንድ ሰው መልካም ነገርን ለመስራት እውነተኛ ፍላጎት በማሳደሩ ምክንያት ብቻ በተግባር ባያውሉው እንኳን ምንዳ እንደሚከፈል የሚያስተምር ሃይማኖት ነው፡፡አንድ ሙስሊም መጥፎ ስራን ለመስራት አስቦ ይህን ተግባር በመፈፀሙ ምክንያተ ከፈጣሪው አንድ ሊደርስበት ሚችለውን ቅጣት በማሰብ ከመጥፎ ተግባር የተቆጠበ እንደሆነ አላህ ዘንድ ምንዳ ይከፈለዋል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ አላህ እንዲህ ብሏል ብለው ተናገሩ "አንድ ባሪያዬ ወንጀል መስራት ባሰበ ጊዜ በተግባር እስኪሰራው ጊዜ ድረስ መላእክቶቼን አትመዝግቡበት፡፡ ከፈፀመው ፃፉበት ለኔ ብሎ ከተወው ለሱ በመልካም ምንዳ መዝግቡለት፡፡ አንድን መልካም ተግባር ለመስራት አስቦ ነገር ግን ባይፈፅመውም እንኳን በመልካም ምንዳ መዝግቡለት፡፡ ያሰበውን መልካም ስራ ከሰራ በአስር እጥፍ እስከ ሰባት መቶ እጥፍ አድርጋችሁ መዝግቡለት" በማለት መላኢካዎችን ያዛቸዋል፡፡

6. ኢስላም ሙስሊም የሆነ ሰው የፈለገውን ያህል ወንጀል ቢዘፈቅ ከፈጣሪው እዝነት የሚጋርደው ያለመሆኑን ያስተምራል፡፡ እንዲያውም የስራ መዝገቡ ቀርቦ የአላህን ሰፊ የሆነ እዝነትና ምህረት በሚመለከትበት ቀን ምነው ወንጀሌ በበዛ ብሎ የሚመኝበት ጊዜ ሁሉ ይፈጠራል፡ ፡

   የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ "ከጅሃነም እሳት የመጨረሻ ሆኖ የሚወጣውንና ጀነትን የመጨረሻ ሆኖ የሚገባውን ሰውዬ ሁኔታ እኔ እመለከታለሁ፡፡ የቂያም ቀን ሰውዬው አላህ ፊት እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ትላልቅ ወንጀሎቹን አንሱለትና ትናንሽ የሰራቸውን ወንጀሎች ብቻ አቅርቡለት ይባላል አላህ ፡፡ እናም ትናንሽ ወንጀሎቹ ይቀርቡለታል፡፡ በዚህ ቀን ይሄን ይሄን ሰርተሃል፡፡ በዚህ ቀን ድግሞ እነዚህን እነዚህን ሰርተሃል ይባላል፡፡ አዎ ሰርቻለሁ ይላል፡፡ ትልልቅ ወንጀሎቹ እንዳይቀርቡበት በመስጋት ትንንሽ ወንጀሎቹን ከመቀበል ውጭ ሌላ ምንም አማራጭ የለውም፡፡ በእነዚህ በሰራሃቸው ወንጀሎች ልክ መልካም ምንዳ ይኖርሃል ይባላል፡፡ በዚህ ጊዜ ሰውዬውም ጌታዬ ሆይ እዚህ ያልቀረቡ ሌሎች የሰራኋቸው ወንጀሎች አሉ እኮ ይላል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በሰውዬው ንግግር የክራንቻ ጥርሳቸው እስኪታይ ድረስ ነበር ሲስቁ ተመልከጅቻለሁ በማለት ሃዲሱን የተናገረው የነብዩ ባልደረባ ተናገረ፡፡

7. አላህ እሱን የሚወነጅሉትንና ካዲዎችን ቻይ የሆነ ጌታ ነው፡፡ አላህ ይናገራል

አላህም ሰዎችን በሠሩት ኀጢአት ቢይዝ ኖሮ በወለሏ (በምድር) ላይ ምንም ተንቀሳቃሽ ባልተወ ነበር፡፡ ግን እተወሰነ ጊዜ ድረስ ያቆያቸዋል፡፡ ጊዜያቸውም በመጣ ወቅት (በኀጢአታቸው ይቀጣቸዋል)፡፡ አላህ በባሮቹ (ኹኔታ) ተመልካች ነውና፡፡ ፋጢር 45

## ኢስላም የአምልኮ ተግባራትን የሃጢአት ማስተሰርያ አድርጓል

ኢስላም ለሰው ልጆች ገርና ቀላልና ምቹ ሃይማኖት በመሆኑ የአምልኮ ተግባራትን የሃጢአት ማበሻ ወይም ማስተሰሪያ አድርጎአቸዋል፡፡

1. ኢስላም በሰዎች እንዲፈፅሙት ግዴታ ያደረገባቸው የአምልኮ ተግባራት የሚፈፅሙ ሰዎች እራሳቸውን የቻሉ ፈጣሪ ዘንድ ምንዳ የሚያሰጡ ከመሆናቸው በተጨማሪ ወንጀልን የማበስ አቅም አላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ይላሉ "አምስቱ ሰላቶች ከጁምዳ እስከ ጁምዳ፣ ከረመዳን እስከ ረመዳን በመካከል የተሰሩ ወንጀሎችን ያብሳሉ ትልልቅ ወንጀሎች እስካልሆኑ ደረስ፡፡
2. የአላህ መልዕክተኛ ይላሉ "ሃጅንና ኡምራን አከታትላችሁ ስሩ፡፡ እነሱም ድህነትን እና ወንጀልን ያስወግዳሉ፡፡ እሳት የብረት የወርቅንና ብርን ቆሻሻ ነገሮች እንደሚያስወግድ ሁሉ ትክክለኛ ሃጅ ያደረገ ሰው ከጀነት በስተቀር ምንዳ የለውም፡፡ ሰሂህ ቡኻሪ
3. ከትላልቅ ወንጀሎች መራቅ ለትንንሽ ወንጀሎች ምህረት ማግኛ ሰበብ ናቸው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

ከእርሱ ከተከለከላችሁት ታላላቆቹን (ኀጢአቶች) ብትርቁ (ትናንሾቹን) ኀጢአቶቻችሁን ከእናንተ እናብሳለን፡፡ የተከበረንም ስፍራ (ገነትን) እናገባችኋለን፡፡" ኒሳዕ 31

4. ኢስላም በሙስሊሞች መሃከል ሰላም መባባልና መጨባበጥ ወንጀል ከሚያራግፉ ስራዎች አድርጓቸዋል፡፡ ሁዘይፋ እንደተናገረው ነብዩ እንዲህ ብለዋል፡፡ "አንድ ሙእሚን ሌላውን ሙእሚን ወንድሙን ሲገኘውና እጅ ለእጅ ሲጨባበጡ በዛፍ ላይ ያሉ ቅጠላት እንደሚረግፉት ወንጀላቸውም እንደዚያ ይረግፋል፡፡"
5. ኢስላም አንድ ሰው ሲታመም፤ መከራና ስቃይ ሲደርስበት፤ ለሀዘንና ትካዜ ሲዳረግ ወንጀሉ የሚታበስበትን ክስተቶች አድርጓቸዋል፡፡ ከአቢሰኢድ አልኹድሩ (ረ.ዐ) የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል ብሎ አስተላልፈዋል፡፡ "አንድም ሙስሊም ችግርና መከራ እንዲሁም ሃዘን አይገጥመውም አላህ በነሱ ምክንያት ወንጀሎቹን ቢያብስለት እንጂ" የአላህ መልዕክተኛ በሌላ ንግግራቸው እንዲህ ይላሉ "አንድም ሙስሊም ችግርና መከራ አይነካውን እሾክም ብትሆን አትወጋውም ወንጀሉ ቢያስወግዱለት እንጂ"
6. ኢስላም ጦሃራ (ውዱዕ) ማድረግ ወንጀልን እንዲታበስ ከሚስችሉ ተግገባራት አንዱ አድርጎታል፡፡ አቢሰኢዲኒል ኹድሪ እንደተናገሩት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡፡ "ወንጀልን የሚያብስ እንዲሁም ምንዳን ከፍ የሚያደርግ ተግባር ላመላክታችሁን?" ሰሃቦችም "አዎን አንቱ የአላህ መልዕክተኛ" አሉ፡፡ "ውዱ ማድረግ በሚያስቸግር ወቅት ውዱዕን አሳምሮ

ማድረግ አንደኛውን ሶላት ሰግዶ ሌላኛውን በጉጉት መጠበቅ ነው፡፡ አንድ ሰው ከቤቱ ወጥቶ ከኢማም ጋር አይሰግድም፡፡ ሰግዶም ሌላኛውን ቀጣይ ሶላት በጉጉት አይጠባበቅም መልአክቶቹ ለዚህ ሰው ጌታችን ሆይ ማረውም እዘንለትም ብለው ዱዓ ቢያደርጉለት እንጂ፡፡"

7. ኢስላም በቀላሉ ሊሰሩ የሚችሉትን ስራዎች አላህን ማውሳትና ማወደስን ይመስል አንድ ሰው ገንዘቡን በአላህ መንገድ ላይ ሲያፈስ ፈጣሪው ዘንድ ከሚያገኘው ምንዳ እና ቅርበት ጋር ይመጣጠናል፡፡ አቢ ሁረይራ እንደዘገቡት (ረ.ዐ) ድሆች ወደ ነብዩ መጡና እንዲህ አሉት "ባለሃብቶች በገንዘባቸው ምክንያት ላቅ ባለ ደረጃና ዘውታሪ በሆነ ምንዳ በለጡን፡፡ እኛ እንደምንሰግደው ይሰግዳሉ እንደምንፆመው ይፆማሉ ነገር ግን እኛ ከምናደርገው በተጨማሪ በገንዘባቸው ሃጅና ኡምራ ያደርጋሉ፡፡ ጅሃድም ይሄዳሉ፡፡ የተቸገሩትን ሰዎች ይረዳሉ" የአላህ መልዕክተኛም "እንግዲያውስ ልንገራችሁ ይሄን የምነግራችሁን ነገር ከሰራችሁት በደረጃ የቀደማችሁን ሰው የምትርሱበት በናንተ ላይ ደግሞ ማንም የማይደርስባችሁ የሆነን በሰማይና በምድር ውስጥም ተመሳሳዩን የሰራ ሰው ሲቀር ከሌላው ብልጫ የሚያደርጋችሁ ስራ ልንገራችሁ" አሏቸው

   "ከእያንዳንዱ ሶላት በኋላ ሰላሳ ሶስት ጊዜ አላህን ታጠራላችሁ (ሱብሃን አላህ)፤ አላህን ታመሰግናላችሁ (አልሃምዱሊላህ) አላህን ታልቃላችሁ (አላሁአክበር)" አሏቸው፡፡ አቡሁረይራም በሃዲሱ መልከዕክት ላይ የተለያየ ግንዛቤ ወሰድን፡፡ ከኛ ውስጥ የተወሰነው ሰላት ሶስት ጊዜ ሲብሃን አሏህ፣ ሰላት ሶስት ጊዜ አልሃምዱሊላህ፣ ሰላሳ አራት ጊዜ አለሁአክበር ነው የምንለው አሉ፡፡ ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተመለስኩና ስለዚህ ጉዳይ ጠየቅኳቸው፡ ፡ እንዲህም አሉኝ "ሱብሃነአሏህ፣ ወልሃምዱሊላህ፣ ወሏሁአክበር ሁሉም እያንዳንዳቸውን ሰላሳ ሶስት ጊዜ ትዘክራላችሁ"

8. ኢስላም መልካም ነገር በመስራት ሃጢአት እንደሚያስተሰርይ ያስተምራል፡፡

   ሙአዝ ኢብኑ ጀበል የአላህ መልዕክተኛ "አንቱ የአላህ መልዕክተኛ ምከሩኝ" በማለት ጠየቃቸው፡፡ ነብዩም "የትም ቦታ ብትሆን አላህን ፍራ" አሉት፡፡ ጨምሩልኝ አላቸው፡፡ "ከወንጀል በኋላ መልካም ስራን አስከትል ወንጀሉን ያብስልሃልና" አሉት፡፡ አሁንም ጨምሩልኝ አላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛም "ከሰዎች ጋር በመልካም መኗኗርን ኑር" አሉት፡፡ አህመድ እደዘገቡት፡፡

9. ኢስላም አምልኮታዊ ተግባራትን በመፈፀም በምድር ላይ ከሚያስቀጡ ትናንሽ ወንጀሎች የሚያስምሩ አድርጓቸዋል፡፡ ከአቢኡማማ (ረ.ዐ) እንደተረጋገጠው አንድ ሰው ወደ ነብዩ ዘንድ መጣ፡፡ እንዲህም አለ "አንተ የአላህ መልዕክተኛ እኔ ወንጀል ፈፅሜአለሁ እና ቅጣቱን

ተግባራዊ አድርግብኝ" አለ፡፡ የአላህ ነብይም ስትመጣ ውዱዕ አድርገሃል?" አሉት፡፡ "አዎ" አላቸው "እና ስንሰግድ አብረህ ከኛ ጋር ሰግደሃል?" አሉት፡፡ "አዎ ሰግጃለሁ" አላቸው፡፡ "ተነስና ሂድ አላህ በእርግጥ ይቅር ብሎሃል" አሉት፡፡

<u>ኢስላምና የወንጀል ቤዛ (ከፋራህ)</u>

ኢስላም ለሰዎች ተፈጣሮ በጣም ቅርብ ገርና ምቹ ከሆኑ መገለጫዎቹ ሌላኛው ባህሪው አላህ የራሱምን ሆነ የሰዎችን መብት በመተላለፍ ወንጀል ለፈፀሙ ሰዎች የሰሩት ጥፋትና ወንጀል እንዲታበስ የሚከፍሉት ቤዛ ወይም የወንጀል ማካካሻዎችን ደንግጓል፡፡ እነዚህን ማካካሻዎች ተግባራዊ ያደረገ ሙስሊም ከወንጀሉ ይጠራል፡፡እንዲህ መደረጉ በተፈፀመው ወንጀልና ጥፋት ምክንያት ሁሌ በመብሰልሰል መንፈሱ በጥፋተኝነተ ስሜት እንዳይረበሽና እንዳይኖር ያስችለዋል፡ ፡ ከዚህ አንፃር የተወሰኑ የኢስላም እንዲህ አይነት ይዘት ያላቸው ገጽታዎች እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

1. ኢስላም ሰውን በስህተት ለገደለ ሰው ለፈፀመው ወንጀል ማካካሻ ወይም ቤዛ (ከፋራህ) በመክፈል ከወንጀሉ ወይም ክጥፋቱ የሚነፃበት መንገድ እንዳለ በሚከተለው የቁርዓን አንቀጽ ያመላክታል፡፡ አላህ ይላል፡-

   "ምእመንንም በስህተት የገደለ ሰው ያመነችን ጫንቃ (ባሪያ) ነጻ ማውጣትና ወደ ቤተሰቦቹም የምትሰጥ ጉማ ምሕረት ካላደረጉለት በስተቀር (መክፈል) አለበት፡፡ እርሱ (ተገዳዩ) ምእመን ሲኾን ለእናንተ ጠላት ከኾኑትም ሕዝቦች ቢኾን ያመነችን ጫንቃ ነጻ ማውጣት (ብቻ) አለበት፡፡ በእናንተና በእነሱ መካከል ቃል ኪዳን ካላቸውም ሕዝቦች ቢኾን ወደ ቤተሰቦቹ በእጅ የምትሰጥ ጉማና ያመነችን ጫንቃ ነጻ ማውጣት አለበት፡፡ ያላገኘ ሰውም ተከታታዮችን ሁለት ወሮች መጾም አለበት፡፡ አላህ መጸጸትን ለመቀበል (ደነገገላችሁ)፡፡ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው፡፡ ኒሳዕ 92…"

2. ኢስላም ወንዶች ሚስቶቻቸውን ሳይፈቱ እንደፈቷቸው በማስመሰል የማላገጣቸው ምክንያት ለፈፀሙት ወንጀል ምህረት እንዲያገኙ ዘንድ ቤዛ ወይም ማካካሻ ስራዎችን እንዲሰሩ ታዘዋል፡ ፡ አላህ ይናገራል ፡-

   እነዚያም "ከሚስቶቻቸው እንደናቶቻችን ጀርባዎች ኹኑብን በማለት የሚምሉ ከዚያም ወደ ተናገሩት የሚመለሱ ሳይነካኩ በፊት ጫንቃን ነጻ ማውጣት በነርሱ ላይ አለባቸው፡፡ እነሆ በእርሱ ትገሰጹበታላችሁ፡፡ አላህም በምትሠሩት ሁሉ ውስጥ ዓዋቂ ነው፡፡ አልሙጃደላህ 3…"

3. ኢስላም መሃላን የማፍረስ ወንጀል ለተፈፀመ ሰው ምህረት እንዲያገኝ ሌሎች ማካካሻ ስዎችን እንዲሰራ አመቻችቶለታል፡፡ አላህ ይላል፡-

አላህ በመሐላዎቻችሁ በውድቁ አይዛችሁም፡፡ ግን መሐላዎችን (ባሰባችሁት) ይይዛችኋል፡፡ ማስተሰሪያውም ቤተሰቦቻችሁን ከምትመግቡት ከመካከለኛው (ምግብ) ዐስርን ምስኪኖች ማብላት ወይም እነሱን ማልበስ ወይም ጫንቃን ነጻ ማውጣት ነው፤ (ከተባሉት አንዱን) ያላገኘም ሰው ሦስት ቀኖችን መጾም ነው፤ ይህ በማላችሁ ጊዜ የመሐላዎቻችሁ ማካካሻ ነው፡፡ መሐላዎቻችሁንም ጠብቁ፡፡ እንደዚሁ አላህ ለናንተ አንቀጾችን ያብራራል፡፡ እናንተ ልታመሰግኑ ይከጀላልና፡፡አልማኢዳህ 89

4. ኢስላም ለተሰሩ ወንጀሎችና ጥፋቶች ማካካሻ ተብለው የተቀመጡትንም ተግባራት ከገንዘብ ወይም ከአቅም ማነስ ምክንያት መስራት የማይችል ከሆነ ማካካሻ ስራዎችን የመስራት ግዴታ ከላዩ ላይ ይወርዳል። ለዚህ ጥሩ ማስረጃ የሚሆነን የዛ የነብዩ ባልደረባ የሆነው ሰውዬ ታሪክ መመልከት በቂ ነው። ይህ ሰው ወደነ ብዩ ዘንድ መጣና እንዲህ አላቸው። “አንቱ የአላህ መልዕክተኛ ለጥፋት ተዳረኩ” አላቸው “ምን ሆነህ ነው” አሉት ነብዩ። “ያመኛ እያለሁ ከባለቤቴ ጋር የግብረስጋ ግንኙነት አደረኩኝ” አላቸው የአላህ መልዕክተኛም “ባሪያ ነፃ ማውጣት ትችላለህ” አሉት እሱም አልችልም አለ “ሁለት ወር በተከታታይ መፆም ትችላለህ አሉት” እሱም “ አረ አልችልም” አለ። “ስልሳ ድሆችን መመገብ ትችላለህ” አሉት እሱም “ በድጋሚ አልችልም” አለ። የአላህ ነብይም ትንሽ ቆዩት አሉና ተምር የያዘ እቃ ይዘው ተመልሰው መጡ። “የታለ ጠያቂው” ብለው ጠየቁ። ጠያቂውም “አቤት” አለ “ይሄ ቴምር የያዘ ዕቃ ያዝና ሰደቃ አድርግ” አሉት። ሰውዬውም “ከኔ በላይ ድሃ የሆነ ማን አለ በጌታዬ ይሁንብኝ በነዚህ ሁለት ተራሮች መሃከል ከሚኖሩ ሰዎች ውስጥ (የሚኖሩበትን ስፍራ እየጠቆመ) ከኔ የባሰ በጣም ድሃ የለም” አላቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የፊት ጥርሳቸው እስኪ.ታይ ድረስ ሳቁና “በል ቤተሰቦችህን መግብበት” አሉት

## ኢስላምና  የመልካም ስራ ምንዳ ዘውታሪት

1. የኢስላም ሃይማኖት ለሰዎች ልጆች የተመቸ ከሆነው ባህሪው ሰዎች ያልሰሩትን ስራ የሚመነዱበት መንገድ ማበጀቱ ነው። ለምሳሌ ያህል ሰዎችን ወደ መልካም ስራ እንዲሰሩ ማመልከትን ይመስል። የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ
   "ወደ መልካም ነገር የሚያመላክት ወይም የሚጣራ ሰው የሱን መልዕክት ተቀብለው የሚሰሩን ሰዎች ምንዳ ያህል ከነሱ ምንም ሳይጎድል አላህ ምንዳውን ይከፍለዋል።
   ወደ ጥሜት የሚጣራ ወይም የሚያመላክት ሰው የሱን መልዕክት ተቀብሎ ወንጀል ላይ የተሰማሩትን ሰዎች በሚፈፅሙት ወንጀል ልክ በእሱ ላይ ይመዘገባል። ወንጀሉን በሰሩት ሰዎችም ላይ አንዳች ነገር ሳይቀነስ።"
   ይህ ነብያዊ አስተምህሮት እያንዳንዱን ሙስሊም በሚኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ መልካም ስነምግባር ንዲሰፍንና እንዲስፋፋ ከመጥፎ ድርጊት የፀዳ ማህበረሰብ በመገንባት ሂደት ውስጥ የድርሻውን ሚና እንዲጫወት ያበረታታዋል።
2. ኢስላም ለተከታዮቹ በህይወት እያሉ ለሚሰሯቸው መልካም ስራዎች ከፈጣሪያቸው የሚመነዱት ምንዳ በዚች ምድራዊ ህይወት ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን ከሞቱ በኋላም ለሰሩት መልካም ነገር እንደሚመነዱ ተከታዮቹን ያስተምራል እንዲሁም ተስፋ ይሰጣል። የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ። "የአዳም ልጅ ሲሞት ሁሉም የመልካም ስራ ምንዳዎቹ ይቋረጣሉ ሶስት ነገሮች ብቻ ሲቀሩ። ዘውታሪ የሆነን ሰደቃ ማድረግ፣ ሰዎች የሚጠቅም እውቀት ያስተማረ እና ለወላጆቹ ፀሎት የሚያደርግ ጥሩ ልጅ ያለው አባት ናቸው።

## ኢስላምና  የሰዎች ተፈጥሮአዊ ስሜታዊ ባህሪ የሚመለከጠበት መነፅር

ኢስላም ለተከታዮቹ ምቹና ገር፣ ቀላልና ተወዳጅ እንዲሆን ዘንድ በእለት ከእለት የሚያደርጓቸውን የህይወት እንቅስቃሴ እንዲሁም ስሜታቸውን ለማረካት የሚፈጽሟቸውን የተለመዱ ተግባራት ንያቸውን እስካስተካከሉ ድረስ ፈጣሪ ዘንድ የሚመነዱበት ተግባራት አድርጎላቸዋል። ለምሳሌ ያህል።

1. አንድ ሙስሊም ተፈጥሮአዊ የሆነውን የግብረስጋ ግንኙነት የመፈጸም ፍላጎቱ አላህ በፈቀደው መንገድ እስከሆነ ድረስና ይሄንም የሚፈፅምበት አላማው እራሱን ከዝሙት ለመጠበቅ አስቦ እስከሰራው ድረስ ይህ ስሜቱን ለማርካት የሚፈጽመው ግብረስጋዊ ግንኙነት እንደ ሌሎቹ አመልኮአዊ ተግባራት በመቁጠር አላህ ዘንድ ይመነዳበታል። አቢዘር እንዲህ ይላሉ "የተወሰኑ ሰዎች የአላህ መልዕክተኛን ጠየቁ። ሃብታሞች በመልካም ስራ ምንዳ ከኛ በለጡ እኮ። እኛ

እንደምንሰግደው ይሰግዳሉ፡፡ እኛ እንደምንፆመው ይፆማሉ፡፡ ትርፍ ከሆነው ሃብታቸው ደግሞ ምፅዋት ይሰጣሉ" የአላህ መልእክተኛም "አላህ ለናንተስ የምትሰጡትን ምፅዋት አላደረጋችሁም እንዴ? በእያንዳንዱ አላህን በምታጠሩት ንግግር ምፅዋት አድርጎላችኋል፡፡ በእያንዳንዱ አላህን በምታልቁበት ንግግር ሰደቃ አላችሁ፡፡ በእያንዳንዱ አላህን የምታመሰግኑበት ንግግር ሰደቃ አለው፡፡ በእያንዳንዱ ላኢላሃ አለሏህ በምትሉት ንግግር ሰደቃ አላችሁ፡፡ በመልካም ነገር ስታዙና መጥፎን ነገር ስትከለክሉ ሰደቃ አላችሁ፡፡ እዲሁም ከባለቤቶቻችሁ ጋር በምታደርጉት ግብረስጋዊ ግንኙነት ሰደቃ አላችሁ" አሏቸው፡፡ አንቱ የአላህ መልዕክተኛ ከኛ ውስት አንዱ ስጋዊ ፍላጎት ለማርካት ከሚስቱ ጋር በሚያደርገው ግብረስጋዊ ግንኙነት አላህ ዘንድ ምንዳ ይከፈለዋልን? ብሎ ጠየቀ፡፡ የአላህ መልዕክተኛም "እስቲ ንገሩኝ ይህ ሰው በተከለከለ መንገድ ቢፈፅመው ኖሮ ወንጀለኛ መሆኑ ይቀር ነበር? ስለዚህ አላህ በፈቀደው መንገድ እስከፈፀመው ጊዜ ድረስ አላህ ዘንድ ምንዳ የማይኖርመት ምንም ምክንያት የለም" ብለው መለሱላቸው፡፡

2. ኢስላም ሰዎች የእለት ተእለት ህይወታቸውን ለማቆየትና ለመምራት የሚያደርጓቸውን የህይወት እንቅስቃሴዎችና ስራዎች በመልካም ንያ ታስበው እስከተፈፀሙ ድረስ ፈጣሪ ዘንድ ምንዳ ይከፈላቸዋል፡፡ መብላትን፣ መጠጣትን፣ መልበስን፣ መተኛትን እና ሌሎች እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ተግባራትን ያጠቃልላል፡፡ለምሳሌ አንድ ሰው ምግብ ሲመገብና ሲጠጣ የሚያስበው ከሚመገበው ምግብና መጠጥ ጠንካራ ሰውነት እንዲኖረው አስቦ ከሆነ ጠንካራ ሰውነት ደግሞ የእለት ተእለት ስራዎቹን ጠንክሮ በመፈፀም አላህ ግዴታ ያደረገውን እራሱንና ቤተሰቦቹን ለማስተዳደር፣ ሙስሊም ወንድሞቹንም ለመርዳት እንዲሁም የአላህን ፍራቻ ሊያስገኙለት የሚችሉትን ተግባራት ለመፈፀም እስከሆነ ጊዜ ድርስ በሚመገበው ምግብና መጠጥ አላህ ይመነደዋል፡፡

   የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ "አንድ ሰው ለቤተሰቦቹ የሚያስፈልጋቸውን የኑሮ ጣጣ የሸፈነ ሰው ከፈጣሪው ዘንድ ምንዳ እንደሚያገኝ አስቦ እስከመፈፀመው ድረስ አላህ ምንዳውን ይከፍለዋል፡፡" ሰሂሁል ቢኻሪ

ሙስሊም የሚፈጽመው እያንዳንዱ ተግባር ንያውን እስካስተካከለና የሚሰራቸውንም ስራዎች የፈጣሪውን ውዴታ ብቻ በማሰብ እስከሰራቸው ድረስ አላህ ዘንድ ይመነዳባቸዋል፡፡ የአላህ ነብይ ይላሉ "በእያንዳንዱ ሙስሊም ላይ ሰደቃ አለ፡፡" ሰሃቦቹም "ምንም ገንዘብ ባይኖረውስ" ብለው ጠየቁ ነብዩም "በእጁ ይሰራና እራሱንም ይጠቅማል ለሌሎችም ሰደቃ ይሰጣል" አሏቸው፡፡ ሰሃቦችም "የሚሰራ ነገር ባያገኝስ" ብለው ጠየቁ ነብዩም " የተጨናነቀ ባለጉዳይ የሆነን ሰው

ያግዝ" አሉት፡፡ "ባያገኝስ" ብለው ጠየቁ ነብዩም "መልካም ነገርን ይስራ ከመጥፎ ነገር ይታቀብ እንዲህ ማድረጉ ለሱ ሰደቃ ነው፡፡" ብለው መለሱላቸው፡፡ ቡኻሪ

## ኢስላም በትምህርትና በስልጠና ዘርፍ ያለው ምቹነትና ገርነት

የኢስላም ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥባቸው መንገዶች የእዝነት  የማግራራትንና ከጽንፈኝነት በጠራ መልኩ  ለሰዎች ቀላልንና ምቹ የሆኑ መንገዶችን ነው የሚከተለው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ “አላህ እራሴምም ሆነ ሰዎችን እንዳጨናንቅ ሌሎችንም እንዳስጨንቅ አይደለም እኔን የላከኝ ነገር ግን አላህ እኔን የላከኝ አስተማሪና ገራገር እንድሆን ዘንድ ነው የላከኝ፡፡” ሰሂሁል ሙስሊም

1. በትምህርት፣ ስልጠናና ለሰዎች ምክር መስጠት ሂደት የአላህ መልዕክተኛ  ለሰዎች ፍቅር በመስጠት፣ መልካም ነገር እንዲገጥማቸው በመጓጓት፣ በእርጋታ እና ርህራሄ እንዲሁም ተወዳጅ በመሆን መልዕክትን የማስተላለፍ ዘይቤ ላይ የተገነባ ነው፡፡ ለዚህም ጥሩ ማሳያ የሚሆነው አንድ ባልደረባቸው ዝሙት እንዲፈጽም ዘንድ እንፈቅዱለት በጠየቃቸው ጊዜ ይህን ሰው ያስተናገዱበትን መንገድ ብቻ መመልከት በቂ ነው፡፡“ዝሙት በእናትህ ላይ ቢፈፀም ትወዳለህን” ነበር ያሉት፡፡ እሱም “በጌታዬ ይሁንብኝ ላንተም ቤዛ ያድርገኝ በፍፁም በእናቴ ላይ እንዲፈፀም አልፈልግም” ሌሎች ሰዎችም በእናታቸው ላይ እንዲፈጸም አይፈልጉም” አላቸው፡፡ “ሴት ልጅህ ላይ ቢፈፀም ትወዳለህን” አሉት፡፡፡ “በጌታዬ ይሁንብኝ አላህ ላንተ ቤዛ ያድርገኝ በፍፁም አልወድም” አላቸው “ሌሎች ሰዎችም በሴት ልጆቻቸው ላይ እንዲፈፀም አይወዱም” አለ፡፡ “በእህትህ ላይ ቢፈፀምስ ትወዳለህ” አሉት፡፡ “በጌታዬ ይሁንብኝ አላህ ላንተ ቤዛ ያድርገኝ በፍፁም አልወድም” አለ፡፡ “ሌሎች ሰዎችም ቢሆኑ በእህቶቻቸው ላይ እንዲፈጸም አይወዱም”፡፡ ነብዩም “በአባትህ እህቶች ላይ እንዲፈፀም ትወዳለህ” አሉት፡፡ “በጌታዬ ይሁንብኝ አላህ እኔን ላንተ ቤዛ ያድርገኝ በፍፁም አልወድም” አላቸው፡፡ “ሌሎችም ሰዎች በአባቶቻቸው እህቶች ላይ እንዲህ እንዲፈፀም አይወዱም” አለ፡፡ “በእናትህ እህቶች ላይስ እንዲደረግ ደስ ይልሃል” አሉት፡፡ “በጌታዬ ይሁንብኝ እኔን ላንተ ቤዛ ያድርገኝ በፍፁም አልወድም”፡፡ “ሌሎች ሰዎችም በአክስቶቻቸው ላይ እንዲከሰት አይወዱም” አለ፡፡ እጃቸውን ትከሻው ላይ አኑረው “ጌታዬ ሆይ ወንጀሉን ማረው፤ ልቡንም አጥራው፤ ብልቱንም ከወንጀል ጠብቀው፡፡” በማለት ዱዓ አደረጉለት፡፡
2. የእስልምና ሃይማኖት የሰዎችን ክብርና ምቾት እንዲጠበቅ ከሚከተልባቸው ቦታዎች ውስጥ አንዱ ተከታዮቹን በመማርና በማስተማር ሂደት ውስጥ የሚከተላቸው የትምህርትና ስልጠና መንገዶች የተከታዮቹን ክብር ምቾት እና ድሎት በጠበቀ መልኩ መካሄድ እንዳለበት ያስተምራል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ይህን የትምህርትና ስልጠና መርህ  በተግባር ለተከታዮቻቸው አሳይተዋል፡፡ ከሳቸው በኋላም ለሚመጡ ተከታዮች ሊከተሉት የሚገባ መርህ

መሆኑን መስጊዳቸው ውስጥ ገብቶ የሸናውን ያ የገጠር ሰው ያስተማሩበት መንገድ ለሁሌም ምሳሌ ሆኖ ይኖራል፡፡ ክስተቱ እንዲህ ነበር፡፡ አንድ ከገጠር የመጣ ሰው ነብዩ መስጅድ ገብቶ ሽንቱን ሸና፡፡ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦችም ሰውየው ከድርጊቱ እንዲታቀብ ሃይለቃል በተሞላ መልኩ ጮሁበት፡፡ የአላህ መልዕክተኛም “አትጭሁበት” አሉ፡፡ሽንቱን ሽንቶ ከጨረሰ በኂላም ጠሩትና እንዲህ አሉት “ይህ የመስገጃ (ፀሎት) ማድረጊያ ስፍራ ስለሆነ እዚህ አካባቢ መጸዳዳትና ማቆሸሽ ነውር ነው፡፡ ይህ መስጊድ ቁርዓን የሚቀራበትና አላህን መዘከሪያ ስፍራ ነው” አሉት፡፡ ከዚያም የአላህ መልዕክተኛ ውሃ እንዲመጣላቸው በማዘዝ የመጣውን ውሃ ሽንት የነካው ቦታ ላይ አፈሰሱበት፡፡

ይህ እንግዲህ ነብያዊው የሰዎችን ተፈጠሮ በማክበርና የማስተማር ዘዴ ነው፡፡ ማስተዋል ያለብን የመጀመሪው ሰውዬ ለመስራት እንዲፈቅዱለት የጠየቃቸው ተግባር በኢስላም ውስጥ ትላልቅ ከሚባሉት ወንጀሎች አንዱን የሆነውን ዝሙትን ነው ለመፈፀም የጠየቀው፡፡ይህ ከመሆኑ ጋር የአላህ መልዕክተኛ ይሄን አፀያፊ ወራዳ ተግባር ለመፈፀም እንዴት እኔን ትጠይቃለህ ብለው አልጮሁበትም፣አልተቆጡትም፣ አልሰደቡትም እንዲሁም ክብሩን የሚነካ ንግግርም አልተናገሩም፡፡ ሌላኛውን ከገጠር የመጣውን ሰው በምድር ላይ ካሉ ስፍራዎች ሁሉ በጣም የተቀደሰና የተከበረው መስጂዳቸው ውስጥ ሽንቱን በመሽናቱ ምክንያት አላንጓጠጡትም፣ አልጮሁበትም፣ አላመናጨቁትም፣ ክብሩንም ዝቅ በሚያደርግ መልክ አላስተማሩትም፡፡ ይህ የነብዩ ተምሳሌታዊ ድርጊት ከሳቸው በኂላ ለሚመጡ ተከታዮች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ሊከተሉት የሚገባ ስርዓት ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ይህንን መፅሀፍ በማንበብህ ሂደት ውስጥ ኢስላም ምን ያህል ለሰዎች ምቹና ገር ሃይማኖት እንደሆነ እና ለሰዎች መልካም ነገር ስትሰራም ሆነ ጥሪ ስታደርግ በጥሩ ፈገግታና አክብሮት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ግልጽ ብሎ ይታይሃል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) “ከወንድሞችህ ጋር ስትገናኝ በጥሩ ፈገግታና አክብሮት መቀበልን ከመልካም ተግባር አሳንሰህ አትመልከት” ብለው አልተናገሩምን?፡፡እንዲሁም ለሰዎች መልካም ነገርን መመኘትን ሲያስተምሩ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለው አልተናገሩምን፡፡“ለራስህ የምትወደውን ለሰዎች ውደድ”

ለሰዎች ትምህርትና የመልካም ነገር ጥሪ በሚደረግበት ጊዜ ሰዎች በማያገባቸውና በማይመለከታቸው ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት አስፈላጊና ጠቃሚ እንዳልሆነ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለው አልተናገሩምን፡፡ “የአንድ ሙስሊም እስልምናው የማማሩ ምልክት የማይመለከተውንና እና የማያገባውን ጉዳይ መተው ነው፡፡”

ሰዎች ከማንኛውም መልካም ነገር ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግና ደስተኛ ይሆኑ ዘንድ ምክንያት መሆን እንደሚያስፈልግ ከተደረጉልን ጥሪዎች ውስጥ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለው የተናገሩት ብቻ ማስታወስ አይበቃምን?፡፡

“አላህ ዘንድ በጣም ተወዳጁ ሰው ለሰዎች ጥቅም የሚሰጥ ሰው ነው፡፡ አላህ ዘንድ በጣም ተወዳጅ ስራ አንድ ሙስሊም ደስተኛ ይሆን ዘንድ ምክንያት መሆን ወይንም ጭንቁንና ችግሩን መፍታት ወይም እዳውን መክፈል ወይንም እራቡን ማስወገድ ነው፡፡ እዚህ መስጊድ ውስጥ (መዲና) አንድ ወር ኢእቲካፍ ከማድረግ የእምነት ወንድሜን የችግር ለመካፈል የማደርገው ጉዞ እኔ ዘንድ የተወደደ ነው፡፡

የአንድን ሰው ቁጣን የቻለ ሰው አላህ አይቡን ይደብቅለታል፡፡የወንድሙን ጉዳይ እስኪፈፀም ድረስ ከሱ ጋር ደፋ ቀና ያለ ሰው አላህ የቅያም ቀን የሰዎች እግር ሁሉ ሲንቀጠቀጥ የሱን እግር ቀጥ ያደርገዋል፡፡

ከላይ የጠቀስናቸው አስተምህሮቶች የአንድ ተራ ሰው ንግግር ሳይሆኑ የኢስላም ደንብ፣ ስርዓትና ህግጋት የሚወሰድባቸው ምንጭ ከሆኑት ቁርዓንና ሱና የተገኙ ናቸው፡፡ እንዲህ ዓይነት የሰው ልጆችን ንፁህ ተፈጥሮ መሰረት ያደረገ የህይወት መንገድ ይዞ የመጣውን ኢስላም ሊከተሉት አይገድምን? ባይከተሉት እንኳን ቢያንስ እንደጠላት ሊፈርጁት አይገባም፡፡ ባይሆን እንዲህ ያለውን የሰዎችን የመከባበር፣ የመቻቻልና የመፈቃቀር መርህ ይዞ የመጣውን ኢስላም እንዲያብብ፣

እንዲስፋፋ እና እንዲበለፅግ ሊደረግ ይገባዋል። ደስተኛ ሰው ማለት ለእንዲህ አይነቱ ሃይማኖት የታደለ ሰው ነው።

ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች ከኢስላም አስተምህሮት እንዲርቁ ከሚያደርጋቸው ነገሮች አንዱ እራሳቸውን ሙስሊሞች ነን ብለው የሚጠሩ ነገር ግን የኢስላም መርሆዎች፣ ስነምግባርና አስተምህሮ በህይወታቸው ውስጥ ከማያንፀባርቁ አረ እንዲያውም ከዛ የራቁ ሰዎች ጋር አብረው በመኗኗራቸው ምክንያት የተገነዘቡት ነው።

ጥቂት ሙስሊም ግለሰቦች በሚያሳዩት ተግባር ብቻ ተንተርሰህ ትክክለኛ ሰፊና ትልቅ የሆነውን ኢስላም ከትክክለኛ ምንጮቹ በተገቢው መንገድ ከመረዳትህ በፊት ግርዶሽ እንዳይሆኑብህ እመኛለሁ።

ይህችን መፅሀፍ ሰዎች የሚጠቀሙባት እንድትሆን፣ የተፃፈለትን አላማ የሚሳካ እንዲያደርግልኝ፣ለሚያነበው ሰው ሁሉ ያቀረብኩት የውዴታ ስጦታ እንድትሆንልኝና አለማችን ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ ሰላም እንድትሆን፣ሁሉም ሰው እውነትን እንዲረዳና እንዲጠብቃት ጌታዬን እለምነዋለሁ።